$1 CAN

ሐ·ዋ·ር·ያ

WWW.HAWARYA.NET - NOW IN DOUBLE LANGUAGES

# HAWARYA

ቅጽ 17 | ቁ. 4 | ፋክስ (905)799-2193 | መስከረም/ጥቅምት 2004

Vol 17 | Issue 4 | Tel (416) 459-5964 | Sep-Oct 2011 | www.hawarya.net | hawarya.publications@sympatico.ca




# "የኢትዮጵያ ቀን መስከረም 1 2004 ከመቼውም በበለጠ በድምቀት ተከብሯል"



ዶ/ር ሃይሌ ፈንታ

ይህ የቃለ ምልልስ ዓምዳችን በትምህርት ሰጭነታቸው፣ ግንዛቤን በማስፋትና ዕውነተኛን መረጃ በማስተላለፍ ለማህበረሳባችን ይጠቅማሉ ያልናቸውን ተቋማት በመመዘንና ቅድሚያ በመስጠት የምናወያይበት ነው።

በዛሬው ቃለ ምልልስ ዓምዳችን በእንግድነት የጋበዝነው የኢትዮጵያ ማህበር በቶሮንቶና አካባቢው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ሃይሌ ፈንታን ሲሆን፣ ዶ/ ሃይሌ ፈንታ በቶሮንቶ የሥነ አእምሮ ተመራማሪ ሲሆኑ ላለፉት 15 ዓመታት በሥነ አእምሮ ምርምር በበርካታዎቹ ተሳታፊና የምርምር ሃላፊ ሆነው እያገለገሉ የሚገኙ ታላቅ ኢትዮጵያዊ ናቸው

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ኦንታሪዮና ሊበራል "ላይፋቱ ተጋብተዋል"!!

## በዳልተን ማጊንቲ የሚመራው የሊበራል ፓርቲ ለሦስተኛ ጊዜ አሸነፈ፡



በብዙ የፖለቲካ ተንታኞች ዘንድ "ቶሮንቶ የሊበራሎች ከተማ ነች" ተብሎ የሚታወቅ ቢሆንም በመላ የኦንታሪዮ ክፍለ ሀገር ደረጃ ሊበራሎች የዚህን ያህል ተመችቱዋቸው ያለማቁዋረጥ ለሦስተኛ ጊዘ ወደ ሥልጣን ይመጣሉ የሚሉ ግን ተመናምነው ነበር።

በዚህ ወር መጀመሪያ አክቶበር 6/2011 በተካሄደው የክፍለ ሀገሩዋ አጠቃላይ የሕዝብ ምርጫ ከ8.7 ሚሊዮን መምረጥ የሚችል ሕዝብ መካከል የተካፈለው ቁጥር በክፍለ ሀገሩዋ ታሪክ አነስተኛ ነው ቢባልም፣ በዳልተን ማክጊንቲ "Dalton McGuinty) የሚመራውን የሊበራል ፓርቲ ለሦስተኛ ጊዜ በሥልጣን ላይ ለማስቀመጥ ችሉዋል። ሊበራሎች ተመልሰው ወደ ሥልጣን የመጡት ከነበራቸው የብዙሃን መቀመጫ 19 መቀመጫ በመቀነስ "ሥዩም መንግግስት" ለመሆን ከሚያስፈልገው 54 መቀመጫ በ"አንዲት ቁጥር" ወርደው 53 መቀመጫ አግኝተው ቀጣዩን የክፍለ ሀገሯን መንግሥት ለማቁዋቁዋም ዕድል ያገኙ ሲሆን፣ ተፎካካሪ ፓርቲዎቹ በቲም ሆዳክ (Tim Hodak) የሚመራው ተራማጅ ወግ አጥባቂው ፓርቲ (Progressive Conservative Party) ካለፈው መንግሥት የመቀመጫ ቁጥሩን በ12 በማሻሻል 37 መቀመጫዎችን ሲያሸንፍ፤ በሀገር አቀፍ ና በክፍለ ሀገራት ደረጃ በታላቅ ግስጋሴ ላይ ያለው አዲሱ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (The New Democratic Party – NDP) ሰባት ተጨማሪ ወንበሮችን በማሸነፍ የመቀመጫ ቁጥሩን ወደ 17 ወንበሮች ከፍ አድርጉዋል። የክፍለ ሀገሩን አዲሱዴሞክራሲያዊፓርቲ የሚመሩት ትልቅ አክብሮትና ተስፋ ያተረፉት እመት አንድሪያ ሆርዋዝ (Ms. Andrea Horwath) ናቸው።

የካናዳ ሊበራል ፓርቲ (Liberal Party of Canada) በኦንታሪዮ ክፍለ ሀገር ደረጃ በተከታታይ ለሦስተኛ ጊዜ ሥልጣን ላይ መቆየት መቻሉ ከብዙ ዘመናት በሁዋላ እውን በመሆኑ ለታሪክ ጸሃፊዎች አዲስ የቤት ሥራ ከመፍጠሩ በላይ ለዚህ መልካም አስተዳደርና ታሪካዊ ድል ያበቁትን መሪውን ፕሪሜር ዳልተን ማክጊንቲን (Premier Dalton McGuinty) ከፍተኛ ክብር አጎናጽፏቸዋል።

# የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት በድምቀት ተከበረ



ቶሮንቶ ውስጥ በተከበረው አዲስ ዓመት በዓል ላይ ከተገኘው ሕዝብ በከፊል

በቶሮንቶና አካባቢው ኑዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያዊያን አዲሱን ፪፲፻፬(2004) የኢትዮጵያ ዓመት በድምቀት አክብረውት ዋሉ። መስከረም 10 ቀን 2011 ዓ.ም (እ ኤ.አ) በቶሮንቶ ከተማ ክጥዋት እስከ ሌሊቱ አጋማሽ ተከብሮ የዋለው ይህ ደማቅ በዓል በሀገራዊ ባህሎችና ልዩ ልዩ ተሳትፎ ያሸበረቀ ነበር። በዕለቱ ወደ 15 ሺህ የሚገመቱ ኢትዮጵያዊያንና አፍቃሪ ኢትዮጵያዊያን የተሳተፉበት የዚህ ዓመቱ ክብረ በዓል በድምቀቱና ሥነ-ሥረዓቱ ስሜትን የማረክ መሆኑን በክብር እንግዳነትና በጸጥታ አስከባሪነት ተገኝተው የነበሩ ባልሥልጣኖች ከተሳታፊዎች ጋር ባደረጉት ልዩ ልዩ የሃሳብ ልውውጥ አንጸባርቀዋል።

በየዓመቱ የሚከበረውን የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት ክብረ በዓል የሚያዘጋጀው በቶሮንቶና አካብባኢው የሚገኘው የኢትዮጵያዊያን ማህበር መሆኑ ይታወቃል። ይህ ማህበር ላለፉት 30 ዓመታት በአካባቢው የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንን በልዩ ልዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ሲያገለግል ከመቆየቱ በላይ ሀገራዊ ባህላችንና ታሪካዊ ይዞታችን እንዲተበቅ የተቻለውን ሁሉ ማድረጉ እውነት ነው። ይሁን እንጅ ላለፉት ወራቶችህ የውስጥና የውጭ ችግሮች ገጥመውት ስለቆዩ የዘንድሮው በዓል እንዳይስተጓጎል አስፈርቶ ነበር። ይሁን እንጅ ዘግየት ብሎ የተቋቋመው በዓል አዘጋጅ ኮሚቴ በአጭር ጊዜ ዝግጅትና ቅልጥፍና እጅግ አመርቂ የሆነ እንቃቃሴ በማድረግ በዓሉ በድምቀትና በደስታ እንዲከበር አስችሏል።

የማህበሩ በዓል አዘጋጅ ኮሚቲ እንቅስቃሴውን በጀመረበት ወቅት በተመሳሳይ ሁኔታ ለመጀመሪያ ጊዜ የአዲስ ዓመት በዓል ሌላ ቦታና ቀን ላይ እናከብራለን በማለት ዝግጅት የጀመሩ ወገኖች በመከሰታቸው በቶሮንቶ ከተማ ኑዋሪ በሆኑ ኢትዮጵያዊያን መካከል ከፍተኛ መነጋገሪያ ጉዳይ ሆነ። "እባብ ያየ በልጥ በረየ" ነውና፣ እንደ ሀገር ቤቱ ሁሉ ከዚህም ልንከፋፈል ነው በማለት ሲዘከር የሚኖር ሃዘንና ንዴት ፈጠረ። ማህበረሰቡ ቁጣውን በተግባር ለመግለጥም በነባሩ ማህበር ሥር ተቋቁሞ እንቅስቃሴ የጀመረውን በዓል አዘጋጅ ኮሚቴ በቻለው ሁሉ በመደገፍና ከጎኑ በመቆም አበረታታ። ከመቼውምጊዜ የበለጠ የገንዘብ ድጋፍ በመለገስና የተቃጣውን የመከፋፈል አደጋ አጥብቆ በመቃወም ሌላ ቦታና ቀን ላይ በዓል ለማክበር መጥሪያዎቻቸውን እየበተኑ ዝግጅት ላይ የነበሩ ወገኖች ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ በወገናዊ ምክሩ አሳሰበ። የአብዛኛው ማህበረ ሰብ አባላት ፍላጎት ተሳክቶም በሕዝብ ግፊት ይሁን ወይም በሊላ ምክንያት ሌላ በዓል ለማዘጋጀት እንቅስቃሴ ላይ የነበሩ ወገኖች ዝግጅታቸውን አጠፉ በመባሉ ትልቅ እፎይታ ተፈጠረ፤ በዚህም ማህበረሰቡ አንድነቱን ጠብቆ ዓውደ ዓመቱን በጋራ አክብሮ ዋለ።






Mario Glykis
Manager
Personal Injury & Accident Benefits

Direct line: 416-734-0438
glykis@pacelawfirm.com
WWW.PACELAWFIRM.COM

MOTOR VEHICLE ACCIDENTS,
SLIP AND FALL,
BRAIN INJURIES,
SPINAL CORD INJURIES,
ACCIDENT BENEFITS,
DISABILITY CLAIMS

PACE III LAW
PERSONAL INJURY LAWYERS

OFFICE LOCATIONS
**Scarborough**, 305 Milner Ave. Suite 910
Scarborough, ON M1B3V4
**Toronto**, 295 The West Mall, Sixth Floor
Etobicoke, ON. M9C 4Z4
**Hamilton**, 987 King Street East, Suite 200
Hamilton, ON L8M 1C6
**Owen Sound**, 250 10th Street West
Owen Sound, ON N4K 3R3
**Collingwood**, 49 Huron Street, Suite 3
Collingwood, ON L9Y 1C5

LEGAL, INSURANCE AND MEDICAL EXPERTS ON STAFF
- Free initial Consultation
- No fees until settlement
- Hospital and home visit
- Get the support you need and the compensation you deserve
- Five office locations, service in 21 languages

**Hawarya- Amharic Monthly**

Owned by African Network Inc.

**Muluken Muchie**
Managing Editor/Publisher:

**Mailing Address:**
P.O. Box 66036
1116 Wilson Ave.,
Toronto, ON
Canada M3M 1G7

Tel:
**416-459-5964**

Fax:
**(905) 799-2193**

E-mail:
hawarya.publications@sympatico.ca

Web Site:
www.hawarya.net

**Graphics & Layout**
Mevlana Media Solutions Inc.
Tel: 416-789-9933
fmelani@rogers.com

Annual Subscription Rate

Canada.... Cdn$35.00

USA....... USD$45.00

Others..... USD$65.00

Institution .... $100. 00
consent of the publisher.

Canadian Heritage Patrimoine canadien

We acknowledge the financial support of the Government of Canada through the Canada Periodical Fund (CPF) for our publishing activities.

**ለሐዋርያ ደብዳቤና ጽሁፍ ለሚያቀርቡ ሁሉ መመሪያ፤**

1) የሚላኩልን ደብዳቤዎች ከ200 ቃላት ያልበለጡ ቢሆኑ ይመረጣል:: (አጫጭርና ፍሬ ነገሮችን ጨምቀው የሚያቀርቡልን ደብዳቤዎች የበለጠ የመታተም እድል ይኖራቸዋል)
2) ጥናታዊና ትምህርታዊ ሰፋፊ ጽሁፎች:-
ሀ) በኮምፒተር የአማርኛ ጽሁፍ ማቀናበሪያ የተዘጋጁ ከሆኑ ከ3 ገፆች፥
ለ) በእጅ ጽሁፍ ከቀረቡ ከ5-7 ገፆች ባይበልጡ ይመረጣል፤ ወቅታዊነት ያላቸው፥ ትምህርታዊ የሆኑ፥ ያልተዛዘዙ ... ጽሁፎች ቀድመው የመታተም እድል ይኖራቸዋል::)
3) ማንኛውም ደብዳቤም ይሁን ጥናታዊና ትምህርታዊ ጽሁፍ አቅራቢ ስሙን፥ አድራሻውንና ስልክ ቁጥሩን አብሮ መላክ ሲኖርበት፥ ከዝግጅት ክፍሉ ጋር የሚደረጉ የግንኙነት መረጃዎች በሚስጥር ይያዛሉ::
4) ለሐዋርያ የሚላኩ ጽሁፎች ሁሉ የጋዜጣው ንብረት ሲሆኑ ይዘታሰውንና መጠናቸውን ተገቢ ለማድረግ የአዘጋጆች የማስተካሻል መብት የተጠበቀ ነው::
5) በኢዲቶሪያል አምዱና የዝግጅት ክፍሉ ከሚያቀርባሰው ዝግጅቶች ውጭ፥ በዚህ ጋዜጣ ለሚቀርብ ማንኛውም ጽሁፍ ይዘት አዘጋጁና አሳታሚው ሃላፊነት አይወስዱም::

## EDITORIAL - ርእሰ አንቀጽ

# አዲስ የተስፋ ዓመት!


እንደ አባት አደሩ፣ ለሀገረ ኢትዮጵያ አዲስ ዓመት እንኳን በሰላም አደረስን እንላለን፤ አዲሱ ዓመት የሰላምና የጤና፣ የፍቅርና የአንድነት እንዲሆንልን ምኞታችን እየገለጽን የዛሬ ዓመት ለሀገራችን ምድር እንበቃ ዘንድ የአዲሱ ዓመት መሪ ምኞት አድርገናል።

ጊዜው ነግቶ በሚመሽ የቀናት ዝውውር ብቻ ሳይሆን በዓለማችን ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ፈጣን ሂደትና ሽግግር እየተለወጠ ነው። አሜሪካ መራሹ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ስልት ከ2008 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) ጀምሮ ቀውስ ያንገበበበት ሲሆን እስካሁንም አልተሻለውም። እንዲያውም የኢኮኖሚው አወቃቀር ስልት ሲናጋ የፖለቲካውን ዛቢያ በመነቅነቁ በየሀገሩ በሚታዩ የመንግሥታት ጭንቀትና አደባባይ በሚወጡ ሕዝባዊ ምሬቶች እየተገለጸ ነው። ከቱኒሲያ አስገምግሞ ግብጽ ላይ የዘነበው የመኸር ዝናብ፣ ቀጣይነት ባለው አዲስ ዑደት ከሰማይ ሰማያት እየከነፈ ከዚህ ሲሉት ከዚያ በመድረስ፣ አንዳንዴ በነጎድጓዱ ሌላ ጊዜ ደግሞ በካፊያው ምልክት ህልውነቱንና ለሁሉም ደራሽ መሆኑን እያረጋገጠ ነው። ለአይቀሬነቱ ማስረጃውና ማሳረጊያው በቅርቡ ጥቅምት 20 ቀን 2011 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) ሊቢያ ላይ የፈፀመውን ትንግርት እማኝ አድርጓል። በዚህ ዕለት ከ40 ዓመታት በላይ የሊቢያ ሥርዎ መንግሥት ቁንጮ የነበሩት አምባገነኑ ኮሎኔል ሞማር ጋዳፊ በሕዝባቸው እጅ ገብተው አሟሟታቸው ሲከፋ ታይቷል። ይህ ኩነት "ነግ በኔ"ን ለማያስቡ ጨካኝ አምባገነኖች የቀን ጨለማ ሲያስውጥ፣ ለምልዓት ሕዝቦች ደግሞ ይህን ትዕይንት ለመውለድ ጽንሳቸውን አርግዘው እንዲጠብቁት ተጨባጭ ተስፋ ሰጥቷል።

የህብረተሰብ ታሪክ በማያቋርጥ የለውጥ ሂደት ውስጥ የሚጸፍ ቢሆንም፣ በዓለም አቀፈ ደረጃ ወይም በተወሰነ የዓለማችን ክፍል ለሚፈጠሩ አንዳንድ ክስተቶች ግን፣ እየመጠነ ሲያሰፍር የሚኖረው የታሪክ መዝገብ ትልቁን ምዕራፍ ይሰጣቸዋል። ከዚህ አኳያ በ19ኛ ምእተ ዓመት መጀመሪያ ላይ የተከሰተው የኢዳስትሪ አብዮት፡ 1ኛውና 2ኛው የዓለም ጦርነቶች፣ የሩሲያ አብዮትና የኅብረተሰባዊነት ሥርዓት እውን መሆን የመሳሰሉት የሚጠቀሱ ሲሆን፣ ኢትዮጵያዊው የአድዋ ጦርነት ድልም ጉልህ ምእራፍ ከያዙት የዓለማችን ሥነክሣራዊ ታሪኮች መካከል አንዱ ነው። የአድዋችን ጦርነት ድል በተሳሳተ አመለካከት ጥቁሩ የሰው ዘር ዕጣ ፋንታው "መገዛት ነው" የሚለውን የጉልበታሞችንና የዘረኞዎችን የቃዠ አመለካከት በማረም "ጥቁርም እኩል ሰው ነው" ሚለውን ሃቅ አረጋግጦ በቅኝ ገዥዎች ላይ ስለመሰከረ ታሪካዊ ቦታው ጀርገዳና ሰፊ ነው።

ዛሬ ደግሞ በመጠኑና በፍጥነቱ ልዩ የሆነ ታሪካዊ ፍሰት ከሰሜን አፍሪቃ መንጭቶ በመውረድ የክብር ቦታውን እየያዘ ነው። በዚህ አዲስ የታሪክ ምእራፍ ውስጥ ተሳትፈው የሚያልፉ ህብረተሰቦች፣ ነገ ከዛሬው በተሻለ ሁኔታ ላይ ሊገኙ ሲችሉ፣ ተመልካቾችና አጨብጫቢዎች ሆነው ከቆሙ ግን ባቡሩ ያመልጣቸውና ቀድመው ተሳፍረው ላመለጡት መጫዎቻ ሆነው ይቀራሉ፤ ታሪክ ይህን በተጨባጭ ዘግቦ አሳይቷልና፣ የበይ ተመልካች ላለመሆን ማዕዱን አዘጋጅቶ ለመመገብ ጊዜ በሮ ሳያልፍ ለተሟላ መብትና ዕድገት ከፍተኛ ጥረትና ተሳትፎ ማድረግ ያስፈልጋል። በኢንዳስትሪው አብዮት ተሻምተው የተራመዱት እንጅ ሁሉም አገሮች አላደጉም፡ ያደጉት ግን ያላደጉትን ተጠቀሙባቸው። በህብረተሰባዊው አብዮት ሁሉም አገሮች ወደ አዲስና የተሻለ ሥርዓት አልተሸጋገሩም፤ የተሸጋገሩት ግን በህልም ላይ የነበሩትን ህብረተሰቦች አሽከር አድርገው በሁለት ጎራ ለተከፈለው ዓለማችን የፖለቲካ መደራደሪያ አደረጓቸው። እኛም ባቅማችን ከአድዋ ጦርነት ድል ማግሥት አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ባንዴራችን ፍትህ በጠማቸው ህዝቦች ዘንድ ሲውለበለብ በደስታ ፈክተን "እነ አጅሬዎች" መባልን ወደድን እንጅ አብረናቸው ሁጅም ገብተን ለነጻነታቸው አልተዋጋንላቸውም፤ ሙሉ ነጻነታቸውን ያጡ ብዙ ጥቁር ህዝቦች ከቅኝ ግዛት በሁዋላም በእጅ አዙር ቅኝ ግዛት ሥር ወድቀው እስከ አሁኗ ሰዓት ድረስ ማቀዋል። መልእክታችን በአጭሩ፤ በአንድ ወቅት አመች ሆኖ የተፈጠረ "ጊዚ" ቁሞ አይጠብቅምና ተሽቀዳድሞ በመሳተፍ ከፊተኞች ጋር መሰለፍ ያስፈልጋል፤ አለዚያ አይሞቱ አይድኑ ነገር "ሌላ ጊዜ" እስኪመጣ ለዘመናት መማቀቅ ይከተላል የሚል ነው።

በዚህ አዲስ ዓመትና ልዩ የታሪክ ምእራፍ ላይ ሆነን ለሀገራችን ኢትዮጵያና ለሕዝቧ የምንመኘው የተሟላ ሰላምና ደህንነትን፣ ዕድገትና ብልጽግናን ነው። ይህ ምኞት ደግሞ እውን ሊሆን የሚችለው የዕድሉና የማንነቱ ወሳኝ ባለቤት የሆነው ሕዝብና በተለያየ መልክ የሕዝብን ጉዳይ ወክለናል የሚሉ ወገኖች በወቅቱ መከናወን ያለበትን የጋራ ጉዳይ ተደማምጠውና ተሳስበው መሥራት ሲችሉ ነው። በአሁኑ ሰዓት በተጨባጭ በዓለም አቀፍ ደረጃ በመረጋገጥ ላይ ያለው፣ ለአዲስ ሥርዓት ለውጥና ለተሟላ መብት ስኬታማነት፣ ሕዝብ ዳር እስከ ዳር በአንድነት ቆርጦ ከተነሳና በጽናት ከታገለ ዓላማውን ለማሳካት የሚያግደው አንዳች ነገር እንደሌለ ነው። በዚህ ሂደት በአውንታነት እየተመዘገቡ ያሉ አንፀባራቂ



ሙሉቀን ሙጨ
Muluken Muchie

ድሎች ስላሉና ለፍቱህነቱ ዓለም አቀፋዊ ትኩረት ስለተሰጠው፣ በግፍና በጭቆና ቀንበር ሥር ያሉ ሕዝቦች ፈጥነው ከተጠቀሙበት አዲስ እድል ተከፍቶላቸዋል።

አምባገነኖች እስከዛሬ ሲያስፈራሩበት የኖሩት ረምራሚ ሠራዊታቸውና እቶን እሳት ተፊ ጠመንጃቸው ነበር። ለዛሬው ሕዝባዊ ትግል የአምባገነኖች ጦር፣ መትረየስና ደማሚት አቅመቢስ ብቻ ሳይሆን ከተጠቀሙበትና የሕዝብን ቁጣ በጭፍጨፋ ለመግታት ከሞከሩ የራሳቸውን አሟሟት ያከፉባቸዋል። ስለዚህ እስካሁን ሲሆን ባይታይም ለብልጥ አምባገነኖች ቆርጦ በተነሳ ሕዝብ ላይ "ከመተኮስ መለምሰስ" አማራጫቸው እንደሚሆን ይገመታል። ከዚያ በፊት ግን የሕዝብ ወገኖችንና አብሪዎችን አስቀድመው ለመመንጠር ከመሯሯጣቸው በተጨማሪ፣ ሕዝብን ከሕዝብ፣ ታጋዮችን ከታጋዮችና በሕዝብና በታጋዮች መካከል ክፍፍል መፍጠር፣ ማጋጨትና ማደናበር ይሁነኝ ብለው ሊከተሉት የሚገባ ዋና ስልታቸው ነው። ይህን ያልተረዳ ብሎም ለመቋቋም ብልሃት ያነሰው ሕብረተሰብና ታጋይ ቢኖር በሚያበራው የዘመናችን የለውጥ ሂደት ውስጥ ሊመለከትና ሊራመድ ይቸግረዋል።

የተደራጀ ሁሉ የሕዝብ ወገን ነው ባይባልም፤ ሕዝባዊ ትግሉን መስመር ለማስያዝና በድል ለማጠናቀቅ መርህ ያላቸው ድርጅቶችና እንቅስቃሴዎች አማራጭ የሌላቸው መሳሪያዎች ናቸው። በአምባገነኖች ሊቋቋሙ የሚችሉና የመሩ መስለው የሚያመኩ አሳቲያን ድርጅቶች ወይም እንቅስቃሴዎች ሊኖሩ/ሊፈጠሩ እንደሚችሉ ግምት ውስጥ አስገብቶ፣ በሕዝብ ጎራ ያሉ ማናቸውም ድርጅቶችና እንቅስቃሴዎች መተባበር፤ መደጋገፍ፤ መደማመጥና በጋራ የሥምሪት ፕሮግራም መንደፍ ለነገ የማይሉት ሃላፊነታቸው ሊሆን ይገባዋል፤ ሕዝባዊ ትግሉን የተሳካ ለማድረግ በተቻለ መጠን አንድ ድምጽና አንድ ዓላማ መያዝ ያስፈልጋል። ይህም ሊሆን የሚችለው የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችና ወኪሎቻቸው መቀራረብና መደማመጥ ሲችሉ ነው።

በደልና ብሶት የጠናበት ሕዝብ በአምባገነኖች ላይ ገንፍሎ ሲነሳ ለዕድሉ ወሳኙ ራሱ ሕዝቡ መሆኑ ጥያቄ ውስጥ ባይገባም፤ የድሉን ቀን ለማቅረብና ዓለም አቀፋዊ ድጋፍን በቀላሉ ለማትረፍ የውጭ ግንኙነት አያያዙን ማሳመር ይጠበቅበታል። "ከአነጋገር ይፈረድ፡ ከአያያዝ ይቀደድ" እንዲሉ፣ የፖለቲካ መሪዎች አንደበትና አቀራረብ ብልህነት የተመላበት ሊሆን ይገባል። ዓለም ጠባብ ናት፣ ሁሉም ይደማመጣል፡ አንዱ ሌላውን ይከታተላል፤ ሁሉም ጥቅምና ጉዳቱን ያመዛዝናል፤ ክፍፍልን እያራገበም ከሚመቸውና ከሚመርጠው ጎን ተሰልፎ የሌላውን ዕድል እስከቻለ ድረስ ይቀናቀናል። ጠላትን ቀንሶ ወዳጅን ለማብዛት የፖለቲካ መሪዎች ሚና ከፍተኛ ነው። የውጭ ግንኙነት አላማቸው በሀገራቸው ጉዳይና ጥቅም ላይ ፍትሃዊና ሚዛናዊ የሆነ ግንኙነት መሻታቸውና ለዚህም ግንባራቸውን ሳያጥፉ የሚቆሙ መሆኑን ማረጋገጥ ነው። ከዚህ አኳያም ከማንም ህጋዊ መንግሥት ጋር በአቻነትና የሀገራቸውን ሁለገብ ጥቅም ባስጠበቀ ሁኔታ ለመቀራረብ ፍላጎታቸው መሆኑን ማንፀባረቅ ይኖርባቸዋል።

አዲሱ የሀገራችን ዓመት ከሀገር ውጭ እስከ ውስጥ በጋራ ዓላማ ላይ ያተኮረ ትብብርና መደጋገፍ እንዲሆን ምኞታችን ነው። ለከሌና ለነእከሌ ሳይባል የጋራ አላማን በሚያራምድ የጋራ ጉዳይ ላይ ማነጻጸር ባህርያችን ይሁን። በውጭ ሀገሮች ኑዋሪ የሆነው ኢትዮጵያዊያን ነጻነቱና አቅሙ አንጻራዊ በሆነ ደረጃ ስላለን፣ ለምናቅዳቸውና ለምንሠራቸው እንቅስቃሴዎች ሁሉ አንደምታቸውን ገምግመንና የጋራ ሀገራዊ ጠቀሜታቸውን መዝነን ሥራ ላይ ማዋል እንደሚገባን እንገንዘብ በማለት በድጋሜ መልካሙን ሁሉ እየተመኘን የከርሞ ሰው ይበልን ብለናል።

# አይጥ ለሞትዋ የድመት አፍንጫ ታሸታለች!

(ብስራት አማረ ማነው?)

ገብረመድኅን አርአያ
(ፐርዝ፣ አውስትራሊያ)

ተ.ሓ.ህ.ት ብሎ ራሱን የሰየመው የዛሬው ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ ፋሺስቱ ፓርቲ፣ በየካቲት ወር 1967 ዓ.ም. ትግሉ ከጀመረበት ቀን አንስቶ በትግራይ ሕዝብ የፈጸመውን አሰቃቂ የወንጀል ግፍ ብዙ ኢትዮጵያዊያን ያውቁታል። የትግራይ ሕዝብ ያ የ17 ዓመት የወያኔ ትግል "ዘመነ እልቂት" ይሉት ነበር። ዘመነ እልቂቱ ከደደቢት ትግራይ አልፎ አሁን በኢትዮጵያ ሀገራችን ሙሉ በሙሉ ሸፍኖ ወደ 'ዘመነ ጨለማ" ተሸጋግሯል።

አሁን ለማንሳት የፈለግኩት፣ በውጭ አገር የምትኖሩ ኢትዮጵያውያን ወገኖች ስለ ወያኔ ማንነትና ማወቅ ያለባችሁ ጉዳዮች ብዙ ነገሮች አሉ። እዛው በየአገሩ በምትኖሩባቸው ከተሞች ውስጥ የወያኔ ድርጅታዊ ተልዕኮ ለማሳካት ከትግራይ የመጡ የፋሺስቱ ወያኔ ደቀ መዛሙርት፣ በጥቅም የተገዙ አድርባዮች እና ካድሬዎች እንዲሁም ሰላዮች በመሆን በምትንቀሳቀሱባቸው ማሕበራዊ እና ፖለቲካዊ ወይንም ሃይማኖታዊ ሕይወታችሁ ውስጥ ተመሳስለው በመግባት አንድነታችሁን ለመበጥበጥ የተሰማሩ እንዳሉ በተለያዩ ሰዎች እንደተገለጸ ይታወሳል። ከተጠቀሱት የወያኔ ካድሬዎች ውስጥ በትግራይ ሕዝብ እና በኢትዮጵያ ላይ በማን አለብኝነት ተነሳስተው ለብዙ ኣመታት ሰብአዊ እና አገራዊ ወንጀሎችን የፈጸሙ እና ያስፈጸሙ የወያኔ እስር ቤት እና የስለላው መዋቅር በሃላፊነት የሰራ ብስራት አማረ ማን ነበር? የሚለውን ዛሬ ግልጽ ላደርግላችሁ እሻለሁ።

ብስራት አማረ ማን ነው?

ብስራት አማረ ትውልዱ አክሱም እስከ 9ኛ ክፍል አክሱም አውራጃ የተማረ ሆኖ ወደ ህወሓት ትግል የተቀላቀለው በ1968 ዓ.ም. ኢጋማሽ አካባቢ ነበር። ብስራት አሁንም የፋሺስቱ ወያኔ ምርጥ ታማኝ እና ሙሉ አባልነቱ እንዳለ ሆኖ በውጭ አገር እየኖረ አሁንም የፋሺስቱ የወያኔ ፖለቲካ እና ፖሊሲ አራማጅ እና ጠበቃ በመሆን በየራዲዮኑ እና ፓል ቶክ ስለ ወያኔ ብፁእነት ሲሰብክ እያደመጥነው ነው። ያ አልበቃ ብሎት አለቆቹን በመወከል ተቃዋሚዎችን በመዝለፍ አልፎም አገር ውስጥ በመሄድ በጌቶቹ ፍረድ ቤት የክስ ማሕደር በመክፈት ተቃዋሚዎችን ለማንገላታት እየሞከረ ነው። ይህ ደግሞ አዲስ ስልት እና አሳፋሪ ተግባር ስራዩ ብሎ ተያይዞታል። ህ.ወ.ሓ.ት. የተባለው ድርጅት የፋሺስትነት ባሕሪይ እንዲኖሮውና እና በታጋዮችና በኗሪዎች ላይ ፋሺስታዊ ድርጊቶች እንዲፈጸም አስተዋጽኦ ካደረጉት የወያኔ ካድሬዎች አንዱ ብስራት አማረ እንደነበር ብዙ ታጋዮች ያውቁታል። ብስራት አማረ ዛሬ ውጭ አገር እየኖረ ወያኔን በመደገፍ ቢለፈልፍ ሰው እየገረፈ እና እየገደለ ስለገነባው ድርጅት ጥብቅና ቢቆም ባሕሪያዊ ነውና መገረም የለብንም።

ብስራት አማረ ማን ነው?

ታሪኩን ትንሽ ወደ ኋላ በመመለስ እስኪ እንዳስስ። የተ.ሓ.ህ.ት (ህ.ወ.ሓ.ት) መሪዎች ከመነሻው ይዘውት የመጡ የድርጅቱ የትግል መርሆ ተግባራዊ ሲያደርጉት የነበረውን ፀረ ኢትዮጵያ፣ ፀረ አማራ፣ እና ፀረ ሕዝብ እንዲሁም በዋነኛነት ኤርትራን ለማስገንጠልና አልፎም የትግራይ ሪፑብሊክ መንግሥት ለማቋቋም አመራሩ ሲከተለው የነበረውን ፖሊሲውና አካሄዱ አብዛኛው ታጋይ አገርና ሕዝብን የሚጎዳ ጥፋት መሆኑን ከተገነዘበ በኋላ፣ አመራሩ እየተከተላቸው የነበረውን ጸረ ሕዝብ እና ፀረ ኢትዮጵያ እምነቶቹ ባጭሩ መገታት አለበት ብሎ በመወሰን ዲሞክራሲያዊ የሆኑ ጥያቄዎች በማስነሳት መንቀሳቀስ ጀመረ። በታጋዩ ውስጥ የተንጸባረቀውና የተነሳው ቅሬታና እንቅስቃሴ በትግራይ ሕብረተሰብ ውስጥም በየቦታው ተመሳሳይ ሆነ። ሕዝቡም የጥንት ቅድመ አያቶቻችን እና ወላጆቻችን ደማቸውን እና አጥንታቸውን ከስክሰው የጠበቋትን እና ያስረከቡንን ኢትዮጵያን ዛሬ የህወሓት መሪዎች ከሻዕቢያ ጋር ተባብረው አገራችንን ሊበትኗት ነው የሚል ስጋት ከገጠር እስከ ትግራይ ከተሞች ተንፀባረቀ። በ1968 ዓ.ም. መጨረሻ የወያኔ መሪዎች ይህ የታጋዩ እና የሕዝቡ እንቅስቃሴና ቅሬታ ስላስደነገጣቸው በድርጅታችን ውስጥ ከመቀሌ፣ከተምቤን፣ ከአዲግራት፣ ከራያና ከሁለት አውላዕሎ አውራጃዎች ተሰባስበው "ሕንፍሽፍሽ" (ብጥብጥ) ፈጠሩ በማለት የተነሳውን የዲሞክራሲ እንቅስቃሴ ለማዳፈን ተነሱ። ሃቁ ግን ታጋይ ሁሉ የተነሱት ቅሬታዎች በሰላማዊ እና በዲሞክራሲያዊ መንገድ ማንጸባረቃቸው እንጂ ህንፍሽፍሹን የፈጠሩት እራሳቸው አመራሮቹ ነበሩ።

በዚህ ጊዜ አመራሩ እንቅስቃሴውን ለመግታት ለኤርትራ የቆመበትን ፖሊሲውን ለማራመድ እና እንዲሁም ፀረ-ሕዝብነቱ እና ፀረ-ኢትዮጵያ እርምጃዎችን ለመውሰድ ያመቸው ዘንድ አመራሩ የሚከተሉትን እርምጃዎች በመውሰድ አፈና ማካሄድ ጀመረ። አመራሩ የወሰዳቸው እርምጃዎች፡ ዚያው ወቅት የነበሩ የድርጅቱ ታዋቂ መሪዎች ስም ዝርዝር 1ኛ ስብሓት ነጋ 2ኛ መለስ ዜናዊ 3ኛ አረጋዊ በርሄ 4ኛ አባይ ጸሃየ 5ኛ ስዩም መሰፍን 6ኛ ግደይ ዘርአጽዮን 7ኛ አውኣሎም ወልዱ 8ኛ ስየ አብርሃ 9ኛ አጽብሃ ዳኘው (በመለስ ዜናዊ የተገደለ) ተሰብስበው በ1968 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ 06 (ሓለዋ ወያኔ/እስር ቤት) እንዲስፋፋ በመወሰን በሁለት ደረጃ አስቀመጡት። ቀዋሚ እና ተንቀሳቃሽ እስር ቤት።

1ኛው - ቀዋሚ 06 ሓለዋ ወያነ የሚባለው፡ በስፋት ሲከፈቱ 1- ቡምበት 2- ባኽላ 3- ዓይጋ 4- ወርዒ 5- ፃኢ 6- ዓዲ በቅሎ 7- ዓዲ ጨጓር 8 ሱር 9- በላሳ-ማይ ሓማቶ 10- ቆሎ ምሽላ.. ወዘተ..ወዘተ.. ሲከፈቱ እነኚህን ለማንቀሳቀስ የተመረጡ ሰዎች ለአመራሩ ታማኝ የሆኑ ብቻ ነበሩ።

2ኛው ተንቀሳቃሽ 06 ወይንም ሃለዋ ወያነ/Mobile የሚባለው ነው። ስራ ተግባሩ የሚከተሉትን የጭካኔ እርምጃዎች፣ ዓለም አቀፋዊም ሆነ ሃይማኖታዊ ወይንም ባሕላዊ ሕጎችን ሳይከተል በማን አህሎኝነት በጠመንጃ ጉልበት ተንተርሶ፣ መፈጸም ነው።

1. ሰላመዊም ሆነ ተጋይ ወንድ፣ ሴት፣ ሽማግሌ፣ ቄስ፣ ድያቆን፣ ቃዲ፣ ሓጂ፣ ሸኽ ሳይል የፈለጋቸውን ጥፋት ይኑረው አይኑረው በስማ በለው እና በአሉባልታ ሰውን አፍኖ መጥለፍ (kidnapping)
2. በተለያዩ የትግራይ ከተሞች ውስጥ ድርጅቱ ነብሰ ገዳይ ተኳሾችን አሰርጎ በማስግባት የሚፈልጋቸውና አብረዋቸው ድንገት የቆሙትን ሲዝናኑ የነበሩትንም ያልተፈለጉ ንፁሃን ጭምር በጅምላ በተገኙበት ቦታ ሰልሎ በመግባት መግደል፡

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

SHARMA & SHARMA

BARRISTERS, SOLICITORS & NOTARY PUBLIC
Also of the Middle Temple, London, England, Barrister -at- law

We work for you
Highly successful and Affordable

OVER 50 YEARS COMBINED EXPERIENCE



Ishwar Sharma, LL.B

CRIMINAL
- Theft
- Impaired Driving
- Assault
- Family Law
- Bail Hearing

IMMIGRATION
- Visitor Invitation Letter
- Family Sponsorship
- Detention Review
- Affidavits Sworn



Roop Sharma, LL.B



Tel.: 416-461-0467
Tel: 416-461-1777

942 Gerrard Street E.
Toronto, ON M4M 1Z2

# “የኢትዮጵያ ቀን መስከረም 1 2004 ከመቸውም በበለጠ በድምቀት ተከብሯል”

ከገጽ 1 የዞረ

ዶክተር ሃይሌ በቀድሞው የቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ዩኒቨርሲቲ ከጎንደር ጤና አጥጠባበቅ ኮሌጅ በጤና አጠባበቅና በህክምና የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ከschool of public health and tropical medicine በ ኢፒዲሚዮሎጂ የማስተር ዲግሪ፣በካናዳ ሚግል ዩኒቨሲቲ ኢፒዲሚዮሎጂ እና በባዮስታትስቲክስ የዶክተሬት ዲግሪያቸውን፣ በተጨማሪም ታንዛኒያ በሚገኘው የደቡብና ምስራቅ አፍሪካ ማኔጅመንት ኢንስትቲዩት የአስተዳደር ትምህርታቸውን ተከታትለዋል።

ዶክተር ሃይሌ ፊንታ በሃገራቸው ኢትዮጵያ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ከያዙበት ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ የሃላፊነት፣ የመምህርነትና የምርምር ሙያ ህዝባችንና ሃገራችንን አገልግለዋል። የቀድሞው የጂማ ጤና ሳይንስ ኢንስትቲዩት አሁን የጂማ ዩኒቨርስቲ ተብሎ የሚታወቀውን ተቋም ከመሰረቱት አንጋፋ ኢትዮጵያውያን አንዱ ሲሆኑ በዚሁ ተቋም በሲንየር ሌክቸረርነትም አገልግለዋል።

ካናዳ በነዋሪነት ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ በሥነ አዕምሮ፣ በኤች አይ ቪ፣ በስደተኛ ጤንነትና በማህበራዊ ኑሮ ዙሪያ ምርምር በማድረግ አጥጋቢ ውጤት ያመጡ ሲሆን ይህ የምርምር ውጤታቸው በበርካታ ዓለም ዓቀፋዊ የምርምር መጽሄቶች ከመስፈሩም ባሻገር ላደረጉትም የማህበረሰብ ምርምር አስተዋጽዖ ከፍተኛ ሽልማቶችን አግኝተዋል።

በሃገራችን ኢትዮጵያ የአእምሮ ጤና አገልግሎት እንዲሻሻል ባደረጉት ከፍ ያለ ጥረት የሳይካትሪስቶች ስልጠና ፕሮጀክት በመንደፍ ከቶሮንቶ ዩኒቨርስቲ ባገኙት ድጋፍ መሰረት ከቶሮንቶ ዩኒቨርስቲ በሚላኩ ፕሮፌሰሮች ስልጠናው ከ2003 ዓ.ም ተጀምሮ ሲካሄድ እጅግ የላቀ ውጤትን በማሳየት በሃገራችን በዚህ ሙያ ረገድ የነበሩትን 11 ባለሙያዎች በአሁኑ ሰዓት ከ40 በላይ እንዲሁኑ አድርጓል። የስልጠናው ፕሮጀክት ባስገኘው የላቀው ውጤትም የአሜሪካን ኮሌጅ ስይኪያትሪስቶች አዋርድ የተባለውን ከፍተኛ ሽልማት ከአሜሪካን ሃገር አግኝተዋል።

እናም እኒህን ምሁር አሁን ለቶሮንቶና አካባቢው ማህበረሰብ እያበረከቱ ስላላለው በጎ ሥራቸው እንዲያዋዩን መጋበዝ በመቻላችንና ጥያቄያችንም ተቀብለው ስለቀረቡ በዝግጅት ክፍላችንና በአንባቢዎቻችን ስም ከፍ ያለ ምስጋና እናቀርባለን- መልካም ቆዩታ።

ሐዋርያ - እስኪ ለመንደርደሪያ እንዲረዳን በመጀመሪያ ስለማህበራችንና እንዴት እንደሚተዳደር ለአንባቢዎቻችን ይግለጹልን?

ዶ/ር ሃይሌ - የኢትዮጵያ ማህበር በአንድነት መርሆ ላይ የተመሠረተ፣ የጎሣ፣ የፖለቲካ፣ የሃይማኖት የመሣሠሉትን ልዩነቶች ሳያደርግ ለአዲስ መጪ ኢትዮጵያውያን የተለያዩ የሠፈራ አገልግሎቶችን (settlement services) እንዲሰጥ የተቋቋመ ድርጅት ነው።

ማህበሩ ከተቋቋመ 30 ዓመት ሲሆነው፤ የሚተዳደረውም ከለጋሽ ድርጅቶች በሚገኝ የባጀት ድጋፍ ነው።ድርጅቱ የሚመራው ነፃ አገልግሎት በሚሰጡ የቦርድ አባላት ሲሆን በአሁኑ ጊዜ 7 ሠራተኞች አሉት። ከነዚህም ውስጥ 3ቱ ቋሚ ሲሆኑ፣ 4ቱ ደግሞ ጊዜያዊ ሠራተኞች ናቸው። ማህበሩ በአሁኑ ጊዜ አራት ፕሮግራሞችን ያካሂዳል። እነርሱም፣

1) በኑሮ ለሚያጋጥሙ ችግሮች እርዳታ ፕሮግራም

(2) የአዛውንቶች አገልግሎት

(3) የአዲስ መጭዎች ምክር አገልግሎት

(4) የኤች አይቪ ኤይድስ ትምህርት አገልግሎት ናቸው። በቅርብ ጊዜ ደግሞ የወጣቶች አገልግሎት ፕሮግራም ይጀምራል።

ሐዋርያ - ማህበሩ በዛ ያሉ ፕሮግራሞችና አስፈጻሚ ሠራተኞች እንዳሉት/እንደነበሩት ይታውቃል ለፕሮግራሙ ማንቀሳቀሻና ለሠራተኛ በጀት ገቢውን ከየት ያገኛል?

ዶ/ር ሃይሌ - ከማርች 31 ቀን 2011 ዓ.ም. በኋላ ሁለት ትላልቅ ፕሮግራሞች ባጀታቸው በመታጠፉ ምክንያት ተዘግተዋል። እነዚህም ፕሮግራሞች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት አገልግሎትና የአዲስ መጭዎች ምክርና ድጋፍ አገልግሎት ናቸው። ከፌዴራላዊ መንግሥት የኢሚግሬሽን ሚኒስቴር (CIC) ለማህበሩ በየዓመቱ ይሰጥ የበነረው ባጀት በመቋረጡ ፕሮግራሞቹ ከመዘጋታቸውም ባሻገር በቀሪዎቹ አገልግሎቶችም ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አሳድሮአል። በዚህ ባጀት መታጠፍ ምክንያት 19 ሠራተኞች ከሥራ ተሰናብተዋል።

ሐዋርያ፡ ለጋሽ ድርጅቶች (Funder) ስንል ምን ማለታችን ነው?

ዶ/ር ሃይሌ - ለጋሽ ድርጅቶች (funders) ማለት፤ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ማህበሩ ለሚሰጠው አገልግሎት የገንዘብ ድጋፍ ወይም በጀት የሚሰጡ፣ (እርዳታ የሚያደርጉ) ማለት ነው።

ሐዋርያ - ማህበራችንን በከፍተኛ ደረጃ ይረዳ የነበረው የካናዳ ፌዴራል መንግስት ድጎማውን እንዳቋረጠ ባለፉት ወራቶች በተለያዩ የዜና ማሰራጫዎች በሰፊው ተዘግቧል እስኪ በቶሮንቶ እና አካባቢው ለምንኖረው ኢትዮጵያውያን ይህንን ድጎማ አስመልክቶ እንዴትና ለምን እንደተቋረጠ ? ይህንንም ተመርኩዞ በማህበራችን ላይ ያደረሰውን ጉዳት ዘርዘር አድርገው ቢያስረዱን

ዶ/ር ሃይሌ - ከላይ እንደገለጽኩት በፌዴራላዊ መንግሥት የኢሚግሬሽን ሚኒስቴር (CIC) ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት አገልግሎትና ለአዲስ መጭዎች ምክርና ድጋፍ አገልግሎት ፕሮግራሞች ለብዙ አመታት ይሰጥ የነበረውን ባጀት በድንገት ሳይታሰብ ከማርች 31 ቀን 2011 ጀምሮ እንዲታጠፍ ወስኗል።

ይህ በኢትዮጵያ ማህበር ላይ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም በርካታ ድርጅቶችም ላይ የደረሰ ችግር ነው። ነገር ግን ውሳኔው በኢትዮጵያ ማህበር ላይ ያስከተለው ችግር ቀላል አይደለም። በዚህ ባጀት መታጠፍ ምክንያት 19 ሠራተኞች ከሥራ ተፈናቅለዋል። የማህበሩ ቢሮ ኪራይና የተለያዩ መገልገያ ቁሳቁሶች መግዣ ወጭ የሚሸፈነው ከዚህ ባጀት ስለነበረ በማህበሩ ላይ ያደረሰው ተፅእኖ ከባድ ነው። የ”CIC” በጀት መታጠፍ ውሳኔ በበቂ መረጃ ላይ ያልተመሠረተ ስለነበረ ጉዳዩ ለፌዴራል ፓርላማ ቀርቦ እንዲታይልን አቤቱታ አቅርበን ስለነበረ ፓርላማው ሁኔታውን አጥንቶ የተሰጠው ውሳኔ ትክክል ስላልሆነ እንዲነሣ በድምፅ ብልጫ ወስኖ ነበር። ነገር ግን የሚኒስቴሩ መሥሪያ ቤት የፓርላማውን ውሳኔ ተግባራዊ ማድረግ አልቻለም። CIC የብዙ ድርጅቶችን ባጀት ሲያጥፍ በበቂ ጥናታዊ መረጃ ላይ ተመርኩዞ እንዳልነበር በብዙ መገናኛዎች ተገልጿል። ለዚህም በቶሮንቶ ስታር የወጣውን “Agencies” Funding rejected despite passing marks” (Sunday, June 19, 2011) የተሰኘ ጽሑፍ ማንበብ ጠቃሚ ይመስለኛል።

ሐዋርያ - ይህንን ዓይነት ድጎማ ወይንም ተመሳሳይ እርዳታ የሚገኝበት ዘዴ ወይም አማራጭ አለ ወይ ? ካለስ ማህበራችን ምን ጥረት እያደረገ ነው?

ዶ/ር ሃይሌ - ከለጋሽ ድርጅቶች የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ብዙ ጥረትን ይጠይቃል።መልካም የሥራ ግንኙነት መፍጠር፣ ፕሮጀክቶችን ነድፎ ማቅረብ፣ ድርጅቶቹ በማህበሩ ላይ እምነት እንዲያድርባቸው ማድረግ የመሣሠሉት በጣም አስፈላጊ ናቸው። በአሁኑ ጊዜ ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር ያለንን መልካም የሥራ ግንኙነት እያጠናከርን ነው። የማህበሩን ድርጅታዊ አቋምና አሠራር በኤክስፐርት አስገምግመናል። በዚህ ግምገማ ውጤት ላይ በመመርኮዝ የአጭርና የረጅም ጊዜ የልማት ዕቅድ ለማውጣትና ለመንቀሳቀስ እየተዘጋጀን ነው። የማህበሩ ግምገማ የሚጠቅመው እቅድ ለማውጣት ብቻ ሣይሆን ከለጋሽ ድርጅቶች የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ጭምር ነው። ይህ ዓይነቱ የሰከነ እንቅስቃሴ ለማህበራችን እድገት በጣም ወሳኝ ነው።

ሐዋርያ - ማህበራችን የረጅም ዓመታት የውስጥ ችግር እንዳለበት ይታወቃል በዚህም የተነሳ ከጊዜ ወደ ጊዜ ችግሩ እየተባባሰ መጥቶ የማህበረሰባችን መነጋገሪያ ርዕስ እስከ መሆን ደርሷል ከእንዲህ ዓይነት አዙሪት ወጥተን ይህንን አንጋፋ ማህበር የተሻለና ራሱን የቻለ እንዲሆን የታቀደ ወይንም የሚሰራ ነገር አለ ወይ?

ዶ/ር ሃይሌ - የኢትዮጵያውያን ማህበር ውስብስብ በሆነ ውስጣዊ ችግር ተተብትቦ የቆየ ድርጅት ነው። ችግሩ አሁን የተፈጠረ ሳይሆን ከማህበሩ ጋር አብሮ የቆየ በሽታ ነው። የዚህ ማህበር ዋና ችግር አንድነት ያለመኖሩ ነው። በአብዛኛው ጊዜ ከአንድነት ይልቅ በልዩነት ላይ ማተኮር፣ በቡድን ተከፋፍሎ መሻኮት፣ መጠላለፍ የሠፈነበት ተቋም ስለነበር ማህበሩን ለማሳደግ እጅግ አስቸጋሪ ነው።እንደሚታወቀው ሁሉ አብዛኛው የማህበረሰባችን አባላት በስደተኛነት የመጣን እንደመሆኑ መጠን ብዙ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ያጋጥሙናል። ከነዚህም ችግሮች ተላቆ ሌሎች ካናዳውያን ከደረሱበት የእድገት ደረጃ ለመድረስ ብዙ ትዕግሥትና ሥራ ይጠይቃል። ብዙዎቹ እንደኛ ወደ ካናዳ ተሰደው የመጡ ወገኖች አሁን ካሉበት ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ የደረሱት፣ በመደጋገፍ በአንድነት ታግለው እንጂ በቡድን ተከፋፍለው እርስ በርስ በመፋጀት አይደለም።ከነርሱ ብዙ ልንማር በተገባ ነበር። ጉልበታችንና እውቀታችንን ለቀና ነገርና ለዕድገት ብናውለው ኖሮ ባለፉት 30 ዓመታት ውስጥ ማህበሩ የት በደረሰ ነበር። 30 ዓመት ሙሉ ያው ሽኩቻ እንጂ ዕድገት የለም። ይህ በቡድን እየተከፋፈሉ መሻኮት የኢትዮጵያውያን ማህበርን ብቻ ሣይሆን የሌሎችንም ማህበራዊ ተቋሞቻችንን ዕድገት የሚገታና አጥፊ ባህርይ ነው። ማህበረሰቡ ይህንን ባህርይ በጥብቅ መዋጋት አለበት። ይህን ችግር ባለፈው መንፈቃዊ ጉባኤ ላይ ገልጠን ካቀረብነው ወዲህ አብዛኛው የማህበሩ አባል ችግሩን በትክክል የተረዳው ይመስለኛል። ጉባኤው ችግሩን ስለተረዳ ችግሩን አጥንቶ የውሳኔ ሐሳብ የሚያቀርብ ኮሚቴ መርጦ ከሰየመ በኋላ የጥናቱ ውጤት ጁን 12 ቀን 2011 ዓ.ም. በነበረው ጉባኤ ላይ ሰፊ ውይይት ተካሂዶበታል። በመቀጠልም ጁላይ 17 ቀን 2011 ዓ.ም. በተደረገው ጠቅላላ ስብሰባ ላይ ሪፖርቱ ቀርቦ 60% የድጋፍ ድምፅ በማግኘት የቀረበው ሪፖርት ፀድቋል። በጠቅላላ ጉባኤው የፀደቀው ውሳኔም የሚለው ሌላ ቦርድ አባላት ተመርጠው እስኪሰየሙ ድረስ አሁን ያለው የቦርድ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ማህበሩን ሲመራ እንዲቆይና ሌሎች የቦርድ አባላት ግን በሙሉ እንዲሰናበቱ ነው። በዚህ ውሳኔ መሠረትም የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሥራውን በሰለም እያንቀሳቀሰ ይገኛል። የጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ ያልተዋጠላቸውና በቡድን መከፋፈል ላይ የሚያተኩር አንድ አንድ ግልሰቦች አሁንም ቢሆን ከውጭ ሆነው የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን በኢሜልና በተለያዩ መገናኛዎች ከመጎንተል አልታቀቡም። ይህን የመከፋፈል ባህርይ ችግር ማህበረሰቡ በጋራ በጥብቅ መዋጋት ያለበት ጉዳይ ነው። ራሳችንን ከሌሎች ማህበረሰቦች እኩል ወይም የበላይ ማድረስ የምንችለው አብሮና ተባብሮ በመሥራት ብቻ ነው። በመከፋፈልና በመነታረክ ያደጉ ማህበረሰቦች ገና አላየንም።

ሐዋርያ - የቀድሞውን ጽ/ቤት ለቃችሁ አሁን 1950 በዳንቮርዝ ጎዳና አዲስ ጽ/ቤት ተዛውራችኋል ምክንያቱን ቢነግሩን ?

ዶ/ር ሃይሌ - የኢትዮጵያውያን ማህበር ጽ/ቤት ድሮ ከነበረበት 2064 ዳንፎርዝ ጎዳና ወደ 1950 ዳንፎርዝ ጎዳና ተዛውሮአል። ይህም የተደረገበት ዋና ምክንያት የቀድሞው ጽ/ቤት ኪራይ በወር $16,000 ስለበረና ይህም ከማህበሩ የባጀት አቅም ጋር ተመጣጣኝ ስላልሆነ ነው። የአሁኑ ቢሮ በዚያው በዳንፎርዝ አካባቢ ሲሆን ኪራዩ በጣም ዝቅ ያለ (በወር $3,300 የሆነ) ለሚካሄዱትም ፕሮግራሞች በቂ የሆነ ሕንፃ ነው።

ሐዋርያ፡ በማህበሩ አስተዳደር ውስጥ የተነሱትን አለመግባባቶች አስመልክቶ በቅርቡ ሲካሄዱ ስለቆዩት አጠቃላይ የአባላት ስብሰባዎች በዛ ያሉ ትችቶች ይሰማሉ። እስቲ አጠር አርገው የችግሩን መንሳኤና የተደረሰበትን መፍትሄ ቢያስረዱን?

ዶ/ር ሃይሌ - በማህበሩ የቦርድ አስተዳደር ውስጥ

የታየው ችግር ድንገት ዛሬ የተፈጠረ አይደለም። ቀደም ሲል እንደገለፅኩት ከማህበሩ ጋር አብሮ የቆየ ችግር ነው። በአሁኑ ጊዜ መነጋገሪያ የሆነው ችግር ተሸፋፍኖ ስለኖረና ዛሬ በግልጽ ስላወጣነው ነው እንጂ አዲስ አይደለም። መሠረታዊ ችግሩ ከቡድናዊ የቦርድ አባላት አመራረጥ ጋር የተያያዘ ነው። እንደሚታወቀው በቦርድ ውስጥ ገብተው እንዲያገለግሉ መመረጥ የሚገባቸው ግለሰቦች ቡድናቸውን ወክለው ሳይሆን ባላቸው ዕውቀትና የሥራ ልምድ በቀና ልቦና አብሮ በመሥራት ማህበረሰቡን ለማገልገል ነው። ዕውነታው ግን ከዚህ የተለየ ነው። በቦርድ ውስጥ ገብተው እንዲያገለግሉ የሚመረጡት ሰዎች በቡድን ላይ የተመሠረተ በመሆኑ፤ ከአንድነት ይልቅ በልዩነት ላይ ማተኮር ከመደጋገፍ ይልቅ መሻኮት፣ ከመግንባት ይልቅ የማፍረስ ባህርይ ጎልቶ ይታያል። በዚህ ዓይነት አሠራር ዕድገት ማሰብ የማይቻል ነገር ነው። ይህ ለማህበሩ ከፍተኛ ችግርና ለዕድገት ዋና መሰናክል ለመሆኑ ባለፈው መንፈቃዊ ጉባኤ ቀርቦ ሰፊ ውይይት ተካሂዶበታል። የቡድን አሠራር ለዕድገት ፀር እንደሆነ ብዙ ተተችቶበታል። ነገር ግን ትችት ብቻ ሣይሆን ሁሉም ተባብሮ ማህበሩን ከቡድን አሠራር ማዕዳት አለበት። ይህ "ይዋል ይደር" የማይባል የጋራ ተግባራችን መሆኑን ሁላችንም ልንገነዘብ ይገባል።

ሐዋርያ - በየዓመቱ የሚከበረው የኢትዮጵያ ቀን (Sptember 10/2011)ዝግጅታችሁ ከወትሮው ዘግይቶ የተጀመረ ይመስል ነበር፤ እስኪ በዓሉን አስመልክቶ የሚነግሩን ብስራት ካለ? ከዚሁ በተያያዘ በዓሉን አስመልክቶ የቶሮንቶና አካባቢው ኢትዮጵያዊያን ትብብርና ተሳትፎ ምን ይመስል ነበር?

ዶ/ር ሃይሌ - በየዓመቱ የሚከበረው የኢትዮጵያውያን ቀን ዝግጅት በእርግጥ ዘንድሮ ከወትሮው በጣም ዘግይቶ ነው የተጀመረው። ይህም የሆነበት ምክንያት ማህበሩ በገጠሙት ከፍተኛ ውስብስብ የውስጥ ችግሮች ነው። የበአሉ ዝግጅት የተጀመረው በአሉ ሊደርስ 6 ሳምንታት ሲቀረው ነው። በዚህ አጭር ጊዜ ውሰት ማህበሩ ባሉት 4 ሰራተኞችና 4 የቦርድ ሥራ አስፈፃሚ አባላት ብቻ በዓሉን በተሟላ ሁኔታ ለማዘጋጀት እጅግ አዳጋች ነበር። ነገር ግን ብዙ የማህበራችን ወዳድ አባላት ራሳቸውን በኮሚቴ አዋቅረው ሌት ከቀን ባደረጉት ርብርብ በአሉ ከመቸውም በበለጠ ደምቆ ተከብሮአል። ከዚህ በተጨማሪ ይህ በዓል

በደመቀ ሁኔታ እንዲከበር ኢትዮጵያውያን የንግድ ድርጅት ባለቤቶች የጤና ባለሙያዎችና ሌሎች ግለሰቦች የገንዘብ ድጋፍ አድርገዋል። ይህም ድጋፍ የበአሉን ዝግጅት ከድሮው ለየት ያደርገዋል:: በበአል አዘጋጅ ኮሚቴው ውስጥ የተሰማሩት ግለሰቦች ያደረጉት የጉልበት የገንዘብና የጊዜ መስዋዕት እጅግ ከፍተኛ ነበር። ከዚህ ባሻገር በሥራው ላይ ያሳዩት የማህበር ፍቅር አንድነትና ቅንነት በጣም የሚያኮራና ሞራልን ከፍ የሚያደርግ ነው።

እነዚህ የማህበርና የአንድነት ፍቅር ያላቸው ሰዎች በአሉ በደመቀ ሁኔታ እንዲከበር ሲረባረቡ በአንፃሩ ደግሞ ህብረተሰቡ እንዲከፋፈል በሕብረተሰቡ መካከል ሰላምና እንድነት እንዳይኖር፤ በአሉ በሰላም እንዳይከበር፣ ከፍተኛ ትግል ያደረጉ ግለሰቦች (ቡድኖች) ነበሩ። እንዚህ ግለሰቦች እስከመጨረሻው ቀን ድረስ በአሉን ለማበላሸት ከፍተኛ ጥረት አድረገዋል።


ሐዋርያ - ዶክተር ሃይሌ ፋንታ፤ ስለሰጡን ሰፊ ግንዛቤ የሚያስጨብጥ ቃለ ምልልስ ከልብ እናመሰግናለን።


# መለስ ዜናይ የሚባል "ኢትጦጵያዊ"

## ሽሙጥ

ሚካኤል ሚስግና (ስዊደን)

ማልዶ ከረፋዱ ላይ ነው። ምንም ነገር የለም። ምንም....





አልጀዚራን የዜና አውታር ስጨርስ ወደ "ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢሕአፓ ራዲዮ ጣቢያ" በቀጥታ አመራሁ። አለ አይደል? በስርጭት ሽፋን እንደ "አሸን" ከፈሉ ሶሻል ኔትዎርኮች ውስጥ መካከል ሙያዊው ዕሴቱ ኖሩዋቸው ሚዛናዊ ዘገባን የሚያስደምጡ እንደመኖራቸው "ወደቀ" ሲባሉ "ተሠበረ" የሚሉ "ዜና" አይነት "ገድል" የሚዘግቡ፤ "ርእሰ አንቀጽ" በማለት ጀምረው "ማሳሰቢያ" አይሉት ""የሃተታ ጅራፋቸውን" የሚያወናጭፉ የስርጭት መስኮች በዲያስፖራ ላይ መቸም በገፍ መኖራቸው ስለሚታወቅ አልጀዚራና ፍኖተ ዴሞክራሲ፤ ቪኦኤና የጀርመን ድምጽን በሚዛናዊነት ዋቢ የሚጠቅሱ መቸም አይጠፉም። ቀጣዩ የስርጭት ጭብጥ ጉድጉዋድ ማነው? ቢባል "ነጻነት ለኢትዮጵያ" ሬዲዮ ነዋ..!

ጎበዝ..! አንድ ነገር አለ...! አንዳንድ የፍርፍርና የቁዋንጣ" የዝልዝልና የጥብስ አቅራቢ የሬስታውራንት ባለቤቶች ሲያሻቸው የቁርጥ ሥጋ ሜኖ ቸርቻሪዎች፣ ሲመቻቸው ደግሞ "ጋዜጠኞች" በመሆን ለወያኔ የፕሮፖጋንዳ አበጋዝነት ዘብ በመቆም ወያኔ ሥለሠራቸው ሠቀላ ቤቶች፣ ስለትራንስፎርሜሽኑ ዘመን ህዳሴ እየሰበኩ "በጣዕር" ላይ የሚገኘውን "ወያኔን" ለማዳን እየተሩዋሩዋጡ ስለሆነ እነዚህን "ጉልበተኛ ጋዜጠኞች" እንደ "ቅንድባሙ አዝማሪ" ገለል..! ማድረግ ያስፈልጋል የሚሉም በቁጥር አነስተኛ አይደሉም።

እንደ ግሪጎሪሳዊያኑ ቀመር በ1991 ዓ.ም ላይ "ሪሳላት አልጅሃድ" የተሰኘው የሊቢያ መጽሄት አንድ ታሪክ አውጥቶ ነበር አሉ። ዛሬ በህዝባዊ አመጽ የታወኩትና ምራባዊያን ላለፉት ሦስት አሥርት ዓመታት ያህል ባላቸው የወላዋይነት ባህርያቸው የማይታመኑ በመሆኑ "ኮሎኔል ቃዳፊ" ከማለት "ኮሎኔል ቀጣፊ.!" ማለቱ ይበጃል በማለት ሲዘባበቱባቸው የነበሩት ኮሎኔል ጋዳፊ በሊቢያ ጁሙህሪያ ሪፓፕሊክ ሸንጎ ላይ ተገኝተው "መለስ ዜናይ ኢትዮጵያዊ የመናዊ(ዐረቦች) ነበርን አጼ ሃይለ ሥላሴና ቀደምት ገዥዎች አስገድደው "ክርስቲያን" አደረጉን እንጅ ወትሮውኑ ሲፈጥረን በማለት ነግሮኛልና "የጠፉት ዐረቦቹ ኢትዮጵያዊያን" ወገኖቻችን ዛሬ ተገኙ ...! በማለት ለተሰበሰቡት ኢማሞችና ሼኮች ዲስኩር ሲያስደምጡ አደራሹ በጭብጨባ በሆታ አስተጋባ" በማለት ትናንትን ለዛሬ የሚቆዝሙ አጠንጣኖች ዛሬም አሉ። የቀድሞው የሴንትራል አፍሪካ ሥዩመ እግዚአብሄር "ዣን ቤዳል ቦካሣ" ወደ ትሪፑሊ አንድ ጊዜ አቅንተውና ለጋዳፊ እጅ ነስተው ሃይማኖታቸውን በመለወጥ "እስልምናን" እንደተቀበሉ አብሥረው ወደ ሀገራቸው ከተመለሱ በሁዋላ ሰባ ሁለት ሰዓት ባልሞል አጊዜ ውስጥ በዘጠና ዲግሪ ተገልብጠው "እስላም" እንዳልሆኑ በአዋጅ አስደንግገው "የጋዳፊን የእጅ መንሻ ዶላር ላፍ ..!" አድርገው ቀሩ በማለት የቀድሞው "የሎስ አንጀለስ ታይምስ" ሀተተኛ የነበረውና "ዚ-አፍሪካን" መጽሃፍ ደራሲ የነበረው "ዴቪድ ላምብ" በእማኝነት ያስቀመጠው ጉዳይ ነው""

"ብድር በምድር" አለ...! የሀገሬ ሰው..! ሰው የእጁን አያጣምና ትናንት ሻዕቢያንና ወያኔን በማስታጠቅ በሀገራችን ላይ እሳት ጭረው ቁጭ ብለው ሲሞቁ የነበሩት የሶሪያ፣ የሊቢያን አግብጽ ፈርዖኖች ዛሬ በገዛ ደጃፋቸው የተነሳው የሕዝብ ሱናሜ ቀያቸውን እያመሰው በመሆኑ "ጋዳፊ" ላይ የወረደው "ዝናም" ካፍያውን የመናዊ (ዐረቡ) መለስ ዜናይ ላይ መጣሉ አይቀርም" ሲሉ የሚያብጠለጥሉ አቃቂረኞች አይጠፉም።

ትናንት ባህረ ነጋሲን (ኤርትራን) ያስገነጠሉት የሀገሪቱን የባህር ክልል ለሻዕቢያ በመመረቅ "ሙልጫችን" ያስቀሩን፤ በሱማሊያ የድሃ አብራክ የሆነውን የመከላከያ ሠራዊታችን በማስጨረስ "የጅሃድ ቀለብ" ያደረጉት፤ በጋምቤላ፣ በኦጋዴን፣ በደቡብ ኢትዮጵያ ጅኖሳይድ (የዘር ፍጅት) የፈጸሙት "ቅንድባሙ መሪያችንን" ኢትዮጵያዊ ነው ..! መንገድ ሠርቱዋል፣ ወፍጮ ቤት ዘርግቱዋል፣ .. ዐባይን ደግሞ አሁን ሊገድብ ነው ..! እያሉ ከሀገር አልፎ በዲያስፖራ ላይ "ወናፍ የሚነፉ" ሻማ አብሪዎቻቸው ካይሮ ላይ በነውጡ ጊዜ "የሙባረክን" ዕድሜ ለማራዘም ሲንገታገቱ የነበሩ "ግመል ሾፋሪዎች" እና "ፈረሰኞች" ስላላዳኑት የወዲ ዜናይ አጋሰሶችም "መለስ ዜናይ የሚባለው ኢትዮጵያዊ መሪያቸውን ከፍጻሜው ጉድጉዋድ ሊያስጥሉት አይችሉም!" ሲሉ በአጽንኦት የሚያሰምሩ ክፍሎችም ይደመጣሉ።:

ባለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት ያህል ወያኔ/ኢህአዴግ በቆረጣ ስልቱዋ ሀገሪቱን ሊገነቡ የሚችሉ ሙህራንን ከሥር አበማባረር፤ በመግደልና ከሀገር ተሰድደው እንዲወጡ በማድረግ "የባህር ክልል" ብቻ ሳይሆን ሀገሪቱን "ሙህር አልባ" በማድረግ የፈጸመውን በደል ዋቢ በማድረግ በዘመን እደርግ "በዕድገት በህብረት ዘመቻ" ወቅት የተከሰተን አንድ ምጸት የሚያመሳክሩ ወገኖች አይጠፉም"":

በዕድገትና በህብረቱ ዘመቻ ወርቅት ታዲያ ወደ ጋምቤላ የዘመተ አንድ ተጫዋች ዶክተር ነበሩ አሉ። በጊዜው ከተማሪዎች ጋር አብረው የዘመቱ የህዝብ ድርጅት ጊዜያዊ ጽ/ቤት የአራት ወር "ለብ ለብ" ኮርስ እየተሰጣቸው የተላኩ ካድሬዎች ሙህራኑን ቀጭን ተዛዝ እየሰጡ ስላስቸገሩ እኒያው ተጫዋች ዶክተር አንዱን "ሳይሞቅ ፈላ" ወጣት ካድሬ በመጥራት "ስማ..! ኢትዮጵያ አንተን ለማግኘት አራት ወር፣ እኔን ደግሞ ሃያ አምስት ዓመት ይፈጅባታል..!" አሉት አሉ ...ቂ....!ቂ...!..ቂ!

በቅርቡ ወዲ ዜናይ በፓርላማው ተገኝተው "የሥራ ዝርዝር ሪፖርት" አይሉት "ማስፈራራት" ዲስኩር ቢጤ አውርደው ነበር አሉ። ሻዕቢያን አከርካሪውን እንደሚሰብሩ፣ ተቃዋሚዎችን "እምሽክ" እንደሚያደርጉ፣ ዐባይን" በቦንድ እንደሚገነቡ፣ አዋጅ በመደንገግ መሪ ቃል አስቀምጠው ነበር አሉ። የድሮ ንጉሦች ዐባይን ልንገድብ ነው እያሉ ያስፈራሩ እንደነበሩት በመሃል አገር የተነሳውን ቁጣ ለማለዘብና አቅጣጫ ለማስቀየር የተለመደ ወያኔያዊ የቆረጣ ስልት ነው የሚሉም አይጠፉም።

የሀገሪቱን ሰፋፊ ደናግል መሬቶችን በአደባባይ ለባዕዳን የቸበቸቡት፣ አሰብ ወደብ" የኤርትራ እንጅ "የኢትዮጵያ" አይደለም በማለት በዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ የተከራከሩትን "የትግሬ ታሊባን መሪን" ኢትዮጵያዊ ነው ...! የሚሉ ደቀመዛሙርቶችን በተመለከተ ትናንትን ለዛሬ በመቆዘም በደርግ ሥሪት ውስጥ የወረደን ምጸት የሚያሰሉ ወገኖች አሉ።

በቀድሞው የደርግ ሥርዓት "የየካቲት ስድሳ ስድት የፖለቲካ ተቁዋም" የነበረውን በአበጋዝነት ይመሩ የነበሩት አንድ የደርግ አባል ነበሩ አሉ። በጊዜው ሕዝቡ በየቀበሌው እየተሰበሰበ በግድ የማርክሲዝም ሌኒንዝም ሳይንስ ያጠና ነበር። እኒያው የደርግ ኢሠፓ የቦተሊካ ሳይንስ ሃላፊ የነበሩት ሹመኛ ታዲያ "ጉዋድ ሮቤርቶ ቺጋኖ" ይባሉ ነበር። ስማቸው ከተለመደው የሀበሻ መጠሪያ ለየት ያለ ስለነበር በዚሁ የሚታወቅ ነው።:

ታዲያ አንድ ጊዜ ጉዋድ "ሮቤርቶ ቺጋኖ" በአንድ የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ትምህርት መስጫ ጣቢያ እየተዘዋወሩ ሲጎበኙ በጨዋታ አዋቂነታቸው የሚያውቁዋቸውን አንድ ቄስ በጣቢያው ውስጥ "ሳይንሱን" ሲወስዱ ያገኙዋቸው ኖሮ ጉዋድ "ሮቤርቶ ቺጋኖ" ተገርመው እንዴ ..! አባቴ..! እርስዎ ደግሞ እዚህ ምን ያደርጋሉ..? እኔ መቸም የቄስ ማርክሲስት ሌኒኒስት አይቼም አላውቅ..! ይሉዋቸዋል። ፈጣን ምላሽ የሚቀናቸው መንፈሳዊ አባትም "እኔም ደግሞ "ሮቤርቶ ቺጋኖ" የሚባል ኢትዮጵያዊ ሰምቸም አላውቅ...!' አሉ እየተባለ ይቆዘማል። አለ አይደል...? ሮቤርቶ የሚባል ስም፣ መለስ ዜናይ የሚባል "ኢትዮጵያዊ መሪ ...!" ይህቺ ናት ጨዋታ..!

ጎይታይ መለስ መንገድ ሠርቱዋል፣ ወፍጮ ቤት ዘርግቱዋል፣ እያሉ በጣዕር ላይ የሚገኘውን ወያኔን ለማዳን እነ አባመላዎቹ ዲያስፖራው ላይ ቢያራግቡም አዶልፍ ሂትለር በጀርመን በኪነ-ህንጻው፣ በሳይንሱ፣ በከባድ ኢንዱስትሪው ግንባታ የላቀ አስተዋጾኦ ሲያደርጉ፤ እነ ሳዳም ሁሴን በኢራቅ የሚያማምሩ ቤተመቅደሶች፣ የጤና ጣቢያዎችና የመሠረተ ልማት አውታሮችን የገነቡ መሆናቸውን በማስላት በዐረብ ሀገሮች የተነሳው የአመጽ አውሎ ነፋስ ወደ ኢትዮጵያ ተነስቶ ሱናሜው ጎርፉን ሲያጥለቀልቅ ለኤርትራ ጥብቅና የቆሙ "መለስ" ዜናይ የሚባል ኢትዮጵያዊ ...!" እንደቀድሞው የደርግ ሸንጎ ፕረዚዳንት እንደ ኮሎኔል መንግሥቱ "ወርቅ ቢያነጥፉለት ፋንድያ ነው የሚል ሕዝብ" በማለት እንደማይራገሙ መቸም እምነታችን ነው..!" የሚሉ ሀቲተኞች ከቶ አይጠፉም።




Local(Canada) ………………. $35.00
USA ………………………….. $45.00
Others ……………………….. $65.00
Institution………………….. $100.00

To Place an ad, please call 416- 459-5964

or email us at: Hawarya.publications@sympatico.ca

# አዬ – ዓይጋ!

## ከ አያልነሽ

ከሁሉ በላይ በቅድሚያ አቶ ፅጌ ሀብተማርያም ከእስር የመፈታታቸውን ዜና ስሰማ የተሠማኝ ደስታ ልክ አልነበረውም። የደስታዬ ምንጭና መነሻ ደግሞ መጀመሪያውኑ እኚህ አባት መታሠር አይገባቸውም ከሚል ፅኑና ቋሚ ከሆነው እምነቴ በመነሳት ነው። ምን ይደረግ ዛሬ፣ ዛሬ እነዚህን መሰል አዛውንቶች እንዳይታሠሩና መከራን እንዳይገፉ ለማድረግ ይቻለን የነበረው ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ለታሰሩና ለተሰወሩ ዜጎቻችን ሁሉ እኩል ሁላችንም አልቅሠን፣ ጮኸን በነበረ ዛሬ የምናየውን መከራ አንደግመውም፣አናየውም ነበር። ያ አልሆነምና አሁን ሁላችንንም አንድ በአንድ እየነካ ስሜታችንንም መጉዳቱ አልቀረም። ዛሬ የእኚህን አባት መንገላታት ስምለከት በእውነቱ የሚሰማኝ ኃዘን ቀላል አይደለም – ልብንም ያደማል። ዳሩ ግን ይሄ እንዳይሆን ማድረግ ስንችል ያልተቻለን ለምንድን ነው …? ጥያቄው ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ይመለከታልና ወደኋላ ላይ በሠፊው ለማብራራት እሞክራለሁ።

ወያኔ እንደነገረን ከሆነ ለእኚህ አባት መታሠር ምክንያት በ2008 ዓ.ም ተሞከረ በተባለ (ኩዴታ) ሰበብ መሆኑ አይዘነጋም። ይህ ራሱ ተሞከረ የተባለው "ኩዴታ" ያልተጨበጠ ከመሆኑም በላይ ወያኔም ግርግሩን በጣም ሊጠቀምበት ሞክሯል። ከዚህ "ኩዴታ" ጋር በተያያዘም እስከአሁን ድረስ ታሥረው ገና ያልተፈቱ ዜጎች እንዳሉን ይታወቃል። የበደሉ በደል ደግሞ ቆርጦ ቀጥሉ ዓይጋ ያማረበት ይመስል፣ የኚህን አባት መፈታት አስመልክቶም እንዲህ ብሎ ሊያስነበብን መብቃቱ የምፀት ምፀት ነው። እጠቅሳለሁ፡

"አቶ ፅጌ ሀበተ ማርያም ከእሥር ሊፈቱ የቻሉት በዋናነት በሠሩት ወንጀል ተፀፅተው፣ ለይቅርታ ቦርድ አቤቱታቸውን በማቅረባቸው ነው" ይልና ኃፍረት የለሹ ዓይጋ ከ80 ዓመት በላይ የሆኑ ሽማግሌን በማንገላታት-ግዳይ የጣለ ይመስል፣ እንዲህ እያለም ሲዘባርቅ ይታያል። "የይቅርታ ቦርዱ…" ይላል ዓይጋ፥ "የይቅርታ ቦርዱ ግለሰቡ በዕድሜ የገፉና በህመም የሚሠቃዩ በመሆናቸው፣ የበደሉትንም ህዝብ ለመካስ ቃል በመግባታቸው፣ እንዲሁም በማረሚያ ቤቱ የነበራቸውን ሥነ ምግባር በማጤንም ይቅርታ እንዲደረግላቸው ለኢፌዲሪ ፕሬዝዳንት ሃሳቡን አቅርቧል"

ይላል የዓይጋ አሳፋሪ ዘገባ። በመሠረቱ እነዓይጋ እና ለገሠ ዜናዊ ይህን ዓይነት አሳፋሪ ድርጊት እንደ ጀብዱ ቆጥረው ማቅራራታቸው፣ ሁሌም ባዶ ሠብዕናቸውን ለመደበቅ ያስችላቸው ዘንድ ነውና አያስደንቅም። "ዘባራቂ ይወዳል መራቂ" እንደሚባለው ሁሉ ዓይጋም ከላይ ያስቀመጠውን ዘገባ ዘባርቆ እንጀራውን ማብሰል ስለአለበት መናኛ ነገሮችን ሁሉ ጠቅጥቆ አለቃውን ማወደስ ግዴታ ተጥሎበታል – እንደ ቦንዱ ታሪክ ማለት ነው። በባዶ ሠብዕና ላይ የቆሙና የሚጥመነመኑ ሰዎች ችግር፣ ነውርን አለማወቃቸው ነው። ሥነ ምግባር፣ ሥነ ደንብ ወይም ሥነ-ሥርዓት የተባሉ እሴቶችን በሙሉ፣ ሁሌም ተፃረው ግብግብ ሲገጥሟቸው ይስተዋላሉ። ትንንሽ ጭንቅላቶች የሚያሳዝኑት ለእንደዚህ ዓይነቱ ምች፣ በቀላሉ የተጋለጡና የተመቹ መሆናቸው ነው።



አያልነሽ

የዜናዊ አገዛዛ ዕድፍና ጉድፍ የበዛባት አገዛዝ ነው። ይህ ብቻ አይደለም – የዚህን ጥርቅም አገዛዝ ገመና ከፍተን ብናየው በሰው ማኃል ቆሞ የሚያስኬድ አይደለም። ዕድገታቸውና ታሪካቸውም ቢጤን ደግሞ ቀና የማያስብልና የማይወላዱበት ነውና ውርደታቸውን – ጌጥ፣ ውድቀታቸውንም – አምሃ ብለው መስበክ የማንነታቸው መደበቂያ አድርገው ይጠቀሙበታል። እነኚህ ሰዎች እነዚህን ለመሠሉ ክቡር ለሆኑ እሴቶች አፅቅ ያህል ቦታ አይሰጡም። ለዚህ ነው የአገሬ ሰው ባለጌን ካሳደገ – ያነቀው ፀደቀ ይልና ለነውር እና ለነውረኞች ፊት የሚነሳቸው። ወጣ ወረደም፣ የአቶ ፅጌ ሃብተማርያም መፈታት በእውነቱ ከሁሉም በላይ አስደሳችና ለወዳጅ ዘመድ ሆነ ለመላው ቤተሰብ በሙሉ፣ እንኳን ደስ አላችሁ ስል ከልብ ነው። ግን ይህ ጉዳይ በዚህ ያቆማልን…..? አሁንስ ቢሆን በእሳቸው እግር "በሽብርተኝነት" ስም ስንቶች ወደ ዝብጥያ አልትወረወሩም…? ወያኔስ ይሄንን መሳይ አጋጣሚ እንዴት ይጠቀምበታል…? እንዴትስ ሲጠቀምበት ቆየ… ? እኛስ ፀረ ወያኔ ነን የምንለው "ታጋዮች" እንዴት አስተናገድነው…? እንዴትስ ተጓዝንበት …? ብለን አንድ በአንድ አካሄዳችንን ብንፍተሽና ራሳችንንም ብንገመግም ሕፀፃችንን ቅልብጭ አድርገን ማዬት ይቻለናልና ነው። በሽታችንንም አውቀን ከመድኃኒቱ ጋር እናገናኘዋለን - "በሽታውን የደበቀ መድኃኒት አይገኝለትም" ይባላል የለ።

የተከብራችሁ አንባቢዎች ! ወያኔ እስካሁን ድረስ እየገዛ (ነፍሱን በቀጭን ክር አንጠልጥሎ የያዝት እንበል) እንደ እውነቱ ከሆነ አንዳንድ አዘናጊዎች እንደሚሉን በጥንካሬው ሳይሆን፣ ፍርኃቱ በሚወልደው ጭንቀቱ አስገዳጅነት መሆኑን ለማወቅ ጠንቋይ መቀለብ ወይም ከአገዛዙ ጋር መሥራትን ግድ አይለንም። ይህ አንድ ሐቅ ነው። እንደእኔ እንደእኔ ወያኔ በእውነቱ ደካማ ነው። በነገራችን ላይ ከእንስሳት ሁሉ የመጨረሻ ፈሪ ዝንጀሮ እንደሆን ታውቃላችሁ…? የወያኔ ድፍረትም የዝንጀሮ ዓይነት መሆኑን፣ የሚያውቁት ያውቁታል - ግን አልተፈተነም።

ይህችን ወያኔ ነፍሱን ያንጠለጠለባትን ቀጭን ክር በጥሰን እንዳንጥል ደግሞ ከፊታችን እየመጡ የሚደነቀሩ እንቅፋቶች አልታጡም። በእውነቱ ችግራችን ሁሉ ወያኔ ብቻ ነው ማለት አይቻለም፣ አይደለምም። ለእኔ ወያኔ ችግር ሳይሆን <u>ጠላት</u> ነው። ችግርማ የቤት ልጅ ነው። በየትኛውም ሕብረተሰብ ውስጥ ችግርና ሃሳብ ምንግዜም የሚኖሩ ናቸው፣ አይጠፉም። ወያኔ ግን ከችግራችንና ከችግር በላይ ነው። ይህ ሃቅ ሆኖ ሳለ ታዲያ፣ እንደ መዥገር የተጣበቀውን ጠላት ማርከሻውን እንዴት አጣንልት ብለን ከጠየቅን፣ ሁላችንም በየጓዳችን የምናገኘው መልስ፣ ማርከሻውን ደብቀን አብዛኛዎቻችን በባዶውና ለታይታ ብቻ የምንጮህ በመሆናችን ነው። እስቲ ከብዙ ችግሮቻችን ውስጥ ዋና ዋናዎችን በጥቂቱ ለማሳየትና ለመዳሠሥ ልሞክር።

ወያኔ ኢትዮጵያን እያተራመሠ በሥልጣን ለመቆየት አገዛዙን ሲተክል፣ ከቀን አንድ ጀምሮ አገዛዙን ያደላደለው በዜጎቻችን ህይወት ላይ እየተራመመደ ለመሆኑ ለሁላችን የተሰወረ አይደለም። ማሰር ብቻ ሳይሆን የዜጎቻችንን ህይወትንም እየቀጠፈና እየሠወረ እስከአሁኗ ደቂቃ ድረስ ሊቀጥል እንደቻለ አሌ ማለት አይቻልም። እነ ተስፋዬ ታደሰን ያስታውሷል። ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ በወያኔ ታሥረው ደብዛቸው የጠፋው የኢሕአፓ አባላት በሙሉ፣ ዛሬም ድረስ ወያኔን ተቃዋሚ ነን በሚሉት ኃይሎቻችን ሁሉ <u>የት ደረሱ</u>?፣ ተብሎ የማይጠየቅና የማይደፈር ተራራ ሆኗል። ግን ነፃነትን ደግሞ እንፈልጋለን። በመሠረቱ የእነኚህን የት እንደደረሱ ያልታወቁ ዜጎቻችንን መዳረሻ መጠየቅ ማለት፣ አዕምሮውን ገልጦ ለሚያስብ ህሊና፣ ቢያንስ የፍትህን ሚዛን ፈልጎ ለማግኘት የመጀመሪያውን እርምጃ ተራመደ ማለት ነው። ተከታዩ ደግሞ ፍትህን በእጅ ለማስገባት ሩጫ ላይ መሆኑን ማሳያ ነው።

በጣም የሚያሳዝነው ግን ከ1997 ዓ.ም ምርጫ በኋላ እንኳን፣ የተቃዋሚ ድርጅት መሪዎች ነን ብለው እንድንቀበላቸው ብዙ ያስገደዱንና የተፍጨረጨሩ "ታጋዮቻችን" ሁሉ፣ ዛሬም ድረስ የእነ ፀጋዬንና የበርካታዎችን የኢሕአፓ አባላት እስረኞች የት ደረሱ ብለው፣ ደፍረው ሊጠይቁ አልተቻላቸውም። ይሄ በጣም አሳዝኝ እና እንደዜጋም የሚያሳፍረን ሊሆን ይገባል። እንደሚመስለኝ ለእነዚህ "ታጋዮቻችን" የኢሕአፓ እስረኞች ማለት ያውም (ለእያንዳንዱ ዜጋ መብት መከበር ሲታገሉ በወያኔ እጅ የወደቁትን) ሁሉ ኢትዮጵያዊ አይደሉም፣ ዜጋም አይደሉም ማለት ነው። ይሄ ታዲያ እንዴት አያሳፍረም…? ወያኔ ስለእነ ደብተራው አስሮ አልናገር ማለቱ እየገረመን ባለበት ሁኔታ፣ በዚህ በኩል ደግሞ የእኛ የምንላቸው ሰዎች 20 ዓመት ሙሉ እነ ደብተራው የት ደረሱ ብሎ ለመጠየቅ አፋቸው ሲሸበብ ምን ሊባል ይችላል ወገኖቼ …?

አሁን፣ አሁንማ እስርን ራሱን ልብስ እንድናደርገው ከለገሠ ዜናዊ ባልተናነስ ሁኔታ፣ ጅዋጅዌ የሚጫወቱበት ሰዎች በርካታ ናቸው። የሠብዓዊ መብት ተሟጋች ወይም (human rights activist) ነን የሚሉን፣ ነገር ግን ግብራቸው ከስሙ ጋር የማይገጥም አያሌ ግለሰቦች፣ እዚህ በምንኖርበት ባዕድ አገር ውስጥ እንዳሽን ፈልተዋል -ይህ የሚያስገረም አይደለም። የአንዱ ሞት ለሌላው ክብረት እንደሚባለው መሆኑ ነው። እነርሱም ቢሆኑ ታዲያ የኢሕአፓ እስረኞችን ሰም ማንሳት ቀርቶ "አስተባበርነው" በሚሉት ሠልፍ ሁሉ ሳይቀር፣ የእነ ደብተራውን ፎቶ መያዝ እየተቸገሩ ስናይ፣ ምንኛ የሕዝባችንና የኃገራችን እጣ ፋንታ በድቅድቅ ጨለማ ውሰጥ እየተንፏቀቀ እንደሚቆይ እናስብና ኃዘናችን ልክ ያጣል። ሌላም አለ - እነኝሁ ሰዎች ወያኔ በዘር ከፋፈላን እያሉ ሲያላቃቅሱ እናይና መልሠው ግን እነርሱ ደግሞ በወያኔ ሰለባ የሆኑ የጋራ እስረኞቻችንን በድርጅት አጥር ከልለው የእከሌ፣የእከሊት በማለት በየፊናችን በር ዘግተን እንድናለቅስና እንድንላቀስ ሲያደርጉን መመለከት አጀብ የሚያሰኝ ነው_በጣም አሳዛኝ!።

ኢትዮጵያ ውስጥ ኢትዮጵያዊያን በዜግነታቸው እንዳይኖሩ ወያኔ የሚያደርስባቸው ጫናና እንግልት ሳያንሰን፣ እዚህ ደግሞ በሠብዓዊ መብት ወይም (human rights activist ነት)ስም ራሳቸውን የሾሙ ግለሰቦች፡ የጋራ እስረኞቻችንን በመከፋፈል ለወያኔ ሰለባ እንዲሆኑ ማድረግ ፈፅሞ ኃላፊነት የጎደለውና፣ አደገኛ አካሄድ በመሆኑ በግልፅ ሊነገራቸውና አቁሙ ሊባሉ ይገባል እላለሁ። በሰው ነፍስ መቀልድ መቆም መቻል አለበት።


80 ሚሊዮን ህዝብ ዛሬ በኢትዮጵያችን በግርግም ውስጥ እየኖረ እንዳለ ከማንም የተሠወረ አይደለም። የሆኖ ሆኖ ለዜጎቻችን መታሰር፣ በድብቅ መሠወር፣ መገደል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ፣ አውቀውም ሆነ ሳያውቁ ወያኔን በሚጠቅም መንገድ የሚራመዱ፣ ኃይሎች አሉ። ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ዜጎች በድበቅ በወያኔ እየታደኑ ሲሰወሩ መቆየታቸው እንዳለ ሆኖ፣ በተለይ ደግሞ ከምርጫ 97 በኋላ እንደ አዲስ አገርሽቶ፣ በግልፅና በአደባባይ ብዙ እስረኞችን ኢትዮጵያችን አስተናግዳለች። እንደዚያም ሆኖ ግን ብዙዎች ስማቸው የማይጠራ፣ የማይነገርላቸው፣ ለሽልማት የማይታጩ ወይም ያልታጩ ይሁኑ እንጅ በወያኔ እስር ቤት ግን መራራውን ፍዳ እየተቀበሉ ናቸው።

እውነታው ይሄ ሆኖ እያለ፣ ብዙ ዜጎቻችንም በኢትዮጵያ እስር ቤቶች በር ተዘግቶባቸው የፍትህ ያለህ በሚሉበት እውነታ ፣ በጣም በሚያሳዝን መልኩ "መቶ (100) እስረኞች" ብቻ ነው ያሉት ተብሎ፣ ሲነገርም አዳምጠናል። በዚህም ሳቢያ ነፈሰ ገዳዩን ወያኔ ትንፋሽ እንዲያገኝ ረድተነዋል።

ጨካኙ መለስ ደግሞ ይሄንን አጋጣሚ ይወደዋልና ዜጎችን ለማሰርና፣ ለመሰወር በገፍ ይጠቀምበታል -ተጠቅሞበታልም። ይህ ብቻ አይደለም። የእነኝህን (Activist) ነን ባዮችን ልክ ያውቃልና፣ ትኩሳታቸውን ለመለካት ወይም ለማስጮህ ሲፈልግ ደግሞ በጥቃቅን ነገሮች እያስታከከ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ባሰኘው ጊዜ ዜጎችን ስም ለጥፎ ያስራል - ባሰኘው ጊዜ ደግሞ ፈርማችሁ ውጡ ብሎ በዜጎቻችን ሕይወት ላይ ገበጣ ይጫውታል፣ ይሳለቃል። ይህ አሳዛኙ ገፅታ ነው። ዊኪሊክስ በዚህ ጉዳይ ላይ ዝረዝር ዘገባ ይዞ ወጥቷል፤ አስገራሚ የሆነውን ግን ቀንጭቤ ለማሳየት እሞክራለሁ። እንዲህ ይላል፥

"በአሜሪካ የሚገኙ አክራሪ የቅንጅት ደጋፊዎች ለአሜሪካ አምባሳደ ከሚያደርሱት ስደብ አዘል የስልክ ንግግሮችና የኢ-ሜይል መልዕክቶች መረዳት የሚቻለው፣ አሜሪካ የሚገኙ የቅንጅት <አክራሪዎች> የእስረኞች በእስር የመቆየት ሁኔታ ጠ/ሚንስትሩን ለማጥቃት የተሻለ መንገድ እንደሆነ የሚያስቡ ናቸው - ምክንያቱም ለእነርሱ የእስረኞቹ መፈታት የኢትዮጵያን መንግሥት የሚቃወሙበትን ሌላ መንገድ እንዲፈልጉ ያደርጋቸዋልና። "… ይላል የዊኪሊክስ መረጃ!።

ዊኪሊክስ ይሄን በተመለከተ ዘገባው ሰፊ ነው። እኔም የዊኪሊክስን መረጃ የሚያጠናክር አንድ ተጨባጭ ነገር ልጨምር። አንድ ሰሞን በካናድ እኖራለሁ የሚል አንድ ግለሰብ፣ ራሱን ለመደርከ ወይም ለእይታ ለመሸጥ ሲል "ብርቱካንን አሁን ዜናዊ መፍታቱ" የምንታገልበትን ወይም የምንጮህበት አጀንዳ ያሳጣናል እና በእኔ በኩል አሁን መፈታቷ አልተመኘም ሲል፣ አሳፋሪ ፅሁፍ በደረ-ገፆች ለቀ አስነብቦናል።

ግን በዚህ አሳዛኝ ገፅታ መኃል የዜጎቻችን ህይወት ያላግባብ ሁሉ ይቀጠፋል። ደግምም ስማቸው የማይጠራ፣ የማይሰተጋባላቸው። ሌላም አለ። በ1997 ምርጫ ወቅት ያኔ አዲስ አበባ በፈረንሳይ ለጋሲዮን አካባቢ "ድምፃችን ይከበር፥ ሰዎቻችንን አሳልፈን አንሰጥም" ብለው እሳት ከሚተፋ ጠመንጃ ጋር ተጋፍጠው ስለተገደሉት 5 ወጣት ጀግኖች፣ እስከ ዛሬ ማንም ሰው ስማቸውን አንስቶ የሚፅፍ ወይም የፃፈ አልታዬም። 8 ዓመት ሙሉ - ከ1997-2004 ዓ.ም -አይገርምም!

በአንፃሩ ግን በእነርሱ ሞት ዝናን ያገኙና "አንቱ" የተባሉ ሰዎች በባዕድ አገር በሽ ናቸው። ለ15 ዓመት ያህል የት እንደነበሩ የማይታውቁ ግለሰቦች ሳይቀር፣ ወደ አደባባይ ብቅ፣ብቅ ብለው ከእነዚያ ጀገኖች በላይ በየድረ-ገፁ እና አዲስ አበባም ብልጭ ድርግም በሚሉ ጋዜጦች ሁሉ ሳይቀር ፎቷቸውን ያስለጥፋሉ፣ ይለጥፋሉ ጉድ ነው። ይህ ብቻ አይደለም፤ በ"ሽልማት" እየታጀቡም ታሪክ የሠሩ ጀግኖች በመባል 8 ዓመት ተወድሠዋል፤ መፅሀፍ ፃፍን እያሉም ብዙ ገንዘብ ከተዋል። ይህም አሳፋሪ ታሪካችን ነው።

እነኝህ 5 ወጣቶች ሕይወታቸውን ለእኛ ቤዛ ሲያደርጉ መልዕክታቸው በጣም ግልፅ ነው። ምኞታቸውና ፍላጎታቸው ደግሞ በወያኔ መቃብር ላይ ፍትኃዊ የሆነ የሕግ ተቋም ለመገንባትና፣ የኢትዮጵያ ሕዝብም በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ይተዳደር ዘንድ ካላቸው ምኞት እንደሆን ጀግንነታቸው ይመሠክርልናል። ይህንን ደግሞ በአፋቸው ሳይሆን በተግባር - እደግመዋለሁ፣ በአፋቸው ሳይሆን በተግባር - ከመረጧቸው ሰዎች በፊት ግንባር ቀደም ሆነው ውድ ሕይወት በመክፈል ጀግንነትን አሳተምረውናል። እነዚህ ወጣቶች እንደዚያኛው እንዳለፈው ትውልድ ጀግኖች፣ ጀግነው ያጀገኑን ዕንቁዎቻችን ናቸው። የኢትዮጵያ ጀግኖች ናቸውና ሁሌም በእያንዳንዳችን ልብ ውስጥ እንደ ወርቅ ነድ ብርሃን የሚሰጡንና የሚያላብሱን ፀጋዎቻችን ናቸው።

ሌላም እውነት ልጨመር። በዚሁ በ1997 ምርጫ ወቅት በዚያው ዕለት በአፍላው፣ አዲስ አበባ አሁንም የወላጆቻችን ድምጽ ይከበር ብለው በወጡ ወጣቶች ላይ የወያኔ አገዛዝ ባዘነበው ጥይት ከተገደሉት ውስጥ የመጀመሪያዋ ጀግና፣ ሽብሬ ደሳለኝ መሆኑዋ አይዘነጋም። ሽብሬ ከቤቱዋ እንደወጣች ሳትመለስ በአሰቃቂ ሁኔታ በአጋዚ ጥይት ተደብድባ ህይወቷ እንዳለፈ በማግስቱ፣ እዚሁ በምንኖርበት ባዕድ አገር ውስጥ የዚህችን ወጣት ልጅ ፎቶ ግራፍ በድረ-ገፆቻቸው ላይ ለጥፈው በስሟ ገንዘብ የሰበሰቡና ወደ ኪሳቸው የከተቱ "የዚያን ጊዜ ታጋዮች" ብዙ እንደነበሩ ዛሬ እየሰማን ነው:: የገበያ ግርግር እንዲሉ አንዳንዶችም አሜሪካ ውስጥ በዚያን ወቅት ገንዘብ በመቦጨቅ የግላቸውን ራዲዮ ከፍተው ዛሬ መተዳደሪያቸው ያደረጉ፣ ግለሰቦች የሚያዙበት፣ የሚናገሩበት፣ የሚወደሱበትና "አንቱ" የተባሉበት ሁኔታ እንዳለ እንመልከታለን - ራዲዮ በኪስ እስኪመሰል።

እነ ሽብሬም በእውነቱ ለዚህ አልነበረም ሕይወታቸውን ቤዛ ያደረጉት። የእነ ሽብሬ ዋና ጥያቄ "የሕዝባችን ድምፅ ይከበር" የሚለው ሆኖ ሳለ ያን የእነርሱን ድምፅ ደፍቀነና አውርደን በ"መሪዎቻችን ይፈቱ" በሚል እንዲተካ የተደረገው ሆን ተብሎ በዕቅድ ለመሆኑ ዋቤ ማቅረብ አያሻም። ይህ ሲባል ግን አሁንም ቢሆን መሪም ሆነ ተራ ፣ማንም ዜጋ (አላግባብ የታሰረ ሰው) ን እንዲፈታ መጮህ የለብንም ማለት አይደለም። ቁም ነገሩ ይህ አቅጣጫን የማሳትና ከሃዲዱ እንዲወጣ የማድረግ ተግባር የወያኔ ብቻ ነው ለማለት ግን ያስቸግራል።

የሡብዓዊ መብት ተሟጋች (human rights activist) ስሙ ብቻ ራሱ እጅግ ያማልላል። እንደስሙ ሁሉ ተግባሩና ግዝፈቱም የዚያኑ ያህል ከባድ ነው። ይህ ከሆነ ዘንዳ በባዕድ አገር ያለው ኢትዮጵያዊ በሙሉ ታዲያ በዚህ ተቋም ሥር ተሠልፎ ተገቢ ሚና ቢጫወት በእውነቱ ከማንም በላይ ተጠቃሚው ራሱ ሆኖ ሳለ ለምን ብዙኃኑ ኢትዮጵያዊ ሊሸሸው ፈለገ...? ችግሩ ምን ይሆን.?

ነገሩ እንዲህ ነው ። የሠብዓዊ መብት ንቁ ተሳታፊ ወይም human rights activist ነን ብለው የቆሙ ኢትዮጵያዊ ወገኖቻችን፣ ለዚህ ለሚሉት ለሠብዓዊ መብት መረገጥ እንታገላለን ሲሉ መተከላቸው/principle አድርገው የሚራመዱበት መንገድ፣ ፍፁም የተሳሳተ መሆኑ ነው። ይኸውም "የእኛ ወይም ምርጥ ሰዎችቻን" የሚሏቸውን ብቻ መሠረት አድርገው ለመንቀሳቀሳ መፈለጋቸውና ማቀዳቸው ነው ዋና ህፀፁ። ግን የዓለም ዓቀፍ ሠብዓዊ መብት ድንጋጌ ደግሞ ይሄንን መሠል "ምርጥ ሰዎች" የሚል ሐረግ በማከል ሰዎችን መለየት (ኢ-ሠብዓዊ አመለካከት)ነው ብሎ አምርሮ ያወግዛል፣

ሠብዓዊ መብት(human rights) እና የአካባቢ የአየር ብክለት (environmental polition) ማለት ድንበር የማያግዳቸው ወይም የማይከልላቸው የሰው ልጆች የአስተሳሰብ ውጤቶች ናቸው። በአንፃሩም እነኝህ ሁለት መሠረታዊና ጥልቅ የሆኑ የሰው ልጅ እሳቤዎች በማንኛውም ሰው ሆን ተብለው ከተገደፉ ማለትም ከተዳጡ፣ ማንኛውም ሰው ለሠብዓዊ መብት እታገላለሁ የሚለውን እሳቤ ወይም የሰውን ልጅ ሰብዓዊነት ተፃረር ማለት ነው። ሰዎች እነኝህን መሠረታው ጉዳዮች እያወቁ ግን አስበው ከእነዚህ መሠረታዊ የሆኑ ፅንሰ -ኃሳብ ሲያፈነገጡና ሲወጡ፣ የሚሠሯቸውና የሚያደርጓቸው እንቅስቃሴያቸው በሙሉ ወርቅ መሳይ አርቲፊሻል መሆናቸው ሳይውል ሳያደር የአደባባይ ምስጢር ይሆናል ማለት ነው።

አንድ ሰው ሠብዓዊ ለሆኑ መብቶች ለመታገል ሲነሳ፣ በሕሊናው የሚጠየቀው ሁለት መሠረታዊ ነገሮችን ብቻ ነው - ፈቃደኝነቱና በተፈጥሮው ለሰው ልጅ ሥስ ልብ ያለው ወይም ያላት መሆኑ/መሆኗ ብቻ በቂ ነው። የእያንዳንዱ ሰው ሕሊና እነኝህን ሁለት ነገሮች ይዞ ባልተነሳበት ሁኔታ፣ ተግባሩ ሁሉ የአፍ ላይ ነፋስ ይሆንና ይህንንም ክቡር ተግባር ማለትም ለሰው ልጅ ሠብዓዊ መብት መታገልን፣ ሰው ሁሉ እንዲጠላው ያደርጋል ማለት ነው፤ ይሄ ታዲያ ወንጀል አይሆንም...? የአየር ብክለትም እንደዚያው ነው። የአንድ አካባቢ የአየር ብክለት የዓለምን የአየር ሁኔታና ደህነነት ይነካል የሚባለውም ለዚህ ነው። በዚሁ ዓይን በተመሳሳይ ሁኔታ ደግሞ በአንድ አካባቢ የሠብዓዊ መብት መጣስ -በየትም ሌላ አካቢቢ ሠብዓዊ መብት መጣስና መረገጥ ነው የሚለውን መርህ አፅኖዖት ሰጥቶ የሚራመደው SOCEPP፣ ቀዳሚ መፈክሩ አድርጎ የያዘውና የሚያስተጋባውም ለዚህ ነው።"Injustice Anywhere is Injustice Everywhere" ሲል ክቡር ዋጋ ለመሥጠት ፈልጎ ይመስለኛል።

ይህ የ SOCEPP አቋም የአፍና የማስመሰል ቢሆን ኖሮ፣ 16 ዓመት ሙሉ ራሱን ችሎ SOCEPP ህልውናውን ጠብቆ መቆየት ባላስቻለው ነበር። በነገራችን ላይ SOCEPP የተቋቋመው ከዛሬ 16 ዓመት በፊት ሲሆን፣ ዓላማውም ኢትዮጵያ ውስጥ የተረሱና በእሥር የሚማቅቁ ዜጋዎችን መታደግ የመሠረት ድንጋይ አድርጎ ሲሆን፣ ቀለሙ ደግሞ ኢትዮጵያዊ የሆነ ተቋም ነው። ከ1986 ዓ.ም(የኢት.አቆጣ.) ጀምሮ ከሰሜን እስከ ደብብ ከምሰራቅ እስከ ምእራብ ዘር፣ሃይማኖት፣ ፆታን ሳይለይ በፀረ-ኢትዮጵያው አገዛዝ (ወያኔ) ሰለባ ለሆኑ ኢትዮጵያኖች በሙሉ ለሁሉም በእኩል ሲያነባ፣ ሲጮህና ሲያስተጋባ የቆዬ ተቋም ነው። አሁንም ይሄንኑ እያደረገ ይገኛል። ለሠብዓዊ መብት እታገላለሁ የሚል ኢትዮጵያዊ ሁሉ የSOCEPP ን ዓርአያ መከተል ይኖርበታል፤ ቢያንስ ቢያንስ ከሕዝብ ታአማኒነትን ለማግኘት SOCEPP ዓርአያነቱ አንድና ሁለት አይባልም። ጨረስኩ።

የሕዝብ ትግል ያሸንፋል! የታሠሩ የፖለቲካ እስረኞ በሙሉ ይፈቱ!
ኢትዮጵያ ለዘላዓለም ትኖር!

ቸር ይግጠመን
October 4/2012

# ኤች አይ ቪ ኤድስ አልኮልና አደንዛዥ እፆች

(ክፍል 2)

በዳዊት የማታው ወርቁ
የኢትዮጵያውያን ማሕበር በቶሮንቶ እና አካባቢው
የኤች አይቪ ኤድስ መከላከያ እና ትምህርት ፕሮግራም
(የበጎ ፈቃድ ሰራተኛ)

አደንዛዥ እፆችና ኤች አይ ቪ

ስለ አልኮል ያነሳናቸው አእምሮን በመለወጥ ለኤች አይ ቪ እንድንጋለጥ የማድረግ ባህሪያት አደንዛዥ እፆች ላይም ይታያሉ:: በመሆኑም ዋና ዋናዎቹ የአደንዛዥ እፆች እነማን ናቸው? በሶወች ላይ የሚያደርሷቸው ጉዳቶች የትኞቹ ናቸው::

1. የህመም ማስታገሻዎች (Depressant or tranquilizers)

እነዚህ የህመም ማስታገሻዎች ለአግባቡ በጥቅም ላይ ከዋሉ በህክምና ስራ ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ:
: በተጨማሪም የህመምተኛ ስቃይ ይቀንሳሉ:: ይሁንና ለመልካም ስራ የተዘጋጁት መድሃኒቶች ሀኪሞችን ጨምሮ ለተለያዩ የህብረተሰቡ ክፍል ውስጥ ባሉ ሰዎች አግባብነት ለሌላው ጥቅም ሲወስዱ ይታያል::ችግሩ በጣም አሳሳቢ የሚያደርገው የመድሐኒቶቹ በአግባቡ አለመወሰድ ብቻ ሳይሆን የሚጠቀሙዋቸው ሰዎች በደም መልስ የደም ስሮች(veins)በመርፌ የሚወስዷቸው ስለሆነ መርፌዎቹ በኤች አይ ቪ የተበከሉ ሊሆኑ ስለሚችሉ ነው::

2. ናርኮቲክስ (ኦፒዮትስ)

እነዚህ አደንዛዥ እፆች በሃኪም ትእዛዝ የሚሰጡትን መድሃኒቶች (ሞርፊን) ወይም የሳል ማስታገሻ መድሃኒቶች(ኮዲን) ወይም የህክምና ጥቅም የሌለወን ሄሮይን የተለባለወን አደንዛዥ እፅ ያጠቃልላሉ:
: ከላይ እንደተመለከትናቸው አደንዛዥ እፆች እነዚህም በመርፌ ሊወሰዱ ስለሚችሉ ኤች አይ ቪ ያስተላልፋሉ::

3. ኮኬንና አነቃቂዎች (cocaine and stimulants)

እነዚህ አደንዛዥ እፆች ኮኬንና ካፊን (ሻይ እና ቡና) ወይም ጫትን ያጠቃልላሉ:
: ቅፅበታዊ የሆነ ከፍተኛ የደስታ ስሜትን መፍጠር፣ድፍረትን መቀነስ፣የእንቅልፍ ስሜትን ማጥፋት፣ የምግብ ፍላጎትን መቀነስ ወይም ከፍተኛ የሆነ የወሲብ ስሜትን በመፍጠር ይታወቀሉ::በመሆኑም እነዚህን አደንዛዥ እፆች የሚጠቀሙ ሰዎች በሁለት መልኩ ለኤች.አይ.ቪ. ሊጋለጡ ይችላሉ::

ሀ. እንደ ኮኬይን ያሉትን እፆች በመርፌ የሚወስዱ ከሆነ በመርፌ ንክኪ ምክንያት

ለ. እፆች ከፍተኛ የወሲብ ፍላጎትን ስለምፈጥር ኤች.አይ.ቪ. መኖሩንም ሊያስረሱ ስለሚችሉ ነው

4. ካናቢስ (ማሪዋና)

ካናቢስ ወይም (ማሪዋና) የተባለው አደንዛዥ እፅ ከቅጠሎች ወይም ከተክሉ የሚወጡትን ንጥረ ነገሮች በሲጃራ መልክ በማጨስ ምክንያት የአእምሮ ለውጥ እንዲከሰት ያደርጋል:: ካናቢስ ኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በካናዳ እጅግ በጣም ከተስፋፉ የአደንዛዥ እፅ አይነቶች ውስጥ አንዱ ነው:: ይህ እፅ በአረገራችን ሀሺሽ ተብሎ የሚጠራ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በወጣቶች ዘንድ እየተዘወተረ ያለ ነው:: እፁን የተጠቀሙ ሰዎች ከፍተኛ የሆነ የስሜት ለውጥ፣ የልብ ምት መጨመር፣የድፍረት ስሜት ማየል ወዘተ ይታይባቸዋል::

ለምሳሌ፦ እናቱን እስከመድፈር ሊከሰት ይችላል:: በመሆኑም እፁን ከተጠቀሙ በኋላ ሴተኛ አዳሪ ጋር መሄድ፣አስገድዶ መድፈር፣ ኮንዶም አለመተቀም ወዘተ ስለሚከሰት በኤች. አይ.ቪ. በቀላሉ የመያዝ እድልን ይጨምራል::

5. ሰመመን (ህልም) ፈጣሪዎች (Hallucinogens or psychedelics)

እነዚህን አደንዛዥ እፅ አይነቶች ተጠቃሚዎቹ ይህን አለም የሚ ያዩበትን፣የሚሰሙበትን፣የሚ ቀምሱበትን፣የሚዳስሱትንና የሚያሸቱበትን የስሜት ሁኔታ በመለወጥ ሌላ መንፈስ ውስጥ መክተቱ ነው:: በመሆኑም ይህንን እፅ የሚተቀሙ ሰዎች ከፎቅ ላይ ራሳቸውን ሊወረውሩ ወይም በመኪኖች መካከል ሊሄዱ ይችላሉ:: ምክንያቱም የሚበሩ ወይም ከመኪኖች በላይ የሚሆኑ ስለሚመስላቸው ነው:: የግብረ ስጋ ግንኙነትንም በተመለከተ የተለየ ገድል ለመፈፀም ስለሚፈልጉ በቀላሉ ለኤች.አይ.ቪ. ሊጋለጡ ይችላሉ::

6. ተመሳስለው የተሰሩ (የክበብ) እፆች (Designer or club drugs)

እነዚህ እፆች በቤተ ሙከራ ውስጥ ሌሎች አደንዛዥ እፆችን በማስመሰል የሚሰሩ ናቸው:
: አብዛኛውን ጊዜ ጥቅም ላይ ሚውሉትም በምሽት ክበቦች፣በጭፈራ ቦታዎች፣ ወይም ሙዚቃ በሚታይባቸው አካባቢዎች ነው:: እፆቹ የተጠቃሚዎቹን ስሜት የሚያነቃቁበትና ሰዎቹን የሚጎዱበት መጠን ተመሳሳይ ነው:: ብዙ በተወሰዱ ቁጥር ስሜት እየጨመሩ የሚሄዱ ሲሆን ከፍተኛው ደረጃ ግን እስከሞት ሊያደርስ ይችላል:: እነዚህ እፆች በወንዶች አማካይነት የመጠጥ ብርጭቆ (ጠርሙስ) ውስጥ ተጨምረው በሴቶች ላይ የወሲብ የበላይነትን ለማሳየት ጥቅም ላይ የሚውሉ ናቸው:: በዚህም ጊዜ ይህንን ድርጊት የሚፈፅሙት ወንዶች ኮንዶምን ባለመጠቀም ኤች አይ ቪ እንዲተላለፍ ያደርጋሉ::

በአጠቃላይ ከላይ እንደተመለከተው ኤች አይ ቪ በከፍተኛ ሆኔታ እየተሰራጨ ከሚገኝባቸው ምክንያት ውስጥ አልኮልና አደንዛዥ እፆች ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚያደርጉ ነው:: አልኮልንና አደንዛዥ እፆችን ብቻ ለብቻ ለያይተን ብንመለከትም አብዛኛውን ጊዜ ተጠቃሚዎቹ ለማደባለቅ የሚወስዷቸው መሆኑ ይታወቃል:: ስለዚህ ችግሮቹንም የተወሳሰቡ ያደርጓቸዋል:: እዚህ ላይ ማሰብ የሚገቡን ብዙ ነገሮች አሉ:: አእምሮአችን በረጋ መንፈስ በተጠቀምንበት ቁጥር ራሳችንንም ሆነ በእኛ ዙሪያ ያሉትን እንጠቅማለን፣ ተክስ ከፋዩ ታማኝ ዜጎች እንሆናለን፤ሌሎች ያለባቸውን ችግሮች እንጋራለን፤ጥገኛ አንሆንም ውጤታማም እንሆናለን::

እናስብ፤እንወስን፤እንተግብር::!

ዋቢ መፃህፍት

1. -----------(2009) population — specific HIV/ AIDs status report: people from countries where HIV is endemic — Black people of African and Caribean descent living in Canada.
Puplic Health Agency of Canada, Toronto

2. Blocker, Jack, etal; (2003). Alcohol and Tempersance in Modern History: An international encyclopidia, ABC —CLIO, Inc., USA.

3. Leonard, Kennet E. And Howard T. Blare (1999). Psychological theories of drinking and Alcoholism (2nd ed). The Guil ford press, NewYork.

4. Daley, Dennis C. (2006). Addiction and Mood Disorders: Aguide for clients and Families. Oxford University press, USA.

5. Ludwig, Arnold M. (1988). Understanding the Alcoholics mind: The nature of carrying and how to control it. Oxford University press, USA.

ከገጽ 3 የዞረ

3. በፈላ ውሃ እና በጋለ ብረት እስረኛን በአሰቃቂ ምርመራ ማቃጠል (Torture) አመራሩ ከላይ የተጠቀሱት ክንዋኔዎች እንዲመራ ለብስራት አማረ ሃላፊነቱን ሰጠው። ወደ ዝርዝር ከመግባታችን በፊት የሰውየው ገጸ ባሕሪያት እኔ እንደማውቀው፣ ውሸት የሚያበዛ፤ ምቀኛ፤ አስመሳይ፤ አድርባይ፤ ለሰው ክብር የማይሰጥ ተሳዳቢ፤ ሰውን የሚንቅ፤ በትግሉ ወቅት የሚያጎበድድላቸውን አለቆቹን በመመካት እና ከአለቆቹ የተሰጠውን ኃላፊነት ምርኩዝ አድርጎ በመመካት ዝሙት በመፈጸም ሴትን አስፈራርቶ የደፈረ ነው።

ከላይ የተጠቀሱት በሁለት ክፈሎች የተመደቡት የ 06 ዘርፍ ስራዎችን ሽብር ለማካሄድ በሃላፊነት የተመድቡ ሌሎች ሰዎች አሉ። እነሱም፤-

1ኛው ብስራት አማረ ዋናው መሪ 2 አሰፋ ጉሬዛ 3 ተስፋይ ጡሩራ 4 ታደሰ (06) 5 ትእግስት አሰፋ 6 ሉኡል በርሄ 7 ታደለ 8 ያለምብርሃን 9 ነፃነት ሰንደቅ (ከትንሽ ጊዜያት በኋላ የተገደለ) እና አልፎ አልፎ አሰፋ ማሞ እና ሌሎች የመሳሰሉ የዚህ የሽብር ቡድን አባሎች ይገኙበታል። ዋና ተልእኳቸው በሕንፍሽፍሽ የተበከሉ ታጋዮች (ሀ) ከሠራዊቱ ከየክፍሉ አፍኖ መጥለፍና ሓለዋ ወያኔ አስገብቶ በሰቆቃ ደብድቦ ማስቃየት እና ከዚያ በኋላ ስለ ሁኔታው በውሸትም በትክክልም እንዳፈለጋቸው ለመደባቸው አመራር ማቅረብ ነው። አመራሮቻቸውም ለስልጣናቸው ማጎልበቻ እስከ ጠቀመ ድረስ በሰው ሕይወት የሚደርሰው ጉዳት ጉዳያቸው አልነበረምና ስለ ሆነም ማጋጣዎቹ ካድሬዎቻቸው እንደ የናዚዎቹ የጎስታፖ ቡድኖች የፈለጉትን ሽብር በማንኛውም ሰዓት ወቅት ቀን ይሁን በውድቅት ሌሊት የማፈን የመግደልና የማስፈራራት ተግባር በፈለጉት ሰው

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

# አይጥ ለሞትዋ የድመት አፍንጫ ታሸታለች!

(ብስራት አማረ ማነው?)

ከገጽ 3 የዞረ ላይ የመፈጸም ሙሉ መብት ነበራቸው። ጥፋት አደረጋችሁ ተብለውም የሚጠይቃቸው ዓለም አቀፋዊም ይሁን ሃይማኖታዊ ወይንም ባህላዊ አካል በስልጣናቸው ዙርያ የለም። ሁሉም በጁ ሁሉም በደጁ በጫካም ይሁን ዛሬም ስልጣናቸው የማይገሰስ ባለሙሉ ስልጣን ነገሥታቶች ናቸውና የተጎዳው ሰው ቤቱ ይቁጠረው። በሰላማዊ ዜጋ ላይ ከባድ ጉዳት አድረሰዋል። የኢ.ድ.ሕ አባል፤የደረግ እና የኢሕአፓ አባል እና ሰላይ፣ ፀረ ኤርትራ ነፃነት ነህ ወይንም ነሽ እየተባሉ ከላይ በተጠቀሱት የሽብር ቡድን አንቃሳቃሾች ትእዛዝ እና ተሳታፊነት ከየከተማውና ገጠሩ እየታፈኑ ለነ ብስራት አማረ እየተላለፉ በመስጠት ብዙ ሰብአዊ ጉዳቶች ተፈጽመዋል። እነኚህ የሽብር ቡድኖችና መዋቅሮች ተልእኳቸው ሽብር በማካሄድ ዲሞክራሲያዊ መብቶችን አፍኖ ሕዝቡ ለድርጅቱ ሙሉ ተገዥ ሆኖ በፍርሃት እንዲንበረከክ ማድረግ ነው።

እንግዲህ የሽብሩ መልክ እና ስፋት ሰፊና የተለያየ መልክ ቢኖሮውም አመራሩ በድርጅቱ ውስጥ ሕንፍሽፍሽ ተፈጥሯል ብሎ ራሱ አመራሩ የፈጠረው ሽብር በታጋዩ ውስጥ በጣም በርካታ ታጋዮች ከ1969- 1975 መጨረሻ የቀጠፈው ያጠፋው ህይወት ዘርዝሮ ለመጻፍ በዚች አጭር ፅሑፍ አስቸጋሪ ነው። ቢሆንም ብስራት አማረ ከነ ቡዱኑ አመራሩ በሰጠው ሃላፊነት የፈፀመው ግፍ ግድያ የሰቆቃ ድብደባ ባጭሩ ከነመረጃው አቀርባለሁ።

ብስራት አማረ ከ1969 ዓ.ም. ጀምሮ በሕንፍሽፍሽ ተለክፈዋል እየተባሉ ያጠፋቸው ጥቂቶች ከማውቃቸው ሰዎች መካከል፤

1. አበራ ማንካ (በብስራት አማረ የተገደለ ነገር ግን እራሱ ገደለ ተብሎ በአመራሩ ለሽፋን የተነገረለት)
2. ተስፋይ (ተስፋይ ህንፍሽፍሽ ተብሎ በአመራሩ የቅጽል ስም የተሰጠው) ብስራት አማረ በሰቆቃ (በቶርቸር አሰቃይቶ) የገደለው፥
3. ወዲ ሓኤታ እንደ ተስፋይ በሰቆቃ የተገደለ
4. ኪዳነማርያም በላይ - የፈላ ውሃ ጭንቅላቱ ላይ ተደፍቶበት የሞተ፤
5. ኃ/ሥላሴ ገ/ሚካኤል በድብደባ እና በጋለ ብረት የተገደለ፤
6. አባዲ ተምቤን (ጎልያድ) በብስራት አማረ የተገደ (ወያኔ የሚለው ራሱ የገደለ)
7. ጐይቶኦም አብረሃ
8. ዳዊት ግምባር (ሕንፍሽፍሽ)
9. ግርማይ ዘርኦም
10. ብስራት አለማየሁ
11. ሐጐስ ኃይለስላሴ
12. ሐድሽ ዮሐንስ
13. ንግሥቲ
14. ግደይ
15. ዘርኡ በዛብህ
16. ሙሉጌታ አብርሃ
17. አዛናው ገ/ጻድቅ (ይህ ታጋይ ከመለስ ዜናዊ እና ከስብሐት ነጋ ጋር በነበረው ቅራኔ ብስራት አማረ ዛና ወረዳ አካባቢ አፍኖ አጠፋው
18. ባሻይ ሐንጣል
19. ተኽላይ
20. ክንፈ ራያ ወዘተ ናቸው።

እነዚህ ለምሳሌ የተጠቀሱት ባሕርን በማንኪያ እንደመጨለፍ የቀረበ እንጂ ረጋ ብሎ በጥናት ይቅረብ ከተባለ በጣም በርካታ ሕይወት ብስራት አማረ በሚመራው የሰቆቃ እና የስለላ ዘርፍ የተገደሉ እና ከየክፈላቸው እየተለቀሙ ታፍነው ደብዛቸው የጠፉ እጅግ በጣም፤በጣም ብዙ ናቸው።በሰቆቃ ማለት በፈላ ውሃ በድብደባ በጋለ ብረት በእሳት እየተሰቃዩ የጠፉ በርካታ የሰዎች ህይወት ተጠያቂዎቹ አመራሮቹ እነ ስብሓት ነጋ እና እነመለስ ዜናዊ እንዲሁም በሰው ልጆች ላይ ክፉ ሰቆቃ ሲፈጽሙ ከነበሩት መካከል ሰው እያፈነ የሕዝብን ሰላም በፍርሃት ሲያስሸብረው የነበረው "የወያኔ ጀስታፖው" ቡድን መሪ ብስራት አማረ እና መሰሎቹ ለተፈጸሙት ኢሰብአዊ እርምጃዎች በሃላፊነት ተጠያቂዎች ናቸው።

የብስራት አማረ የሽብር ቡድን እና ተግባር እስከ 1975 ዓ.ም በተቀናጀ የአፈና እና የግድያ እንቅስቃሴ ያለምንም ተጠያቂነት አሁንም ወደ ሰላመዊ ነዋሪ ሕዝብ ተሸጋገረ።ለምሳሌ ከሕዝቡ መሃል እየታፈኑ የውሃ ሽታ ሆነው እዚህ ቀሩ ሳይባሉ እየታፈኑ የተገደሉት ጥቂቶቹን ልጥቀስ።

በ1971 ዓ.ም. መጀመሪያ አካባቢ ብስራት አማረና በስራ ከሚገናኘው በመቀሌ አካባቢ የከተማ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ የነበረው አለማዮህ በቀለ ከሚባለው ሃገረ ሰላም ኗሪ የሆኑ በጠላ ንግድ የሚተዳደሩ ሁለት ወጣት ሴቶች በተደጋጋሚ አስገድደው ከደፈሯቸው በኋላ ድርጊታቸው በታጋዩ እና በሕዝቡ እንዳይጋለጥባቸው የደርግ ሰላዮች ናቸው በማለት በብስራት አማረ ሪፖርት ተዘጋጅቶ በሌሊት ከመኖሪያ ቤታቸው አፍኖ በመውሰድ ያጠናቀረውን ሪፖርት ለስብሓት ነጋ አቅርቦ በሁለተኛው ቀን በሓለዋ ወያነ አባሎች በጥይት ተደብድበው እንዲረሸኑ ተደርጓል።

በ1972 ዓ.ም. ብስራት አማረ እና አፋኙ ጉጅሌው ከማይጨው ወደ መቀሌ በሚወስደው ዋና መንግድ ላይ አድፍጦ በመጠበቅ አንዷት መኪና ሰዎች ጭና ወደ መቀሌ አቅጣጫ ስትጓዝ ቤት ማራ በሚባለው ቦታ አስቁሞ 6 አስተማሪዎች 2 ከደሴ የመጡ የመንግሥት ሠራተኞች ከመኪናው እንዲወርዱ በማድረግ አስገድዶ በመጥለፍ ፃኢ ወደ ሚባል አካባቢ ወሰዳቸው። ብስራት አማረ እነኚህ ሰዎች ከጠለፈ በኋላ ብዙ የመቀሌ ኗሪ የሚያውቀው በቅጽል ስም "ጥንቸል" እየተባለ የሚጠራው እና አራት አስተማሪዎች እንዲሁም ሁለት የደሴ ሰዎች በጠቅላላ 6ቱ ሲገደሉ የዓድዋ ተወላጆች የሆኑት የተቀሩት ሁለት አስተማሪዎች ግን በነፃ ለቀቃቸው። ሲገደሉም ብስራት አማረ ለአባይ ፀሃየ ስለተጠለፉት ሰዎች ጉዳይ እንዲገደሉ ብሎ ሪፖርት አቅርቦለት ይገደሉ አለ፡ብስራትም እንዲገደሉ አደረገ።

ሌላው አሳዛኝ ድርጊት በ፶አለቃ በላይ የሚባል ተመርተው በሰላም እጃቸው የሰጡ የኢትዮጵያ የደርግ ወታደሮች በብስራት አማረ የተዘጋጀ ሪፖርት ለመስ ዜናዊ እና ስብሐት ነጋ ከተሰጠ በኋላ በሙሉ አማራዎች ስለነበሩ ግደሏቸው ተብሎ 1 ብስራት አማረ 2 ክንፈ 3. ገ/መድኅን 4. አለምሰገድ እይንቺ 5. ሐሰን ሽፉ ሆነው ከ06/ ባዶ ሽድሽተ/ ከሓለዋ ወያነ አባላት ጋር በመተጋገዝ በሚጠጡት ውሃ ላይ መርዝ ተጨምሮበት ውሃው እንዲጠጡት ተደርጎ አብዛኞዎቹ ወዲያው ሲሞቱ በሞት አፋፍ ሲግሩ የነበሩት ቀሪዎቹ ደግሞ በጋለ ብረት ሆድ እቃቸው እያስገቡ ጨረሿቸው። ጊዜው በ1972 ዓ.ም. ወርዒ ውስጥ ነው።

በሰላማዊ ትግራይ ዜጎች ላይ ተፈጸመ አፈና እና ግድያ አሁንም ብስራት አማረ ከአሸባሪው የወያኔው ጀስታፖ ቡድን በመንቀሳቀስ በቀንም በሌሊትም እያፈነ የወሰዳቸው ኗሪዎች፤

1. ፊታውራሪ ብፁእ ወ/ጊዮርጊስ እንደርታ
2. ቀኛ/ኪሮስ ዓድዋ
3. ቀኛ/ኃይለስላሴ ዓድዋ
4. ግራ/ታደለ ማሩ ተምቤን
5. አቶ ወርቀ ልዑል ተምቤን
6. ፊታውራሪ ዘገየ ክለተ አውላዕሎ
7. ግራ/በላይ ገብሩ ተምቤን
8. አቶ ኪዳነ ሐጐስ
9. ወ/ሮ አባዲት
10. አሰፋው ወልዷ አረጋይ ዓድዋ ይሓ
11. ቄስ አርኣያ ዛና
12. ቀኛ/እምብዛ ዛና

ወዘተ…የመሳሰሉ ሰዎች በብስራት አማረ መሪነት እየታፈኑ መድረሻቸው የጠፋ የውሃ ሽታ ሆነው ቀርተዋል። በእነ ብስራት የሚመራው አሸባሪው ቡድን በፈለገው ቦታ እየተንቃሰቀሰ ሕዝብን ሲያፍን በሽሬ አካባቢ ደግሞ ሌላው በህወሓት አሸባሪው የስለላ እና የምርመራ እንዲሁም የእስር ቤት ሰቆቃ ፈጻሚ ቡድን ሽሬ ውስጥ በእነ አበበ ተክለኃይማኖት (ጆቢ/ዑስማን) እነ አውዓሎም ወልዱ፤ ታደለ እና የመሳሰሉ በብዙ ሰዎች ላይ ሰቆቃ ሲፈጽሙ ነበር። ለምሳሌ- 1 ሃለቃ ገ/ሚካኤል 2. አቶ ገብረሊባኖስ መዝገቦ 3. አቶ ገዛኢ ረዳ 4.አቶ ተወልደ ገ/ሥላሴ 5 አበበ ገ/ማርያም 6. አቶ ሙሉጌታ ደስታ 7. አቶ በላይ ባህታ 7 ቄስ ጽጌ 8. አቶ ወልደ ንጉሥ 9.አቶ ገብረጻድቅ ጸጋይ 10 ሃለቃ ጥላሁን እና በ እድሜ እጅግ ወጣቶች የሆኑትን ሳይቀር በሰቆቃ እየተሰቃዩ በጥይት ተደብድበው ተገድለዋል። ከላይ የተጠቀሱት ሰዎች የሽሬ አውራጃ ተወላጆች ናቸው።

ብስራት አማረም በበኩሉ ሌላው የሽብር ቡድን በመምራት ከ1970-1972 ዓ.ም. በየከተማው የፈጸሙትን ሽብርና ግድያ እንደገና እንመለከት።

ዓድዋ፦ በ1971 ዓ.ም. አካባቢ ዓድዋ ከተማ ከቀኑ 11 ወ/ሮ ጉንቦወርቅ የሚባሉ ጠጅ ነጋዴ ቤት በመግባት እጅ ወደላይ ብሎ ያስገደላቸው ሰዎች 1. መምህር ይሕደጐ 2. አቶ ብርሃነ ኪ/ማርያም 3. ፍስሃ የሚባል ወጣት ነጋዴ 4. አቶ ቢተው ብርሃነ ጠጅ ቤቱ ውስጥ እያሉ ሲገደሉ ከመጠጥ ቤቱ ውጭ ደጃፍ ላይ የተገደሉ ደግሞ 1. አቶ አብርሃ አበራ 2. አቶ ገብረዝጊ ዓለማየሁ ይባላሉ። የመጠጥ ቤቱ ባለቤት ወ/ሮ ጉንቦወረቅ ታፋቸው ተመቱ፣ ግን አልሞቱም ። አቶ ተፈሪ ተክለሃይማኖትም እግራቸው ተመትተው ቆሰሉ። በዚህ መልክ የብስራት አማረ የሽብር ኦፐረሽን ቡድን 6 ሰዎች ገድሎ 2 ሰዎች አቁስሎ ወጣ።

አክሱም፦ በመግድያ ፈጻሚ ክፍል (ፈዳይን) የተሰማሩ አክሱም ተወልደው አክሱም ያደጉ የከተማው መውጫ እና መግቢያ የሚያውቁት የአክሱም ልጆች እና ብስራት አማረ ከሚያስተባብረው የሽብር ግድያ የአፈና የእስራት እና የስለላ ቡድን ጉጅሌውን መርቶ አክሱም ከተማ በመግባት መምህር መልአኩ መንገሻ እና ሁለት አስተማሪዎች አስገድሎ አንድ ተማሪ አቁስሎ ወጣ።

መቀሌ፦ ብስራት አማረ ከነቡዱኑ መቀሌ ከተማ ተሽሎክሉኮ በመግባት አለነ ቢሆን የሚባለው ታጋይ ከበረሃ ሸሽተው እጃቸውን ለደርግ የሰጡ እና የግ.ሓ.ት (ግምባር ሓርነት ትግራይ) አባሎች የነበሩ ከወያኔ እስር ቤት ከሞት አፋፍ ያመለጡትን እነ ተፈራ እነ ሃይለኪሮስ የመሳሰሉት ለመግደል መድኅን መልጐም ወደ ተባለ ቡና ቤት አለነ ቢሆን የተባለ የበረሃ ታጋይ ገብቶ ሁሉም መጠጥ እየጠጡ እዛው ባሉበት እንዲረሸናቸው በመግባት ሁለት ሰዎች ገድሎ ከቡና ቤቱ ለማምለጥ ሲሞክር ከቡና ቤቱ ውስጥ ከነበሩት ሰዎች በተተኮሰበት ጥይት ህይወቱ አልፎ የነብሰ ገዳዮቹ ቡደኑ እና የስለላው አቀነባባሪ እና መሪው ብስራት አማረ ግድያውን አስፈጽሞ ወደ በረሃው ተመለሰ።

ሽሬ - ብስራትና ጉጅሌው ሽሬ ከተማ ገብተው ተከስተ አሰፋ የሚባል የፊታ/ አሰፋ ልጅ ከሦስት ጓደኞቹ ጠላ ቤት ገብተው እየጠጡ ሲዝናኑ ብስራት እና ጉጅሌው ተከታትሎ በመግባት ተከስተ አሰፋ እና ሦስቱ ጓደኞቹ ገድሎ አንድ አዛውንት የፖሊስ ጡሮተኛ አቁስሎ ወጣ። ብስራት አማረ በሁለት አውላዕሎ እና አዲግራት እና በተለያዩ የትግራይ ከተሞች ሰላዮች እና ነብሰ ገዳዮች (ፈዳይን) በማሰማራት ተመሳሳይ ሽብር በሰው ህይወት ላይ መውሰዱ ይታወቃል። ብስራት አማረ በነበረው የደህንነት፤ የስለላ እና የእስር ቤቶች (ሓለዋ ወያነ) ሃላፊነት ሲፈጽመው የነበረው የህ.ወ.ሓ.ት. ሽብር ስራ አሁንም እስከ 1978 በጥልቀት ሲያስፈጽም የነበረው የአፈና፤ የመግደል ሰቆቃ ተግባር በተደራጀ መልኩ ቅርንጫፎቹ እንደተስፋፉ መዋቅሩ እንደሚከተለው ተዘርግቶ ነበር፡

ፖሊት ቢሮ የበላይ ሃላፊዎች፡ መለስ ዜናዊ፥ ስብሓት ነጋ፥ አባይ ጸሃየ

የደኅንነት ዋና ሃላፊ፡ ክንፈ ገ/መድኅን

የሓለዋ ወያነ የበላይ ተጠሪዎች፡ ሓሰን ሽፋ፣ ቢተው በላይ፣ ብስራት አማረ፣ ዘርአይ ይሕደጎ (ዘርአይ ማንጁስ)

የስለላ እንዲሁም የሲቪል እና ሙርኰኞች እስር ቤት፡

የሴት ሲቪል እስር ቤት(063)
የወንድ ሲቪል እስር ቤት (062)
የሙርኰኞች እስር ቤት (061)




Tikam K. Lalla, LL.B.

• BARRISTER • SOLICITOR • NOTARY PUBLIC

•ኢሚግሬሽን •ቪዛ •የህግ ውክልና

• House Purchase/Sale/ Mortgages
• Wills • Incorporation • Business
• Immigration • Visa • Declarations
• Power of Attorneys • Notarizations

ቲካም ኬ ላላ፥ የህግ ጠበቃ

Toronto Main Office:
1203B Bloor St. W., Toronto, ON, M6H 1N4
(Between Lansdowne & Dufferin)
Tel: 416-532-2801 • Fax: 416-532-4942
email: tklalla@rogers.com


Mississauga Home office:
5159 Hidden Valley Court
(Eglinton & Creditview)
Tel: 905- 812-8004
(Evening & Weekends - By appointment only)

SUNRISE
TRUCK AND AUTO COLLISION AND GENERAL REPAIR

በብራምፕተን ኦንታሪዮ (Brampton, Ontario) እና አካባቢው ለምትኖሩ አሽከርካሪዎች በሙሉ፥ መልካም ዜና! በማንኛውም መንገድና ሁኔታ ልትተማመኑበት የምትችሉ የመኪና መጠጋገኛ መደብር እናስተዋውቃችሁ - ሳራይዝ (Sunrise) ይባላል!!

INSURANCE CLAIMS WELCOME

www.sunrisetruckandauto.com



• Body Work, Paint, & General Repairs
• Complet Collision & Wheel Alignment Services
• We Also Sell Quality Used Cars & Tires

Call Paul or Darshan
**Tel: (905) 453-5899**
**Fax: 905-453-3209**
12 Hale Rd.
Brampton Ontario

ወዲ ሻምበል፣ አበበ ዘሚካኤል፣ ታደሰ መሰረት የታጋዮች እስር ቤት
የሴት ታጋይ እስር ቤት (065)
ወንድ ታጋይ እስር ቤት (064)
እነኚህ አምስት ዋና ዋና ክፍሎች ሰቆቃ የርሸና/ግድያ የአፈና ስራዎች የሚካሄድባቸው ፈጻሚ እና አስፈጻሚ ክፍሎች ናቸው።

ከዘሚካኤል ለገሰ (ወዲ ሻምበል) ስር
064 የሚቆጣጠረው ታደሰ
065 ደግሞ ብርሃነ ሲሆኑ
ከብስራት አማረ ስር
061 ካሕሳይ ቆራጽ
062 ግደይ ወዲ ፊውዳል
063 ወዲ ኮበል
የመሳሰሉት አሉበት።

እነኚህ እስር ቤቶች የሚገኙት “ግህነም” ከሚባላው ቦታ ፀገዴ ውስጥ ነው። እስረኞች የሚታሰሩበት ክፍሎች ብዛት እስከ 150 ክፍሎች ሚደርሱ ሲሆኑ፤ ከመሬት በታች ሁለት ሜትር ጥልቀት ተቆፍሮ ከመሬቱ ተመሳስሎ የተሰራ በ4,500 የወታደር ሙርከኛ እስረኞች ጉልበት ነበር የተገነባው። ተገደው ይህ እስር ቤት የሰሩት ሙርከኞችም እዛው ገብተው እንዲታሰሩ ተደረገ።

ይህ ቦታም አሰቃቂ እና ሰቆቃ የሚካሄድበት አስፈሪ እስር ቤት የሚጠብቁት ዘበኞች ብዛት 500 ታጋዮች ሲሆኑ ሁሉም ጉልበተኞች እና ደንዳና ቁመና ያላቸው ምልምል ታጋዮች ናቸው። መጀመሪያ የተረሸኑት እንኚህ 4,500 የሚሆኑ እስር ቤቱን የቆፈሩት ሲሆኑ ከመላው ኢትዮጵያ ጎሳዎች የተውጣጡ ወታደራዊ ምርኮኞች ይሁኑ እንጂ አብዛኛዎቹ አማርኛ ተናጋሪ አማራዎች ነበሩ።

ምርኮኛ እየተባላ በሰላም እጁን የሰጠ ደርግ ካድሬዎች፤ የደርግ አባል፤ የደርግ አገልጋይ ወ.ዘ.ተ. እየተባለ ሴቶችም ሳይቀሩ ከጐንደር፤ ወሎ፣ ጐጃም በገፍ ወደ እዚሁ የምድር ገሃነም እየተወሰዱ በብዙ ሺሕ ሚቆጠሩ ሕይወት በመለስ ዜናዊ፣ በሰብሓት ነጋ እና አባይ ፀሓየ አርከበ ዑቕባይ የመሳሰሉት የዛው ግደለው ደብድበው አፍነው የሚል ትእዛዝ በመስጠት ትእዛዛቸውን ለሚፈጽመውና ለሚአስፈጽመው ለብስራት አማረ በሚተላለፍለት መመሪያ ተረሻኞቹ የሚቀበሩበትን ጉድጓድ ተቆፍሮ በጅምላ የተቀበሩ ሰዎች መቃብር በዓይኑ ያየ ሰው ዘግናኝ እና አስፈሪ በመሆኑ ጤነኛ እንቅልፍ መተኛት ያስቸግራል። በጣም የሚገርመው 10 ሺህ ሰው ገድያለሁ ሲል የተደመጠው ብስራት በሰው ልጆች ላይ የፈጸመውን ግፍ ይቅርታ ጠይቆ ከመጸጸት ይልቅ አሁንም አሜሪካ አገር እየኖረ ለአለቆቹ ጥብቅና ቆሞ ማየት እጅግ ያሳዝናል።


ውድ ኢትዮጵያውያን ሆይ!

በብስራት አማረ እጅ በጥይት ተደብድቦ የተረሸነው ዜጋ እሱ ከሚያምነው በላይ እጅግ በርካታ ህይወት ጠፍቷል። ብስራት አማረ በነበረው የስለላ፤ የምርመራና የእስር ቤቶች ተቋም እና የፈዳያን/የገዳይ ቡድን አቀናባሪነት ስልጣን ተጠቅሞ በፈጸመው ግፍ በሕግ ቋንቋ ጀነሳይድ ነው። ለፈጸመው ወንጀል በዓለም የሰብአዊ መብት ተማጓች ፍረድ ቤት መቅረብ አለበት። ይሄ ካልሆነ የሰው ህይወት ከድመት ህይወት ጋር የሚያወዳድሩት እነ ብስራት አማረ የመሳሰሉ የህ.ወ.ሓ.ት ቁልፍ ሰዎች በሰው ልጆች ደም እያላገጡ መኖራቸውን ሊቀጥሉ ነው ማለት ነው። ይህ ሁሉ ደም አፍስሰው ለሰው ልጆች መብት እና ዲሞክራሲ ተቆርቋሪ ንጹሃን ነን ሲሉ ላደመጠ ውስጣቸው ለሚያውቅ ሰው እጅግ ይዘገንናል። ስለዚህ ባንድነት ሆነን አቤት ማለት አለብን። ይባስ ብሎ አፋቸው መዝጋት ሲገባቸው እና የሰሩት

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# I WANT TO GIVE THANKS… TO NASA!

Thanksgiving is just around the corner and during this holiday the people in Leslieville and the Beaches will give thanks for living in one of the most abundant countries in the world. We'll also give thanks for our children's good health and the warmth of our homes. We'll give thanks for our family and friends and this year I think we should give thanks that so far no one has been hit on the head by space junk flying overhead.



Bob Cook

Now I know this isn't usually included in the traditional "thanksgiving toast" but I think it should. Let me explain.

Did you know that 2000 kilometers above Woodbine and Queen there are over 500,000 objects floating around just ready to fall to earth?

Now the majority of this stuff is smaller than 10 centimeters, which means about the size of your index finger.

But there are 19,000 other objects flying overhead that are larger than 10 centimeters, which means they could be the size of a bus.

And no this is not why the TTC bus on Woodbine Ave. was running late yesterday.

Now I don't want to be an alarmist but when you have that much "stuff" flying overhead it's good to know exactly what is falling from the sky.

According to NASA on September 23rd a decommissioned satellite the size of aforementioned TTC bus re-entered the earth's atmosphere over the Pacific. No one was hurt but fishermen on a Japanese whaler were freaked because looking for things the size of whales above the boat wasn't in their job description.

Now here's something else you should give thanks for. According to NASA'S Centre for Orbital and Re-Entry Debris, which is a place where people look for garbage in space. Our Canadian equivalent is a black bear at a dumpsite. The odds of getting hit on the head are one trillion to one.

The last time we heard odds like that people were talking about Mayor Rob Ford showing up at the Pride Parade.

Here's something else to give thanks for.


NASA had asked the federal government of Canada if they could use our vast wilderness for some of this falling debris. They were denied our wilderness and instead offered the riding of Beaches-East York because the residents had voted NDP in the last election. But cooler heads did prevail and it was finally decided that the space junk should go exactly where it would do the most good and that's Queen's Park!

አሪፍ
ARIF HEATING AND AIR CONDITIONING
More than 10 years experience

SERVICE & INSTALLATION
Residental-Commercial-Industrial
Force air furnaces-Mid
Efficiency furnaces-Hi
Efficiency furnaces-clean
& check up
Furnaces Boilers
Humidifiers-Central
air conditioning

Quality Work Manship
Satisfaction Guaranteed
Reasonable Rates
Services to all Makes & Models
Professional Courteous

24 Hours
EMERGENCY SERVICE




Haile Mammo
Certified Stationary Engineer
GF-1, OBM-1 1MT, HVAC



በክረምትም ሆነ በበጋ ወቅት የቤትዎን ውስጥ አየር ለማቀዝቀዝም ሆነ ለማሞቅ የሚጠቀሙበትን ቁሳቁስ ለማደስ፣ ለመግጠምና ለመቀየር ሲፈልጉ በሙያው ተገቢ ሰርቲፊኬት ያለውን ሃይሌን ያነጋግሩ።

Call: Haile Tel: 416 995 1244

# አይጥ ለሞትዋ የድመት አፍንጫ ታሸታለች!

(ብስራት አማረ ማነው?)

ከገጽ 8 የዞረ

ግፍ ሳይቆጫቸውና ይቅርታ ከመጠየቅ ፈንታ የበደሉትን ዜጋ እንደገና ሳያፍሩ ሲዘልፉት እና ከተሰደደበት አገር ሰላም ሲነሱት ይታያሉ።

ፋሽስቱ፣ ነብሰገዳይ፣ ሽብርተኛ እና ቅጠረኛው ህ.ወ.ሓ.ት በግንቦት ወር 1983 ዓ.ም. ኢትዮጵያ እንደተቆጣጠረ 1-ብስራት አማረ 2- ታደሰ መሰረት 3-ዘርአይ ይሕደጎ/ዘርኣይ ማንጁስ በቀጥታ ማእከላዊ ምርመራ በሰቆቃው ማእከል ውስጥ ተመደቡ። ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ‘መላ አማራ ሕዝብ ድርጅት’ በሚባለው ሰላማዊ ድርጅት በአባሎች እና አመራሮች ላይ ብዙ የሰቆቃ መርመራ በማካሄድ ባልዋሉት ወንጀል ፈጽመሃል እየተባሉ አዲስ አበባ ማእከላዊ ምርመራ ድረስ ከየክፍለሃገሩ እየተለቀሙ ሰቆቃ እንዲፈጸምባቸው ቁልፍ የደህንነት

ሰልጣን በመያዝ ተዋናዮች ከነበሩት በርካታ የህ.ወ.ሓ.ት. ባለስልጣኖች አንዱ ብስራት እና ከላይ የተጠቀሱ እና የመሳሰሉ አረመኔዎች ናቸው። እነ ፕሮፌሰር አስራት ስቃይ የዚህ ነብሰገዳይ እና ሕብረተሰብ አሸባሪ ቡድን ውጤት ነው። እነ አሰፋ ማሩ የተገደሉት በዘርአይ ይሕደጎ እና ግበረ አበሮቹ ነብሰገዳዮች ነበር። አንደነት ቢኖረን እና በዚህ ዓለም ሕግ የሚከበር ቢሆን ኖሮ እነ ብስራት አማረ በሰው ልጆች ህይወት ቀልደው ሲያበቁ ዛሬም እየተንደላቀቁ ስለ ዲሞክራሲ እና የሰው ልጆች መብት መከበር በወያኔ ጀሌዎች የሚካሄዱ የዜና ማሰራጫ ማእከሎች እየተጋበዙ ሕሊናቸውን ሳይወቅሱ እንደ ፒላጦስ ከደሙ ንጹህ ነን እያሉ ባልዘላበዱ ነበር። ጠመንጃ አንግበው በዜጎች ላይ የሰሩት ግፍ [በሞት] የሚያስቀጣ ወንጀል ነው የፈጸሙት። እነዚህ ሰዎች አንድ ቀን እንኳ ስህተት ፈጽመናል አላሉም።

እነ ብስራት አማረ “ሽብርተኛው እና ነብሰ ገዳዩ ወያኔ” ኤርትራ እንዳስገነጠለ የኢትዮጵያ ጥቅም እና ሉአላዊነት አልተከበረም ብለው ያዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሰላማዊ ሰልፍ ሲያደርጉ፣ እንደ ዱር አራዊት በፖሊሶች እየታደኑ እና እየተዋከቡ ማእከላዊ እና የመሳሰሉት አሰቃቂ እስር ቤቶች እየተወረወሩ የተገረፉ እና ልዩ ልዩ ሰቆቃ የተፈጸመባቸው ስናስታውስ የእነ ዘርአይ ይሕደጎ እና ብስራት አማረ የገነቡት የስለላ እና የሽብር ቡድን ያከናወነው ዘግናኝ ግፍ ብዙ ተማሪ የሚያስታውሰው ወቅት ነው።

በ1984 ዓ.ም. በአርባ ጉጉ እና በሌሎች ቦታዎች ብስራት አማረና አጋሮቹ የሲቪል ልብስ ለብሰው በወቅቱ የነበረው ጠቅላይ ሚኒስቴር ታምራት ላይኔ፣ መለስ ዜናዊ፣ በረከት ስምኦን እና የመሳሰሉ ባለስልጣኖች ትእዛዝ እና እውቅና ያለ ቦታው የሚኖር ተስፋፊ ነፍጠኛ እያሉ ከተገንጠይ ቡድኖች ጋር አባሪ አስተባባሪ ሆነው በአማራው ሕብረተሰብ ላይ ለተፈፀመው ግፍ ተጠያቂዎች ናቸው። በመጨረሻ ላይ በጠመንጃ ሃይል ተማምነው በዜጎች ላይ ቁጥር ስፍር የሌለው ግፍ ከፈጸሙ በኋላ ባዲስ አበባ ኗሪ እና በሌሎቹ ዓይን ውስጥ ስለገቡ ስብሓት ነጋ እና መሰል አለቆቻቸው ድጋፍ ታክሎበት ዘርአይ ይሕደጎ/ ዘርአይ ማንጁስ ወደ እንግሊዝ አገር ለትምህርት ብለው ላኩት። ብስራት አማረ ደግሞ ወደ አሜሪላ ላኩት። የሁለቱ ድብቅ ተልእኮ ግን ዘርኣይ ማንጁስ አውሮጳ ውስጥ ካሉት የትግራይ ተወላጆች አስተባብሮ ስደተኛው እና ተቃዋሚ ሃይሎችን እንዲሰልል (በነገራችን ላይ ዘርኣይ በማዕርጉ የወያኔ ሻምበል ነው) በዚህ እንቅስቃሴ ተሰማርቶ የዓድዋ የሽሬ የአክሱም ተወላጅ ተባባሪዎች ሲያገኝ የስለላ ትምህርቱን እየተማረ በተሰማራው ተልእኮም እየፈጸመ ይገኛል። በዚህም ወያኔ ከፍተኛ የገንዘብ ጠቀሜታ እና እንክብካቤ ይደረግለታል። ዘርአይ ማንጁስ ትውልዱ አክሱም ነው።

ብስራት አማረም ያው ትውልዱ አብረው አክሱም ናቸው። ብስራት ‘ጅብ በማያውቁት አገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ አለ’ እንደሚባለው የፈጸመው ግፍ እና ሰብአዊ ወንጀል አይታወቅብኝም በሚል ራሱን በማታተለል ጨዋታ ተጠምዶ አሜሪካ ውስጥ ሆኖ ኢትዮጵያውን የወያኔ ተቃዋሚዎችን ሲዘልፍና ለሻዕቢያ ጥብቅና ቆሞ የሻዕቢያን ፖሊሲ የሚቃወሙ የትግራይ ህወሓት ታጋዮችና ኗሪዎችን ሲያሸብሩ ከነበሩት ከነ ኰሎኔል ይትባረክ የመሳሰሉ ከጥቂት እሱን መሳይ የወያኔ ካድሬዎች ጋር ሆኖ ሕብረተሱን በመከፋፈል በየቤተክርስትያኑ እና ትግራይ ተወላጆች ማሕበራት እጁን እያስገባ አንድነት እንዳይኖር የመለስ እና የስብሓት ነጋ ተልእኮ ለብዙ ዓመታት ያለ ስጋት በመፈጸም ላይ ይገኛል። ያ አልበቃ ብሎ አሉላ አባ ነጋ በተባለ የመለስ ዜናዊ ካድሬዎች ፕሮፓጋንዳ መጨፈሪያ ፓል ቶክ ውስጥ እሱ እና ኰሎኔል ይትባረክ በመሆን እኔ ባቀረብኩት የ1977ቱ የዝርፍያ ሰነድ ከመተቸት ይልቅ አንዴ “ሊሆን ይችላል” ሲል አንዴ ደግሞ “ገብረመድኅን አርአያ ተደረገ የተባለው ዝርፍያ የሚያውቅበት ስልጣን ወይንም ግንኙነት አልነበረውም” እያለ የአለቆቹን ንቅዘት/ ሙስና እና አምባገነንነት ለመከላከል ከመዘላበድ አልፎ እኔን ወደ ተራ ዝልፊያ በመግባት ከንቱ ሙከራ ማድረጉ ስታዘበው፣ ይሉኝታ የማያውቅ አንድ ፍጡር ባደባባይ እርቃኑን ጥሎ ቢራመድም ደንታ እንደሌለው ያሳያል። ለድርቅ የተሰጠ ዕርዳታ ሁኔታ ማወቅ ከነበረበት እንደ እነ ተኽለወይኒ አሰፋ የመሳሰሉት እንጂ ገ/መድኅን አርአያ የሚያውቀው ነገር የለም ሲል ፓል ቶክ ውስጥ ተናግሯል ሲሉ ሰዎች ነግረውኛል። ስልጣን ካልነበረኝ ተክለወይን አሳፋ እና እኔ አርዳታ ከሰጡት ፈረንጆች ጋር ቁጭ ብየ ገንዘብ እየቆጠርኩ የሚያሳየው ዓለም የተመለከተውን የቢቢሲውን ፎቶግራፍ “ ገ/ መድኅን አርአያ ከሁኔታው ጋር የተያያዘ ስልጣን ካልነበረኝ የብስራት አማረን ምሳ እና እራት ቂጣ ስጋግር የተነሳሁት ፎቶ ነው ሊል ነው?” የመለስ ዜናዊ ካድሬዎች እና ብስራት አማረ ለማያውቃቸው ሰው ውሸታቸውን ሲዘላብዱ ለሚሰማ እውነት ይመስላቸው ይሆናል። ለዚህም ነው ሰውየው ውሸታም ነው የምላችሁ። አውነታው ለምናውቀው ግን ከሚዘላብዱት ቅጥፈት የተለየ ጉድ የተሸከሙ ጉደኞች ናቸው። የትግራይ ተወላጆች ከነዚህ ውሸታሞች ራሱን ማግለል አለበት። ያ ሁሉ ግድያና ግፍ ፈጽመው ምንም የማይሰማቸው አረመኔዎች ናቸው። ሳይነካ ኑ ንኩኝ እያለ የሚወተውት ለችግር ራሱን የሚጋብዝ ፍጡር እንደ ብስራት አላየሁም።

ብስራት ለወያኔ መቆሙ የራሱ ፍላጎት ነው። ነግር ግን ከሰራው ገበና ሳይጸጸት እንደ ገና በላያችን ላይ ሊወጣብን ሲሞክር አስገራሚ ነው። ወያኔ በግፍ የተጨማለቀ ድርጅት ነው። አንድ ቀን በግህንም የተፈጸመው የግፍ ግድያ በ1980 ዓ.ም. በግንቦት ወር ደጀና ውስጥ ለውይይት ተሰብስበን አባይ ጸሃየ በድንገት “በዖት ግህንም ውስጥ የታሰሩ ሲቪል እስረኞች እና ደርጎች የሰው ዘር በግፍ እየገደልን ነው ...” ካለ በኋላ ሳያስበው ድንገት ከሕሊናው ገፍቶ የወጣው ንግግሩ አስደንግጠው፣ ፊቱ ሁሉ ተለዋወጠ እና ከስብሰባው ተነስቶ ሄደ። ህ.ወ.ሓ.ት. የመላእክት ድርጅት ነው፣ በሰው ልጆች ላይ ግፍ አልፈጸምንም እያለን ያለው ብስራት አማረ እየተከላከለለት ያለው የፋሺስቶች ድርጅት በኔ ላይ የተደረገው የመግደል ሙከራ እና የአካል ማጉደል ወንጀል ብስራት እንደ ዲሞክራሲ ይመለከተዋል። የህ.ወ.ሓ.ት አረመኔ ስራ በተመለከተ ለወደፊቱ በዝርዝር የማቀርበው አሰቃቂ የወያኔ ህ.ወ.ሓ.ት. አመራር የፈጸመው ደርግ በቀይ ሽብር ያስደነገጣቸው ልብ ያልሰሩ ታዳጊ ወጣቶች ወደ ትግሉ ከተቀላቀሉ በኋላ በነዚህ ላይ አመራሩ ያሳለፈው (ከ1970 ዓ.ም-1972 ዓ.ም) የርሸና ውሳኔ አቀርባለሁ። እነኚህ የሞት ቅጣት የተወሰነባቸው እና እርምጃ የተወሰደባቸው ታጋዮች ዕድሜአቸው ለአቅመ አዳም ያልደረሱ የ13 እና 14 ዕድሜ ወጣቶች ናቸው። ሁሉም የበረሃው ኑሮ መቋቋም አቅቷቸው፣ ወላጆቻቸው የናፈቁ ህጻናት ነበሩ። ወላጆቻችን ናፍቀውናል እና ወደ እየ ትውልድ ቀያችን መመለስ እንፈልጋለን የምትሉ አስታውቁን ይፈቀድላችኋል ብሎ አመራሩ ካታለላቸው በኋላ፡ እንሄዳለን ብለው እራሳቸውን ያጋለጡ ልጅ እግር ታጋዮች ከየቦታው ከሠራዊት ማሰልጠኛ እና ከታጋይ ጋር የተቀላቀሉትን ሁሉ እየተለቀሙ ተረሽነዋል። አረመኔው ወያኔ እነኚህ በጥይት ደብድቦ የገደላቸው ህጻናት “ናብ እነይ” (ወደ እናቴ) በሚል ቅጽል ይጠራቸዋል።

የእነኚህ ወጣቶች ብዛት በጣም በርካታ ስለነበር፣
1ኛ ፃኢ ሓለዋ ወያኔ ወዲ ሻምበል፣ ዘርኣይ ይሕደጎ እና ሙሉጌታ ዓለምሰገድ
2ኛ ዓዲ በቅሊ 06 ዓለምሰገድ እዩንቺ እና ተስፋይ ጡሩራ
3ኛ ዓዲ ጨጓር 06 - ድልዋ- ብስራት አማረ - እና አሰፋ ጉሬዛ
4ኛ ሰር 06 ጆቢ አበበ ተ/ሃይማኖት እና አወተ ተስፋይ
6ኛ ባሽላ 06 አበበ ዘሚካኤል፣ ሙሉጌታ ወዛም


TANA PRINTING ENT.
ጣና ማተሚያ ቤት

ማንኛውንም የህትመት አገልግሎት በየትኛውም ቋንቋ እንሰጣለን።
Complete Printing & Copy Services Including Wedding Invitations



2,500 Full Color Business Cards (Both Sides) $125

5,000 Full Color Business Cards (Both Sides) $199

10,000 Full Color Business Cards (Both Sides) $375

Limited time offer
633 Vaughan Rd. Toronto ON. M6C 2R4 (Vaughan & Oakwood)
Tel: 416.654.2020
Fax: 416.653.6191
e-mail: print@tanaprinting.com
website: tanaprinting.com





አድማስ የቪዲዮ አገልግሎት
ADMAS VIDEO SERVICES
SINCE 1996
ለሠርግ
ለቀለበት
Wedding
Behailu
(416)6993921
(647) 9913921
በፕሮፌሽናል ዲጂታል ካሜራ በማንሳትና ኤዲት
በማድረግ ጥራቱን እንደጠበቀ በDVD/HD ያቀርባል
.Digital Video Editing Services.

# ኤች አይ ቪ ኤድስ አልኮልና አደንዛዥ እፆች

በዳዊት የማታው ወርቁ(ቶሮንቶ)

የኢትዮጵያውያን ማሕበር በቶሮንቶ እና አካባቢው የኤች አይቪ ኤድስ መከላከያ እና ትምህርት ፕሮግራም (የበጎ ፈቃድ ሰራተኛ)

## መግቢያ

ኤች አይ ቪ ኤድስ በመጀመሪያ ከታወቀበት ከ1981 ዓ.ም እ.አ.አ. ጀምሮ በጣም ብዙ የምርምር ውጤቶች ወጥተዋል፡፡ እነዚህ የምርመራ ውጤቶች ቫይረሱ እንዴት እንደሚተላለፍ፤ምን አይነት በህርያት እንዳሉት እንዲሁም የበሽታው ምልክቶች ምን እንደሆኑ መከላከያ መንገዶች የትኞቹ እንደሆኑ ጠቁመዋል፡፡ በመላው ዓለም እየተከናወኑ ባሉ የፀረ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ዘመቻዎች ላይም ጥቅም ላይ በመዋል ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ የዚህ ጽሑፍ አላማም ጥናቶች ከጠቆሟቸው ምክንያቶች መካከል የተለያዩ ዋቢ መፅሐፍትን በመጥቀስ በካናዳ የሚገኙ የማህበረሰባችን ክፍሎች ራሳቸውን ከኤች አይ ቪ/ ኤድስ እንዲጠብቁ ጥቂት አስተዋፅኦ ማድረግ ነው፡፡ እንደሚታወቀው ኤች . አይ. ቪ. አለውን ልጅ ተፈጥሮአዊ የሆነ የበሽታ መካለከያ አቅም በማዳከም ለኤድስ በሽታ እንዲጋለጥ የሚያደርግ ነው፡፡ ይህ ቫይረስ የሚተላለፈው በደም ንክኪና ከሰውነታችን በሚመነጩ የተለያዩ ፈሳሾች አማካኝነት ነው፡ ፡ በመሆኑም የደም ለደም ንክኪንም ሆነ የፈሳሽ ልውውጥ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው እንዲተላለፉ የሚያደርጉ መንገዶች አሉ፡፡ ከእነዚህም ጥቂቶቹ ልቅ የሆነ የግብረ ስጋ ግንኙነት፣ክፍት ቁስል፣መርፌና ስለት ያላቸው ነገሮች ምክንያት ነው፡፡

በዚህ ፅሑፍ ውስጥ ለኤች.አይ.ቪ. የመጋለጥ ሁኔታን ሊያሰፉ የሚችሉና ከራሳችን ቁጥጥር ውጭ እንድንሆን የሚያደርጉትን አደንዛዥ እፆችንና አልኮልን እንመለከታለን፡ ፡ለዚህም ሰዎች አልኮልን ለምን እንደሚወስዱ የሚያመለክቱ ንድፈ ሐሳቦችን እንዲሁም አደንዛዥ እፆች የሚባሉትነ በምሳሌነት ለማንሳት ምን አይነት ጉዳት እንደሚያደርሱና እንዴት ለኤች.አይ.ቪ. ለመጋለጥ እንደሚያበቁን እናያለን፡፡ እ.አ.አ በ2009 ዓ.ም በካናዳ መንግስት የህብረተሰብ ጤና ኤጀንሲ አማካኝነት ታትሞ የወጣ (ፀሑፍ 1) አንድ የጥናት ውጤት እንደሚያመለክተው አፍሪካዊና የካረቢያን ዝርያ ባላቸው የካናዳ ነዋሪዎች ውስጥ (ኢትዮጵያውያንን ጨምሮ) የኤች.አይ.ቪ./ ኤድስ ስርጭት በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ በጥናቱ ላይ እንደተጠቀሰው በእነዚህ የማህበረሰቡ አባላት መካከል ለኤች. አይ.ቪ. ስርጭት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ካደረጉት ነገሮች መካከል---

1. ኮንዶም አለመጠቀም
2. ተመርምሮ ራስን ለማወቅ አለመፈለግ
3. ኮንዶምን ለመጠቀም ጊዜ የማይሰጥ ምስጢራዊና ቅፅበታዊ የግብረ ስጋ ግንኙነት ማድረግ
4. ከኤች.አይ.ቪ. ጋር የሚኖር መስሎ አለመታየት አለማሳወቅ
5. አልኮልና አደንዛዥ እፆችን (ማሪዋና፣ጫት፣ኮኬንን---) መጠቀም
6. በወሲብ ንግድ ላይ መሰማራት ናቸው

## አልኮልና ኤች.አይ.ቪ.

በ2003 እ.ኤ.አ የታተመ( ፅሑፍ 2) እንደሚጠቁመው አልኮል ከካናዳ ህዝብ የዕለት ተዕለት ኑሮ ጋር የተዛመደ አንዱ የባህሉ አካል ነው፡፡ በ17ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ከመጀመሪያዎቹ የካናዳ ሰፋሪዎች ጋር ተያይዞ የተጀመረው የአልኮል መጎንጨት ባህል ዛሬም ድረስ ከህዝቡ ኑሮ ጋር ተዋህዶ ያለ እሴት ነው፡ ፡ በዚሁ ፅሑፍ ላይ በ1990ዎቹ አጋማሽ ላይ አንድ እድሜው/ዋ 15 አመት የሞላው /ት የካናዳ ነዋሪ በአመት በአማካይ 7.52 ሊትር (2 ጋሎን) ንፁህ አልኮል እንደሚጠጡ ተጠቁሟል፡፡ በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አልኮል ይወስድ የነበረው በወሊድ ጊዜ የሚከሰተውንና የተለያዩ ህመሞችን ለማስታገስ እንዲሁም በጊዜው ከነበረው የመጠጥ ውሃ የተሻለ ስለነበር ነው፡ ፡ (ይህ ዛሬም በገጠሪቱ ኢትዮጵያ አካባቢ የተለመደ ነው) ዛሬስ? ዛሬ ላይ ሆነን አልኮልን የምንጠቀምባቸው የተለያዩ ምክንያቶች ሊኖሩን ይችላሉ፡፡ እነዚህን ምክንያቶች በንድፈ ሐሳብ ውስጥ ለማስገባት እንዴት ለኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ተጋላጭ እንደሚያደርጉን እንመለከታለን፡፡ በካናዳ መንግስት የህብረተሰብ ጤና ኤጀንሲ (2009) የታታመው ፅሑፍ በግልጽ እንዳስቀምጠው በአገሪቱ ውስጥ በሚገኙ ጥቁር ህዝቦች እጅግ ከሚዘወተሩ ነገሮች አንዱ አልኮል ነው፡፡

## አልኮል ለምን ይጠጣል?

ፅሑፍ 3

1. ራስን ከጭንቀት ለማላቀቅ / Tension — reduction theory

ይህ ንድፈ ሃሳብ የሚመለከተው እጅግ በጣም ከተለመዱት አልኮልን የመጣጣት ምክንያቶች ውስጥ ቀዳሚውን ነው፡ ፡ ስራቦታ ተበሳጭቶ የመጣ (የመጣች)፤ ቤት ውስጥ ስምምነት የጣ(ች) ከጓደኞቹ(ቿ) የተጣለ (ች)፤ በኑሮ የተማረረ(ች)፤ያሰበው(ችው) ያልተሳካ ወዘተ ራሳችንን ለመርዳት ይረዳናል በሚል አልኮልን እንደሚወስዱ ይናገራሉ፡ ፡ ይህም የሚሆነው አልኮል ለቅፅበትም ቢሆን ትልቁን ማንነታችንን ረስተን ጊዚያዊ የሆኑትን ነገሮች ላይ እንድናተኩር ስለሚያደርግ ነው፡፡ ለኤች. አይ.ቪ. የምንጋለጠውም በዚህ ምክንያት ነው፡፡

2. ከማህበረተሰቡ የተማርነው ነገር ለመተግበር (social learning theory)

የሰው ልጅ መለያው ከሆኑት ነገሮች አንዱ ማህበራዊ በህርየትን የሚያሳይ መሆኑ ነው፡ ፡ በግሉ የሚያሳያቸውም ባህርያት ቢሆኑ ማህበረሰቡ ውስጥ ከሚታዩት የተለዩ አይደሉም፡፡ ከዚህ መማር የምንችለው ነገር ሰዎች አልኮልን የሚጠጡት በማህበራዊ ባህርያቸው ምክንያት ከሌሎች ስለሚማሩት ነው ማለት ነው፡፡ በዚህም የሚማሩት መጠጣትን ብቻ ሳይሆን ተያይዞ ያለውንም ችግር ነው፡፡

ከላይ ያየነው በካናዳ መንግስት የህብረተሰብ ጤና ኤጀንሲ (2009) የተደረገው ጥናት እንደሚያሳየው ካናዳ ውስጥ በሚገኙት ጥቁር ህዝቦች መካከል አልኮል መጠጣት የእርስ በርስ ቅርርብን እንደሚያጠናክር ተደርጎ የሚታመንና አብዝቶ መጠጣት የጤና ችግር ሊያመጣ ይችላል ተብሎ እንደማይገመት ተጠቁሟል፡፡

እዘህ ላይ በእኛ ማህበረሰብ መካለል ያለውን ባህልም መመልከት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ በተላያዩ የአገራችን ክፍሎች አልኮልን መጠጣት እንደነውር ሳይሆን እንደመልካም ነገር የሚቆጠር ነው፡፡

ለምሳሌ፦ ደብረብርሃን አካባቢ ካቲካላን መጠጣት፣ጠላ መጠጣት፣ በጋምቤላ አካባቢ በርዴ በካቲካላ መጠጣት፣ ትግራይ አካባቢ ያለውን ጠላ በቅል መጠጣት፣ ወይም በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ጠጅን መጠጣት የእርስ በእርስ ቅርርብን ማጠናከሪያና የልምድ ልውውጥ ማወራረጃ ናቸው፡፡ እነዚህ ምሳሌዎች የሚያሳዩን አልኮል በማህበረሰባችን ውሰጥ ያለውን ቦታና ለኤች.አይ.ቪ. ተጋላጭ እንዲሆን ማድረጉን ነው፡፡

3. የምንፈልገው ነገር የሚሳካ ስለሚመስለን (Expectancy theory)

በማንኛውም ሰው አእምሮ የሚተወስ ነገር በአንድ ወቅት የተከሰተ ወይም በስሜት ህዋሳቱ አማካይነት ያገኛቸው ናቸው፡፡ አልኮልን የሚጠጡ ሰዎችም በአንድ ወቅት ያወቁትን ነገር ተግባራዊ የሚያደርጉበት ወይም ጓደኞቻቸው፣ ቤተሰብ፣የቅርብ ወዳጅ ወዘተ ሲያደርጉት ተመልክተው ከነዚያ ሰዎች ያዩትን ነገር ተግባራዊ ለማድረግ የሚሞክሩበት ነው፡፡ ብዙ ሰዎች አልኮልን የሚጠጡት ለአንድ ወቅት ከሞከሩት በኋላ ያዩትን ያንን ስሜት ለማሳካት በሚል ነው፡ ፡ እዚህ ላይ አልኮል መጠጣት ያልጀመረ ሰው ምን ማድረግ እንደሚኖርበት በአግባቡ መመልከት ይችላል፡ ፡ የአልኮል ሱስ እጅግ በጣም ከባድ ከሆኑና የራስንም ሆነ በቅርብ ያለ ቤተሰቡ፣ወዳጅ፣ጓደኛ፣ ወዘተ የሚጎዳ ድርጊት ነው፡፡ በመሆኑም ሲያደርጉት አይቶ ጥንቃቄ እንዲያደርግና ራስን ከኤች.አይ.ቪ. ብሎም ከተያያዘ ችግሮች ለመጠበቅ የሚመክር ንድፈ ሃሳብ ነው፡፡

4. አእምሮታዊ ንድፈ ሃሳብ (Cognitive theories)

ይህ ንድፈ ሃሳብ የሚዳስሰው ለአንድ ወቅት በተከሰተ የማህበረሰብ እንቅስቃሴ በአእምሮአችን ላይ ለተፈጠረ መረበሽ ምክንያት አልኮልን እንደጭንቀት ማላቀቂያ አድርገን ስንወስደው የሚፈጠረውን ሁኔታ ነው፡፡ ማንኛውም ሰው በህይወት ሲኖር የአእምሮ መረበሽ ሊያጋጥመው ይችላል፡፡ ለምሳሌ፦ያሰበው ነገር አልሳካ ሲለው፣በዘር ማግለል(racism) አማካይነት፣ውጤት በማጣት ወዘተ ሊሆን ይችላል፡፡

5. በጤጪነትና በአልኮል ሱስ ላይ ዘረመል ያለው ተጽእኖ (Genetic influences on drinking and alcoholism)

በአሁኑ ወቅት በብዛት እየታመነባቸው ከመጡ ሳይንሳዊ ትንታኔዎች አንዱ ጠጪነት ወይም አልኮል ሱስ ከዘር ወደዘር የሚተላለፍ መሆኑ ነው፡ ፡ ይህም ብቻ ሳይሆን በየጊዜው የምንጠጣው አልኮልና ብዛቱም ከእኛ ወደ ልጆቻችን የምናወርሰው ነገር እንደሆነ ተጠቁሟል፡፡ በመሆኑም ጠጪነታችን ያሉበትን ችግሮች ሁሉ እናስተላልፋለን ማለት ነው፡፡ ጠጪነት በልጆች ጤንነት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደርሳል፡፡ ከእነዚህም መካከል የአእምሮ ዝግመት፣የሰውነት ክፍሎች አለመስተካከል፣የፊት ቅርጽ መበላሸት ወዘተ ናቸው፡፡ እነዚህ ቀጥተኛዎቹ ጉዳዬች ሲሆኑ ዋናው ርዕስ ጉዳያችን ኤች.አይ.ቪ.ም ከአንድ ሰው ወደ ሌላ እንዲተላለፍ ከሚረዱት ዋና ሀይሎች መካከል ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል፡፡

ከላይ ያየናቸው አልኮልን የተመለከቱ ንድፈ ሃሳቦች አምስቱ ብቻ ናቸው፡ ፡ ይሁንና ሰዎች አልኮል እንዲጠጡ የሚገፋፉቸውን ነገሮች በጥቂቱ እንድንረዳ እያደረጉ ናቸው፡ ፡ አልኮልን የመጠጣት ጉዳት በተለያዩ ጥናቶች የተረጋገጠ ነው፡፡ ኤች.አይ.ቪ. እንደ ዋና መሳሪያ እየተጠቀመ ያለውም በአልኮል የተረበሸ አእምሮን ነው፡ ፡ ስለሆነም ጥንቃቄያችንን ይጠይቃል፡፡

ክፍል 2 ይቀጥላል


በኤች አይቪ ኤድስ ጉዳይ ማንኛውንም መረጃ ለማግኘት ወይም መሳተፍ ቢፈልጉ 1950 Danforth Avenue ወደሚገኘው ማሕበራችን ብቅ ይበሉ


ወይንም

በ 416-694-1522 Ex 27 ይደውሉልን

የኢትዮጵያውያን ማሕበር በቶሮንቶ እና አካባቢው የኤች አይቪ ኤድስ መከላከያ እና ትምህርት ፕሮግራም

*www.ethiocommun.org*

Discount Optical Inc.
1312 Bloor St., W., Toronto, Ontario M6H 1P2
532-7997 (West & North Corner of Bloor & Lansdowne Subway)
1 Hour Service
986 The Queensway
Etobicoke M8Z 1P6
416-253-7224


We Beat Everybody's Prices Because We Grind Our Own Lenses
DuraSoft Colours

FREE FRAMES
Compare our Prices
Single Vision ................ Reg. $60.00 Sale $39.00 & up to +3.00
SV Anti-reflection ............Reg. $120.00 Sale $85.00
Fitted by Certified Contact lens fitter
Transitions Single Vision ...Reg. $140.00 Sale $89.00
Progressive (No Line Bifocal) .... Reg. $150.00 Sale $99.00
Progressive Transitions (No Line Bifocal) ... Reg. $280.00 Sale $199.00
Bifocal (28 Bifocal) ..........Reg. $89.00 Sale $59.00
Bifocal Transitions Ft 28....Reg. $190.00 Sale $139.00
Contact Lenses
Disposable Omni (55) 4 Boxes $99.00
Disposable Omni (55) 2 Boxes $50.00
Soft Lenses (Daily wear) $65.00
Colour Disposable 1 Box (3 Pairs) $65.00
We carry Popular Imported Brand Name Frames
Large Selection of Latest Eye Fashions
(Visit our Showroom) 2 Locations
Low Prices and High Quality Service
We Craft Quality Lenses In Store Lab
Eye Examination Arranged (next door)
Over 3000 Frames to choose from
Large quantity of contact lenses in stock
Satisfaction Guaranteed

# “የመንገድ ላይ ወግ” ሲጀምር -ምፀት!!


ሚካኤል ምስግና (ሸውድን)

… ዕኩለ ቀን ከረፋዱ ላይነው። ሰው በሙቀቱ ሃይል ጨርቁን ሁሉ ጥሉዋል። የበጋው ወራት በመግባቱ ፀደይ በርትታለች። ስካንዲኒቪያ ላይተቀምጬ ካናዳን በህሊናዬ እየቆዘምኩ በትዝታ “ሶምሶማ” መጋለብ ጀመርኩ። ከቀጠሮዬ አንድ ሰዓት አስቀድሜ በመምጣቴ መሃል አደባባይ ከሚገኘው “የአይሪሾች” ቡና ቤት ጥግ ፈልጌ ተቀመጥኩ።

የከተማውን የሰው ግርግር በቤቱ መስታወት አሻግሬ እየቃኘሁ በእጀ የያዝኩትን “የአውራምባ ታይምስ” ጋዜጣን ማገላበጥ ጀመርኩ። ጥሩ የእረፍት ጊዜ ማጣፈጫ ነበር፡፤ የቀድሞው የህወሓት/ወያኔ አባል የነበሩት አቶ “አብረሃም ያየህ” በጋዜጣው ላይ የጀመሩትን ተከታታይ አንደ ለመንገድ “እንጎቻ ወግ” በማወራረድ ዘና ብዬ ተቀምጫለሁ። በአንድ በኩል የቀድሞው ወዳጆችን ድምጻቸው ጠፍቶብኝ ሳፈላልግ ጎብጬ ልከዘራ እንዳልበቃ ስጋት ቢጎበኘኝም “መቀሌ ገብቱዋል…!” መባሉን ሰምቼ ወደ “ታላቁዋ የትግራይ ሪፓፐሊክ” ፤አቀና “ቪዛ” ሳፈላልግ ያለሁት ዛሬም “ዴንማርክ ነው …!” በማለት እረ አለሁ..! ስላሉና ድምጻቸው በመስማቴ ደስታዬ ወሰን አልነበረውም። ያውም እሳቸው እንደሚሉት “እግዚአብሔር ሲፈጥራት እጁን ታጥቦ በሠራት በዴንማርክውስጥ …ቂ..ቂ..ቂ… ! በሌላ በኩል እግዚአብሔር ዴንማርክን እጁን ታጥቦ ሲፈጥራት አቶ አብርሃም ያዬህ “ውሃ” ያመላልሱ ነበር …? ማለቴም አልቀረም።

በእስልምና ፎቢያ(ፍርሃት) በምትሰቃየው “ገለልተኝነትን” እያራገበች ነገር ግን ከግሎባላይዜሽኑ ዓለም የሃይል መራሾች ጎን የተሰለፈችው ሀገር ትናንት “ወያኔን አሻዕቢያ” ሀገር በመቀራመቱ በዐውደ ዘመቻቸው ወቅት “የአንበሳውን ድርሻ ስትለግሳቸው የነበረች “ገለልተኛ” ሀገር በመሆኑዋ በጥርጣሬ የሚገላምጡዋት ሃተተኛ በአንጻሩ ይኖራሉ አሉ። ስደት የዛፍ ላይ እንቅልፍ በመሆኑ ዛሬ ትውልዱ የሃፍረት ማቅ ለብሶ ሀገር ላገር ሲንከራተት፣ “ታግሎ አታግሎ” ለአንዲት ሀገሩ ማብቃት ሲገባ ለመጠለያ “ዲፕሎማሲ” ሲባል ብቻ እገሌ የተባለው ሀገር ሲሠራው ሲፈጥረው “እግዚአብሔር እጁን ታጥቦ ነው..!” እያሉ ስደትን ላቀረው ትውልድ ማበረታታቱ በምንም መመዘኛ ሚዛናዊ አይደለም ሲሉ በመቁዋጠር ከዚህ ቀደም ነፍጠኞቹን (ኢትዮጵያዊያንን) ከአሥመራ ላይ “የወርቅ ጥርሳቸውን” እያስወለቀ ያባረራቸውን “ሻዕቢያ”ን የኤርትራ መንግሥት እንግዳ ተቀባይ ነው…!” በማለት በዘጠና ዲግሪ አቶ አብረሃም ያየህ ገልብጠው ሲቀባቡት የመደመጣቸውን እንደምታ ተንተርሰው ጉም ጉም የሚሉ አቃቂረኞች አይጠፉም አሉ።

የእዝ ቀጠናቸውን አሥመራ ላይ አድርገው ለነፍጠኛው ሀገር (ለጦቢያው) አንድነት እንታገላለን …! በማለት የአሥመራው ባላባትን ጎይታይ “ኢሳያስን” ተማምነው እንደ “በግ ላት” ጭራቸውን የሚወዘውዙ “ቁጭ በሉ ነጻ አውጭዎች” ወያኔን አንበርክከን አንድ ጊዜ “ለፋሲካ” ሌላጊዜ “ለቡሄ” ሐዲሽ ዕምባባ እንገባለን ..! እያሉ ሲያስጎመዥን በተስፋ ጥርሳቸውን ከጨረሱ ዜጎች መካከል “የጎሣ ባንዴራዬን እጃፌ ላይ አልተክልም…!” በማለት ባህር ማዶ እንገፍ እንገፍ ከሚሉት ነፍጠኞች መካከል አንዱ እኔ በመሆኔ አቶ “አብርሃም ያየህ” ያ አሉኝ የሚሉት “ጦር” ሸገር አቅንቶ ድፍን ጦቢያውን ያልተቆጣጠረበት ሚስጥር ምንድን ነው..? ምናልባት የመረብ ምላሽ ወንዝ ሞልቶ ጦሩን አላሻግር ብሎ ይሆን..? ዘንድሮ መቸም ተፈጥሮ እራሱ አምጹዋልና …! በማለት እርር ድብን ማለቴ አልቀረም። የእኔ እነገር…!



ጸሐይ እየበረታች መጣች። የያዝኩትን ጋዜጣ ሽብለል በማድረግ ጠረጴዛው ላይ አኑሬ ቡናዬን አንስቸ ማግ ማግ አደረኩ። ቀዝቅዞ ነበር። ከተቀመጥኩበት ካፌ ቤት ማዶ ወንበር ላይ ከምትታይ አንዲት ልጅ እግር “ሳዱላ” ላይ ዕይኖቼ አረፉ። የጋሸበውና የተዘናፈለው ፀጉሩዋ ከትክሻዋ ወርዶ መቀመጫዋ ላይ ደርሱዋል። በሠራው ገላዋ ላይ እራፊ ጨርቅ ጥላለች። የደሙዋ ዑደት በቆዳዋ እስኪታይ ለብሳለች። ቆም -ቆም ያሉትን ጡቶቹዋ “ምነው ልጁዋ ባደረገኝ ..!” ያሰኛል። በድንገት “አታመንዝር..!” የሚለው የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ለምን እንደሆነ ትዝ አለኝ። ሰሞኑን የስዊድን የሮያል-ፋሚሊ በማሬጅ ስካንድል (ቅሌት” ተዘፍቆ ወሬ ሁላ የንጉሡ ጉዳይ ነበር። ባለቤታቸውን ንግሥት “ሲልቪያን” በማጀት አስቀምጠው “በኮሽም” ለቀማ እያሳበቡ በመውጣት ንጉሥ “ካርል ጉስታቭ” ከዕቁባቶቻቸው ጋር ሲቀብጡ በመገኘታቸው ሚዲያው ሁሉ እያብጠለጠላቸው ነበር። እኔ ግን አላመነዘርኩም። ብመነዝርስ…? ዶላር እንኩዋን ይመነዝር የለም እንዴ..?

በድንገት ከሃሳቤ ጋር ሙግት ገጥሜ የውሸት ፈገግታ ፈገግ አልሁ። ሲመጣብኝ፡ እንደዚያው ነኝ። የሚሰማኝን “ትኩሳት” በሌጣ ወረቀት ላይ መለካት እወዳለሁ። አንተ ደግሞ የብሪታኒያ የስዊድን ሮያል ፋሚሊ እስካንዳል ትላለህ እንጅ የወያኔ መሪዎችስ ሀገር በመቀራመቱ ዘመቻ ብቻ ሳይሆን አንዱ የአንዱን”ሚስት” ይቀማ የለ..! የሚለው የቀድሞው የወያኔዎች “የቤት ልጃቸው” የፕሮፖጋንዳ አበጋዝ የነበረው “የተስፋዬ ገ/አብ” አባባልም ትዝ አለኝ። መቸም የተስፋዬን የበእር አጣጣሉን አደንቅለታለሁ። ችግሩ”ችሎታውንም፣ ሙያውንም” ለጥላቻ ለተንኮል አደረገው…! ምን ነበር ያለው..? የወያኔ መሪዎች ሚስቶቻቸውን ይበዳደራሉ አይደለመንዴ ያለው…? ልክ “ከዓለም ባንክ” ከረደኤት ተቁዋሞች በነፍጠኛዋ ሀገር ስም እንደሚበደሩት “ዶላር” መሆኑ ነው…! ቀዳማዊት አዜብ መጀመሪያ የሙዋቹ የመረጃ ፊታውራሪ የክንፈ “ሚስት” ነበረች። የአንበሳውን ድርሻ ሁሌ የሚወስደው “ጀከሩ” መለስ ዜናይ የሁዋላ ሁዋላ ከክንፈ እጅ ላፍ…! አደረጋ። የቀድሞው የአይ. ኤም.ኤፍ ቀለብ ሰፋሪያቸው የነበረው ፈረንሳያዊው “ካህን” እንኩዋንሚስቱን አስቀምጦ የአንዱዋን ድንግል መሬት አስገድዶ ሊያርስ ሲል “ነጻ ገበያ ነዋ…!!” ነው የርክላይ የመያዙም ዜና ትዝ አለኝ። አንዳንድ ሃቲተኞች የወሲብ ውስልትናው ጥልፍልፍ ወሬ ምናልባት ከመጋረጃው በስተጀርባ “ቦተሊካዊ” ይዘት ይኖረዋል የሚል አንደምታ ስላላቸው ይኼንንም ግምት ውስጥ አስገባዋለሁ። የአውሮጳና የአሜሪካ የዜና አውታሮች የሚያራግቡትንሁላ እንዳለ መቀበል ያስቸግራል።

በድንገት የእጇ ሞባይል ስልክ አቃጨለ። ኪርር…ኪርር….! ከሃሳቢ እነቃሁ። አርቲስት “ዣን ሥዩም” በቀጠሩዋችን መሠረት መምጣቱናበሰረኝ። ተጨባበጥንና ወንበር ስቦ ተቀመጠ። “ዣን ሥዩም” ደግሞ ምን አይነት ስም ነው..? አትበሉ። የማዕረግ ስም ነው። ሀበሻው በስዊድን አርቲስት “ሄኖክ አስበ” በሚለው መተሪያ ያውቀዋል። ላለፉት በርካታ ዓመታት በስዊድን የኖረ በሙያው የዜማ አቀንቃኝ የሙዚቃ መሣሪያ ተጫዋች ሁለገብ የሙያ ሰው ነው።

አንድ ጊዜ በስቶኮልም ተከፍቶ በነበረ የብሮድካስት (የሬድዮ ስርጭት) አዘጋጅን ዓቅራቢ በመሆን በጋዜጠንነት ሙያም ድርሻውን ተወጡዋል። የአንዳንድ ሰው ሁለገብ ችሎታ መቸም ይገርማል። ከአርቲስት “ሄኖክ አስበ” ጋር ቁጭ ብለን ወግ ስንጠልዝ ከታሪክ ጋር የተጨባበጥኩ ይመስለኛል ብል ማጋነን አይሆንም። የባዕዳን ሃይሎች የማደጎ ልጆች የሆኑት የዛሬዎቹ የሥራአቱ አቀንቃኞች “ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን” ሲያራክሱና በማንነት ዝቅጠት (ክራይስስ) ውስጥ ይኼ”ተማርኩ..በቃሁ…!” የሚለው እሊት (ምሁር) ጭምር መለሠ ዜናይ ያሰፋለትን የጎሣ ቁምጣ ጥልቆ ሲዞር ሲታይ አርቲስት “ሄኖክ አስበ” ግንየሰው ልጅ ዕውደ ታሪክ መነሻና መድረሻ “ጦብያውናት” ይለናል። ጭብጥህ ምንድን ነው..? ሲባል ከርሠ መቃብር ፈንቅሎ የዐለት ድንጊያ ፈልፍሎ ለምርኩዝነት ያቀርብልናል። ተዘዋውሮ ያላየው አድባራትና ገዳማት በሀገር ውስጥ አይኖርም። “በኢትዮጵያዊነትና በኢትዮጵነት ላይ የሚያነጣጥሩ በርካታ የመጽሃ ፍጥራዞች ባለቤት ነው።

በፍልስፍና፣ በቁዋንቁዋ፣ በሰው ዘር አመጣጥ (አንትሮፖሎጅይ)፣ በቲዮሎጅይ(ሃይማኖት) መነሻዋ ጦቢያው እንጅ ከቶ ማን ይኖራል? በማለት በራስ

ወደ ገጽ 15 ዞሯል







# YAMAMOTO: TIME FOR US TO RE-ASSESS SUPPORT FOR DISAPPOINTING MELES ZENAWI

## WikiLeaks | September 5, 2011

A June 2008 leaked Cable of US Embassy Addis Ababa shows the Ambassador so irritated that he proposed:

[we]will make it clear to the Ethiopian government at the highest levels that the U.S.-Ethiopia strategic partnership requires reciprocity and that, for the United States, counterterrorism and security cooperation does not occur in a vacuum……the long-term risks to USG interests posed by robust support for the EPRDF government, as well as the level and breadth of our foreign assistance programs, may have to be reassessed.

What did Ethiopia do? Ambassador Yamamoto presents a long list:

1. In March, 2005, Ethiopia became the first country in 20 years to expel the International Republican Institute (IRI), the National Democratic Institute (NDI) and International Foundation for Electoral Systems (IFES), effectively eliminating USG programming in political participation. IRI, NDI and IFES have not been allowed to return.

2. the National Electoral Board….effectively sidelined the Carter Center from training the limited domestic observer organizations in the run-up to the April 2008 local elections despite the ready allocation of USD 1.358 million in USG funding and additional support from others.

3. The [ruling party] EPRDF refused to participate in our Voluntary Visitor program planned in Fall 2007 on multiparty democracy for a cross-section of political party representatives.

4. a draft civil society law currently under consideration would ban any foreign funded international or non-governmental organizations (NGOs) from working to further democratic reform.

5. Ethiopia was until earlier this year the only African country to jam persistently Voice of America (VOA) broadcasts (and has done so off and on since the mid-nineties).

6. Ethiopia has rejected 29 of 41 security assistance training offers designed to strengthen mutual understanding and enhance future cooperation, including three War College slots.

7. Ethiopia also turned down Special Operations Forces training, perhaps the only country to do so in the recent past, spurned a number of high-level seminars and turned down, by not acting on U.S. offers, Exercise Related Construction (ERC), Defense Reutilization Marketing Service (DRMS), and combat engineer assistance — all programs specifically requested by the ENDF.

8. The Ethiopian National Defense Forces (ENDF) barred Combined Joint Task Force – Horn of Africa (CJTF-HOA) civil affairs teams from the Ogaden in 2006 (they have not been allowed to return) and expelled United States Defense Department counterterrorism and border security trainers from Bilate and Hurso training camps in 2007, despite USD 3 million in USG-funded infrastructure upgrades at the camps.

9. Earlier this year, the GoE rejected a USG-proposed bilateral agreement designed to address the threat of Man-Portable Air Defense Systems (MANPADS) in Ethiopia, and has repeatedly refused USG access to a North Korea-supported munitions factory in Ambo.

10. The Ethiopians told the Embassy that they cannot support the International Military Education and Training (IMET) program due to their current military operations tempo, yet accepted some 60 training slots in Russia. Ethiopia also declined a USG offer of assistance for direct support for developing a non-commissioned officer corps.

11. Ethiopian State Security refused Federal Bureau of Investigation (FBI) attempts to question a detained person of interest despite five weeks of FBI attempts to gain access to the individual.

12. The United States Treasury Department was forced to suspend its Office of Technical Assistance (OTA) intermittent advisory program after the GoE refused to take action to develop AML and CFT regulations and legislation despite ten months of negotiations with OTA (Ref F). Although the GoE signaled its interest in OTA assistance, Senior National Bank of Ethiopia (NBE) officials declined every opportunity to support necessary reforms.

13. For more than a year the GoE has delayed the registration and launch of an American Chamber of Commerce in Ethiopia and rejected Embassy advocacy for the diversification of the telecommunications sector.

By way of contrast, the GoE, consistent with its statist tendencies, over the same span awarded a Chinese company a USD 1.5 billion monopolistic contract for telecommunications, granted the Chinese government the right to develop a USD 700 million special economic zone for Chinese companies in Ethiopia, and announced that another Chinese company would be granted a no-bid contract to build a highway in Ethiopia.

14. Earlier this year, the GoE requested "re-negotiation" of Ethiopia's tax exemption for programs funded by U.S. foreign assistance. Without further dialogue or negotiation, the GoE has unilaterally begun taxing the approximately USD 700 million in U.S. Foreign Assistance-funded procurements and subjected implementing partners' procurements to full import duties, value added tax and additional taxes.

15. The GoE now requires a USD 200,000 deposit by U.S.-funded NGOs into a blocked Ethiopian bank account before considering work permit applications for expatriate staff.

16. The GoE has restricted access of USG-funded NGOs to conflict-affected populations in the Ogaden area of the Somali region and placed at least one American citizen working for an international NGO (INGO) under house detention.

17. Already this year, the GoE has informed USAID that it will no longer register USAID implementing partners. Women's Concern International (WCI) and the American Bar Association (ABA) have both been refused registration in recent weeks despite being requested by the Ethiopian Parliament and Supreme Court respectively to provide assistance. The Foreign Ministry advised USAID that, notwithstanding the GoE's earlier request for judicial assistance, the ABA is a "consultant" to USAID therefore and USAID should arrange for ABA's phone lines, bank accounts and other basic services during the life of the three-year program.

Therefore, the Ambassador suggested to his bosses at Foggy Bottom that :

A paradigm shift must occur in the United States' discourse with Ethiopia on foreign assistance. Over the past year, the USG has delivered on all GoE claims of "broken promises" in order to enhance the security of the Ethiopian state and to help Ethiopia combat terrorism. However, even as the USG met its promises, Ethiopia consistently rebuffed USG efforts to pursue other priorities, notably political and economic reform, and also turned down a significant number of programs designed specifically to enhance trust, communication and security cooperation between our militaries. The GoE rejected many of the programs it specifically requested.

Actually, it doesn't seem the Ethiopian Military formal requested most of the programs. As another Secret Cable of the Embassy states, 'the training program offerings were based on Ethiopia's needs and past planning sessions'.

Yet, the Ambassador concluded his remark by mixing some lofty terms. It reads:

The Ambassador will take every opportunity to highlight for Ethiopian leadership the linkage between democratic governance/free market economy and social cohesion and stability, and urge the GoE to reconsider the current statist and authoritarian trajectory of its policies. If the GoE persists in rejecting United States priorities in such critical areas as transparency (especially AML and CFT), governance (especially civil society support for political), market reform (especially necessary diversification) and security cooperation, the long-term risks to USG interests posed by robust support for the EPRDF government, as well as the level and breadth of our foreign assistance programs, may have to be reassessed.

*IMPORTANT SECTIONS*
*WikiLeaks - Part One*
*WikiLeaks - Part Two*

ከገጽ 13 የዞረ

በመተማመንመንፈስ ያስረግጣል። እጅግ አንደበተ ርቱዑ ስለሆነ ስለሀገሩ ሲዘከር ቢውል አይደክመውም። "ተማርኩ የሚለው ክፍል ባህር ማዶ በፈረንጅተቁዋማት ገብቶ ነጮች የራሱን ታሪክ በርዘውና አጨቅይተው ያስተማሩትን አሰሥ ገሰሡን "ሳይንስ" ወደ ሀገሩ ጭኖ በመምጣት ሀገሩን የቤተ ሙከራ ሳይንስ መፈተሻ አድርጎታል" የሚል መደመሚይ ዓለው።

ኢትዮጵያን ለማፈራረስ ባዕዳን "ወያኔና ሻዕቢያ"ን አስታጥቀው (የራሴ ማጠንከሪያ ነው) በመላክ አፍራሽ ሚን አሲጫወቱ "የሃይማኖት ተቋዋሞች የአንበሳውን ድርሻ ወስደዋል" ይለናል። የቀረውን የራሱ እንጎቻ ወግ ክፍል አንድ በጥቅሉ ላነሳሁለት ጥያቄዎች የሰጠውን መልስ እንደወረደ ቀጥዬ በጥሬው አቀርበዋለሁ-

ጥያቄ፡- ራስክን ለሐዋርያ ጋዜጣ አንባቢዎች ባጭሩ ብታስተዋውቅ?

ሄኖክ፡- መጠሪያ ስሜ ሄኖክ አስበ፤ ዕለተ ትዉልዴ መስከረም ፱ቀን ፲፱፻፶፱ ዓ.ም፤ የመጀመሪይ አደረጃ ትምህርቴን በልደታ የወንዶች ትምህርት ቤት (ካቴድራል በመባል ይታወቃል)፤ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ያጠናቀቅሁት በሐረር መድሃኔዓለም አጠቃላይ ሁለተጋ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው።

ዓድሜ የዓግዚአብሔር የግል ሥጦታ ነውና በቁጥር አልጠራውም። የግድ ማወቅ ካለብህ ግን አስላው።

ጥያቄ፡- ከሕይወት ገጠመኞችህ ያዘንክባቸውና የተደሰትክባቸው ቢኖሩ ምን ይመስላሉ?

ሄኖክ፡- ከሕይወት ገተመኞቼ የሚያሳዝነኝ የኢትዮጵያዊያን ወገኖቼ ያቿንየመሰለች ልዩ ዓየር ንብረት፤ የበዛ የከርሰ-ምድር ሃብት፤ ፤ ለባዕድ የተረፈ የውሃ ሃብት ከፈጣሪ የታደለች አገር ያለው፣ በፈጣሪው ላይ አብዮ የስደት ሰለባ እየሆነ የምእራባዊያንና የአረብ ባርያ መሆኑና ለመሆንም በየበረሃውና በየውቅያኖሱ የአውሬና የዓሳነባሪ እራት እየሆነ መቅረት ነው።

የተደሰትክብት አጋጣሚ ላልከኝ፣ እውነተኛውን የኢትዮጵያዊነት ትርጉም የተረዱና የኢትዮጵያዊያንን መነሳት የሚጠባበቁ የተለይየ አገር ዜግነት ያላቸው ሰዎች እንዳሉ ያወቅሁ ቀን ዓይኔን በዓይኔ ያየሁ ቀን የተሰማኝ ደስታ የሚታወሱኝ ናቸው።

ጥያቄ፡- እስካሁን ከሕዝብ ጋር የተዋወቅባቸው የሙዚቃ ሥራዎችህ ምንድን ናቸው፤ ወደፊትስ ለመሥራት ያሰብካቸው አሉ?

ሄኖክ፡- የመጀመሪያው የሙዚቃ ሥራዬ ከሌሎች ከጉዋደኞቸ ጋር በመሆን የሠራነው "ዴልአበሻ" የተባለው መድበል ሲሆን ከእዛም ላይ "ትዝ ይልሻል ወይ" የሚለው ዜማ ይታወቃል። ከዚያም በመቀጠል የሥደት ገጠመኘን የገለጽኩበት፣ እንዲሁም ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊያን እውነተኛ ማንነት ለመግለጽ የሞከርኩበት "ጉድ" የተሰኘው መድብል እስካሁን ለሕዝብ የወጡ ሲሆኑ፣ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ወደፊትም የማቀርባቸው በዝግጅት ላይ ያሉ ሥራዎች ይኖራሉ።

ጥያቄ፡- ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊያንን በሚመለከት የምታካፍለው ጉዳይ ካለ?

ሄኖክ፡- ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን በሚመለከት ላልከኝ፣ ወደ ዝርዝር ትነናው ሳልገባ በአጭሩ ለመግለጽ፣ ኢትዮጵያ ማለት ለእኔ እግዚአብሔር አዳምን ፈጥሮ እንዲኖርባት የሰጠው በምድር ላይ የምትገኘው ገነት ማለት ስትሆን፣ ኢትዮጵያዊያን ደግሞ የአዳም ዝርያ የሆኑ ኼደም ሲል ሰባዊያን (ሳባዊያን) በመባል ይትታእቁ የነበሩ፣በመቀጠልም የአዳም ሰባተኛ ትውልድ በሆነውን አበእግዚአብሔር ፈቃድና ምርጫ በመልአኩ ቅዱስ ሚካኤል አመካይነት ወደ ሰማየ ሰማያት ተወስዶ ከፈጣሪ የተገናኘው፣ ከዚያም ብዙ ጥበባት የተገለጹለትና ሞትን ያልሞተው ቅዱስ ሄኖክ፣ በሱም የልጅ ልጅ በሆነው በኖህና በሶስቱ ልጆቹ፣በሁዋላም የሰላሙዋን ከተማ እየሩሳሌምን በቆረቆረው የሳሌም ንጉሥ በተባለው ከፈጣሪው ትልቅን የብቃት ደረጃ የተቀበለው መልከጼዴቅ ፣ኛ ምለኡ የኲልሄ የመሆንን ብቃት ያገኘ ባለ ሶስት መዋቅረ ሥርወዘር (ዲ.ኤን.ኤ) ይኸውም በሚወልዳቸው ባለ ሶስት ቀለም ልጆቹ የሚገለጽ ልዩ ምልክት ያለው የእውነተኛው ፈጣሪ ሕዝብች(እስራኤል) የምንባለው እኛ ነን። ነገር ግን ዛሬ የአሕዛብን መንገድ በመምረጥ ከፈጣሪያችን በመጣላታችን እነሆ ሁሉም ነገር እያለን ምንም የሌለን ብኩኖች ሆነን በዘመናዊ ባርነት ቀንበር ታሥረን በመማቀቅ ላይ እንገኛለን።

ጥያቄ፡- በሕይወትህ የምትጸጸትበት ነገር ካለ እሱ ምንድን ነው?

ሄኖክ፡- ከምትጸጸትበት ላልከኝ፣ አበው አባቶች ትተው ያለፉትን ጥበብ ለመረዳትና ለመጠቀም የሚያበቃኝን የግዕዝ ቁዋንቁዋ ያለመማሬ፣ በተለይ ብዙ የአውሮፓ አገሮች ውስጥ ሲያስተምሩትና ጥናታቸውን ሠርቀው ባመጡዋቸው የብራና ጽሁፎች ሲያድጉ ሳይ ዘወትር የሚቆጨኝ ነገር ነው።

ወስብሃት ለእግዚአብሔር!!!

